የመጋቢነት አገልግሎትህን ወደ ላቀ ደረጃ አሳድግ

ዳግ ሂዋርድ-ሚልስ

ትርጉም - በሬቨረንድ አማኑኤል ቶማስ

ካልተገለጸ በቀር፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

Email Dag Heward- Mills :
bishop@daghewardmills.org
evangelist@daghewardmills.org

Find out more about Dag Heward Mills at:
www. daghewardmills.org
www. lighthousechapel.org
www.healingjesuscrusade.org

Write to:
Dag Heward-Mills
P.o. Box 114
Korle-Bu
Accra
Ghana

ላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል
መ.ሳ. ቁጥር 15134
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ይህን መጽሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከለ ነው።

መታሰቢያነቱ

ለ ሬቨረንድ ኤዲ አዲ

ለእነኚህ ሁሉ ዓመታት ስላሳየኸኝ ታማኝነትህ እና ጓደኝነትህ

አመሰግንሃለሁ

ማውጫ

ክፍል ፩ - እውነተኛ አገልግሎት

1. የማመሳሰልን አገልግሎት ማስወገድ ለምን ያስፈልጋል 11
2. በአገልግሎት የላቀ መሆን እንዴት እንደሚቻል 18

ክፍል ፪ - ጸሎት

3. አገልጋይ ሁሉ መጸለይ የሚገባበት አሥር ምክንያቶች 23
4. አሥራ ስምንት የመንፈሳዊ ውጊያ እውነቶች 38
5. ጠላትህን ታሸንፈው ዘንድ የጠላትህን ማንነት እንድታውቅ የሚረዱ ሃያ መንገዶች 46
6. መጋቢች ውጤታማ ጸሎት እንዲጸልዩ የሚያደርጉ አምስት መንገዶች . .57
7. ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን እንድንጸልይ የሚያደርጉ ስድስት ምክንያቶች 61
8. ከልብ በመነጨ ስሜት የመጸለይ ሰባት ምሳሌዎች 68
9. በቅንዓት የመጸለይ ሰባት ምልክቶች. 73
10. ረጅም ሰዓት ለመጸለይ የሚረዱ ዘጠኝ እርምጃዎች 77
11. ምልጃን ለመረዳት የሚረዱ ሁለት እርምጃዎች 83
12. ለእያንዳንዱ መጋቢ የሚማልድለት ሰው የሚያስፈልግበት ሃያ ምክንያቶች 85

13. የዝቅጠትን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 88
14. የዓለምን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 91
15. የሥጋን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 92
16. የተፈጥሮ ክስተቶችን በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 94
17. የሰውን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 96
18. የተፈጥሮ ሕግን በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 99
19. የሰይጣንን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 101
20. የጊዜን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 103
21. የሚያደቡ ነገሮችን በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 105
22. የተቆረጡ ነገሮችን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል . . .108
23. የከዋክብትን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል 111
24. ስለ እግዚአብሔር ሕግጋት እንዴት መማለድ እንደሚቻል 114
25. በምጥ ጸሎት ውስጥ እንዳለህ የሚያሳዩ ሰባት ምልክቶች 116
26. በልሳን የምጸልይበት ሰላሣ - ሁለት ምክንያቶች 119

ክፍል ፫ - ጉብኝት

27. መጋቢዎች መንጋቸውን ሊጐበኙ የሚገባበት አሥራ ሁለት ምክንያቶች 125
28. ከጉብኝት ኃይል ጀርባ ያሉ ሦስት ምስጢሮች. 128
29. ስምንት የፍሬያማ ጉብኝት መመሪያዎች 130
30. አሥር የጉብኝት ሕግጋት 132
31. ጉብኝትን ቀላል የሚያደርጉ ሰባት ነገሮች 138
32. ሕይወት የመለወጥ ኃይል ያላቸው አምስት ጉብኝቶች 141
33. ቋሚ የሆነ ለውጥ የሚያመጡ አምስት ጉብኝቶች 145
34. የቤተ ክርስቲያን አባላቶችን ያጸኑ አምስት ጉብኝቶች 149

ክፍል ፬ - ማስተማር

35. ስኬታማ የቃሉ አስተማሪ ለመሆን የሚጠቅሙ አሥራ አምስት ቁልፎች 155
36. እያንዳንዱ መጋቢ ጉባኤውን እንደ እግዚአብሔር እርሻ ሊመለከት የሚገባበት አራት ምክንያቶች 161
37. አንድ መጋቢ ተከታታይ ትምህርት ሊያስተምር የሚገባበት ሰባት ምክንያቶች 164
38. የማስተማር አገልግትህን የሚያሳድጉ አራት ቁልፎች 166
39. የስብከት ካሴቶች ማድመጥ የስብከት አገልግሎትህን የሚለውጥበት ሰባት ምክንያቶች 168
40. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት አስተምህሮን መመስረት ይቻላል 171
41. መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰብኩ የሚገባበት ሰባት ምክንያቶች . .173
42. መሪዎችህን ማስተማር የሚገባበት ሰባት ምክንያቶች 180
43. ለምን "የውሸት ቃል" እና የሰይጣንን አስተምህሮዎች ልታስወግድ ይገባል 183

ክፍል ፭ - ጎብረት ማድረግ

44. ጎብረት ማድረግ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነበት ስምንት ምክንያቶች 189
45. ከሰዎች ጋር እንዴት ጎብረት ማድረግ እንደሚቻል 193
46. ሰዎች ልዩ የመሆን ስሜት እንዲሰማቸው ልታደርግ የምትችልበት ስምንት መንገዶች 196
47. በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል እንዴት ጎብረት ማድረግን ማበረታታት እንደሚቻል 200
48. P. V. T. I ጸ. ጉ. ማ. ጎ 203

ክፍለ ፩

እውነተኛ አገልግሎት

ምዕራፍ 1

የማመሳሰልን አገልግሎት ማስወገድ ለምን ያስፈልጋል

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ እውነተኛ አገልግሎት በመቅደስ ውስጥ ባለው ወርቅ ተመስሏል። በመቅደስ ውስጥ ያለ አስፈላጊ የሆነ እቃ ሁሉ በንፁህ ወርቅ ተሸፍኖ ነበር። ጌታ የመቅደሱን አሠራር ለሙሴ ሰጠው።

> እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፦ ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር፤ በገዛ እጁ ሊሰጠኝ በልቡ ከሚያምረው ሰው ሁሉ መባ ተቀበሉ። . . . በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ። . . .ከጥሩ ወርቅም . . . የስርየት መክደኛ ሥራ . . . የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ፤ እኔም የምሰጥህን ነገር ሁሉ፣ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል፣ በሰረየት መክደኛው ላይ ሆኜ አነጋግርሃለሁ።
>
> ዘጸአት 25፡ 1,2,8,17,21,22

እግዚአብሔር መቅደሱ እንዲመስል የፈለገው ይህን ነው። ማንም ሰው በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የራሱን ማሻሻያ የማምጣት መብት የለውም። ንጉሥ ሰለሞን መቅደሱን ሲገነባ፣ የእግዚአብሔርን እቅድ ቃል በቃል ተከትሏል።

> የቅድስተ ቅዱሳንም ርዝመት ሀያ ክንድ፥ ስፋቱም ሀያ ክንድ፥ ቁመቱም ሀያ ክንድ ነበረ በጥሩ **ወርቅም** ለበጠው። በቅድስተ ቅዱሳኑም ፊት ከዝግባ የተሠራ መሠዊያ አደረገ በጥሩ **ወርቅም** ለበጠው። ቤቱንም ሁሉ ፈጽሞ **በወርቅ** ለበጠው በቅድስተ ቅዱሳኑም

ፊት የነበረውን መሠዊያ ሁሉ **በመርቅ** ለበጠው። በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው አሥር ክንድ የሆነ ከወይራ እንጨት ሁለት ኪሩቤል ሠራ። . . . ኪሩቤልንም **በመርቅ** ለበጣቸው። የቤቱንም ወለል በውስጥና በውጭ **በመርቅ** ለበጠ።

1ኛ ነገሥት 6፡20-23፣28፣30

ሰለሞንም በእግዚአብሔር ቤት የነበረውን ዕቃ ሁሉ አሠራ፤ **የመርቁንም** መሠዊያ የገጹም ኅብስት የነበረበትን **የመርቅ** ገበታ፣ በቅድስተ ቅዱሳን ፊት አምስቱ በቀኝ አምስቱ በግራ የሚቀመጡበትንም ከጥሩ **መርቅ** የተሠሩትንም መቅረዞች፣ **የመርቁንም** አበባዎች እና ቀንዲሎች መኮስተሪያዎች፣ ከጥሩ **መርቅ** የተሠሩትን ጽዋዎችና ጉጠቶች፣ ድስቶቹንና ጭልፋዎቹንም፣ ማደጃዎቹንም፣ ለውስጠኛውም ቤት ለቅድስት ቅዱሳን ደጆች የሚሆኑትን **የመርቅ** ማጠፊያዎች አሠራ።።

1ኛ ነገሥት 7፡ 48-50

ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ሌላ ንጉሥ ወርቁን በናስ ተካ። ናስ በጣም ወርቅ ይመስላል። “የሚቀርብ እና ተመሳሳይ” ነው፣ ግን ወርቅ አይደለም። ንጉሥ ሮብዓም ናስ ወደ እግዚአብሔር ቤት አመጣ። ምናልባት እውነተኛ ነገር መስሎ ሊሆን ይችላል ግን እግዚአብሔር ደስ አልተሰኘበትም ነበር። ናስ የመዳብና የዚንክ ቅይጥ ነው። እውነታው ግን፣ ናስ ከጥሩ ወርቅ በጣም የተለየ ነው! ብዙ ሰዎች እውነተኛው ነገር በተመሳሳዩ ሲተካ ይታለላሉ። ለእዚያ ነው ይህንን መጽሐፍ የምጽፈው።

የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅም ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፣ የእግዚአብሔርንም ቤት መዛግብትና የንጉሡን ቤት መዛግብት ወሰደ ሁሉንም ወሰደ፤ ደግሞም ሰሎሞን የሠራቸውን የወርቁን ጋሻዎች ወሰደ። ንጉሡም ሮብዓም በእነርሱ ፋንታ የናስ ጋሻዎችን ሠራ፣ የንጉሡንም ቤት ደጅ በሚጠብቁ በዘበኞች አለቃ እጅ አኖራቸው።

2ኛ ዜና 12፡ 9-10

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ ወርቁን በመቅደስ ውስጥ ታኖር ዘንድ ልረዳህ እፈልጋለሁ። እውነተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎት በምንም መተካት

የለብህም፡፡ በብዙ ሙያዎች እንደሚሆነው፣ ተራ ሰዎች በእርግጥ ባለሙያው የሚያደረገውን አያውቁም፡፡ ተራ ሰዎች፣ ለምሳሌ፣ አውሮፕላን አብራሪ ወይም ዶክተር የሚያውቀውን፣ በእርግጥ አያውቁም፡፡ ማንኛውም ወደ አገልግሎት የሚገባ ሰው ሁሉ አገልግሎት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ በጣም ያስፈልገዋል!

ብዙ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ረቂቅ ለማድረግ እንደሚሞክሩ ተረድቼአለሁ፡፡ ይህን የሚያደርጉት በሙያው ገነው ለመታየት ነው፡፡ ቢሆንም ግን፣ ጌታ የመጋቢ እውነተኛ ተግባር ምን እንደሆነ እንዳስተምር አነሳሳኝ፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ የመጋቢን ዝርዝር ሥራዎች ሁሉ ምን እንደሆኑ ለመሸፈን አልሞክርም የማካፍልህ ዋነኛ የሆኑትን ነገሮች ብቻ ነው፡፡

የአገልግሎትን ቀላልነት እንድታምን ጸሎቴ ነው፡፡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ቀላል ለሆኑ እውነቶች የተወሳሰቡ አስተምህሮዎችን እንደሚመርጡ ተረድቻለሁ፡፡ መልዕክቱ ይበልጥ በተወሳሰበ ጊዜ፣ ይበልጥ ከእግዚአብሔር ሊሆን ይችላል የሚል ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ግን ታላላቅ የሆኑ እውነቶች አብዛኛውን ጊዜ ተራ ሰው ሊረዳው በሚችል መጠን ግልጽ ናቸው፡፡

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት በአገልግሎት መስቀለኛ መንገድ ላይ ደረሱ፡፡ በመስቀለኛው መንገድ ላይ፣ የትኛውን አቅጣጫ አንደሚይዙ መወሰን ነበረባቸው፡፡ **እውነተኛ አገልጋዮች ይሁኑ ወይም ሥጋዊ አስተዳዳሪዎች መወሰን ነበረባቸው፡፡ እነርሱ ግን እውነተኛ አገልግሎትን መረጡ!**

> አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፡- **የእግዚአብሔርን ቃል ትተን፣** ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም፡፡ ወንድሞች ሆይ፣ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፣ ለዚህም ጉዳይ **እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ስጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን፡፡**
>
> የሐዋርያት ሥራ 6፡ 2-4

በእውነተኛ አገልግሎትና በማመሳሰል አገልግሎት መካከል ልትለይ ይገባሃል። የማመሳሰል አገልግሎት ትክክለኛ ነገር አይደለም! እንደ ናስ፣ ወርቅን የመተካት አቅም የሌለው፣ እውነተኛውን ነገር የሚቀርብና ተመሳሳይ ነው። ብዙ እውነተኛ አገልግሎት የሚመስሉ ነገሮች አሉ ግን አይደሉም።

ለምሳሌ ያህል፣ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መሆን በአገልግሎት ዙሪያ በሥራ ሊጠምድህ ይችላል። ብዙ መጋቢዎች በእርግጥ አስተዳዳሪዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ቢሮ ውስጥና አካባቢ በሥራ ተወጥረው ይታያሉ። በልቦናቸው፣ ለእግዚአብሔር እየሠሩ እንደሆነ ይሰማቸዋል። ቢሆንም ግን፣ ዓለም ሁሉ ቢሮ ውስጥ እና ከኮምፒውተሮች ጀርባ ነው ያለው። ሰዎች በየቀኑ ከጠዋት ሦስት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ያላቸው ይመስላቸዋል። እንደ ጸሐፊ፣ ጥበቃ፣ ኮምፒውተር ፕሮግራመሮች ወዘተ ወደ እዚያ ይሄዳሉ። መጋቢው ተመሳሳይ ነገር ሲሠራ ካልታየ ሠራተኛ እንዳልሆነ ይሰማዋል። ሰዎች ማለዳ አምስት ሰዓት ላይ ቤቱ ይደውሉልኛል። ተኝቼ እንደሆን ይጠይቃሉ። መጋቢ ሣምንቱን በሙሉ የሚተኛ ይመስላቸዋል።

ውድ የወንጌል አገልጋዮች በሰዎች ግምት አትወሰዱ። ለዓለማዊ ግፊቶች አትሸነፉ። ይህን ዓለም የሚገዛውና የሚመራው የአየሩ መንፈስ አለቃ ነው። በእዚህ ዓለም ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ በመንፈሳዊው ዓለም ቁጥጥር ስር ነው። ሰይጣን ብልህና ዓለሙን ሁሉ የሚያስት ፍጡር ነው። ግን ይህ ማሳት ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊመጣ አይገባም።

> . . . በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፣ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። ኤፌሶን 2፡2

ዓለም ከሞት በኋላ ሕይወት የለም ብሎ በማሰብ ስቷል። "ነገ ትሞታለህና ብላ፣ ጠጣ እና ተደሰት! ስትሞት እንደ ውሻ ነው የምትሞተው! መንግሥተ

ሰማይም፣ ሲያልም በምድር ላይ ነው! ሕይወት አንተ እንዳደረግሽው ነው!" እነኚህ ጮሌ መፈክሮች ብዙ ሕዝብ ሕይወቱን ገንዘብና ደስታን በማሳደድ እንዲኖር ተዕዕኖ አሳድሮበታል።

እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ሰዎች ዓለማዊ (መንፈሳዊ ያልሆኑ) ነገሮች ይበልጥ አስፈላጊ ናቸው ብለው ያስባሉ። መጋቢዎች እንኳ ኮምፒውተር እንዲገዙና በቢሮ ውስጥ እንደ ሌላው ሰው እንዲቀመጡ ግፊት አድሮባቸዋል። እኛ ግን "እንደሌላው" አይደለንም! እኛ የእግዚአብሔር መንጋ እረኞች ነን! እረኞች ከበጎች ጋር ከሚኖሩ "ቆሻሻ" ሰዎች ናቸው። እረኞች ሕይወታቸውን ለበጎቻቸው የሚሰጡ ሰዎች ናቸው። እረኛ የሚመች ወንበር ላይ የሚቀመጥ ባለሥልጣን አይደለም!

ሥራህ ጸሎት እንደሆነ ስታውጅ፣ ወዲያውኑ እንደ እንግዳ ነገር ልትታይ ትችላለህ! የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ቤተ ክርስቲያን "ፍሬያለው" ነገር በመሥራት ጊዜዋን ልትጠቀም ይገባታል የማለት ድፍረት ይኖራቸው ይሆናል። እርግጥ ነው! ከጸሎት በላይ ምን ፍሬያማ ነገር አለ? ለምን የማያምኑ ሰዎች ሥራችንን እንዴት መሥራት እንደሚገባን ሲነግሩን እንሰማለን? ለምን አምላክ የለሽ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ስለ ኃላፊነቷ ያስተምሯታል?

ብዙ አገልጋዮች ታላቁን ተልዕኮ ወደ ጎን ስለተዉት ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ግፊት ውስጥ ትገኛለች። ታላቁ ተልዕኮ ከቤተ ክርስቲያን ራስ የተሰጠ ዋነኛው መመሪያ ነው።

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።
>
> **ማቴዎስ 28፡19-20**

ለራስህ አንብበው! በግልጽ ተቀምጧል! ስለ ማሕበራዊ፣ ጤና እና ስለ ትምህርት ሥራዎች የተጠቀሰ ነገር የለም። ጤና እና ትምህርት ምናልባት ከታላቁ ተልዕኮ በኋላ ሊመጣ የሚችል ጉዳይ ሊሆን ይችላል ግን ዋናው ጉዳይ ሊሆን አይችልም!

ዛሬ፣ አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ክፍል ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፣ የእርዳታ ድርጅትና ማሕበራዊ ክበብ ሆኗል። ይህ የሚያሳዝን ነው! ዓለማዊ የጤና እና የትምህርት ተቋማት የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ሥራቸውን ወደ ጎን አይተውም! የወንጌል አገልጋዮች ወደ ፖለቲከኝነት፣ ማሕበራዊ አገልግሎት ሠራተኝነትና ጤና ባለሙያነት ሲለወጡ ሰይጣን ፈገግ ብሎ ያበረታታቸዋል። የአገልግሎት ወርቅ በናስ ተለውጧል!

ይህ ሁኔታ ወደ ተራው ክርስቲያንም ዘልቋል። አንድ ቀን፣ ወጣት ተማሪ ከዩኒቨርስቲው ሪፖርት ይዞልኝ መጣ። እንዲህ አለ "መጋቢ፣ እግዚአብሔር በዩኒቨርስቲው ውስጥ እየሠራ ነው!" እኔም፣ "በእውነት ምን እየሆነ ነው?" ብዬ ጠየቅሁት እርሱም፣ "እግዚአብሔር እየሠራ ነው!" ሲል መለሠልኝ። እኔም፣ "እንዴት ነው እግዚአብሔር እየተንቀሳቀሰ ያለው ምን እያደረገ ነው?" ብዬ ጠየቅሁት። እንዲህ አለኝ፣ "ሰዎች ፈተናዎችን እያለፉ ነው!" ተደነቅሁ ፈተናዎች? ምንም እንኳ ድምፄን አውጥቼ ባልለውም ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብሁ፣ "እግዚአብሔር ሲንቀሳቀስ፣ ሰዎች ይድኑና በመንፈስ ይሞላሉ።"

ፈተናዎችን ማለፍ ከእግዚአብሔር የሆነ በረከት ነው ግን የእግዚአብሔር መንቀሳቀስ አይደለም። ስለ እግዚአብሔር ሥራ ግራ አንጋባ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አገልግሎት የሚያስተምረንን እንረዳ። ናሱን ከወርቅ ጋር አናሳስት። ወደ መቅደሱ ወርቅ ብቻ በማምጣት የሮብዓምን ፍርድ እናስወግድ።

ይህን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ መጋቢዎች እረኞች እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን መሥራት እንደሚገባቸው ትረዱ ዘንድ ጸሎቴ ነው። "ከማመሳሰል አገልግሎት" የመለያ ጊዜ አሁን ነው። እውነተኛ በሚመስል ግን

እውነተኛ ባልሆነ ነገር የጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት ልናፋጥን አንችልም።

ሦስት ምክንያቶች

በማጠቃለያም፣ የማመሳሰልን አግልግሎት ልናስወግድ የሚገባን ሦስት ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፡-

1. ወንጌልን የመሰበክና ደቀ መዛሙርትን የማፍራት አደራ የተጣለባት ብቸኛ ድርጅት(ተቋም) ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት። የእኛን ሥራ ማንም አይሠራልንም!

2. ዓለም እንድንሠራ የምትፈልገውን ነገር በመሥራት የዓለምን ትኩረት ለመሳብ መሞከር የለብንም። የጠራን እግዚአብሔር ነውና ደስ ልናሰኘው የሚገባን እርሱን ነው።

3. ሰይጣንን እና ሠራዊቱን ድል መንሳት የምንችለው በእውነተኛ አገልግሎት ብቻ ነው! የተመሳሰለ አገልግሎት በታላቁ የመጨረሻ ዘመን ጦርነት ስፍራ የለውም።

አንተ እና እኔ በእግዚአብሔር የተሰጠ መጋቢነት ትሁት ተግባሮችን እንድናስታውስ የሚረዳን ትንሽ የምስጢር ጽሑፍ(ኮድ) አለኝ። እርሱም እንደሚከተለው ነው፡- P(Prayer) (ጸ)ጸሎት V(Visitation) ጉ(ጉብኝት) T(Teaching) ማ(ማስተማር) I(Interaction) መ(መቀራረብ) (P.V.T.I) (ጸ.ጉ.ማ.መ)

ምዕራፍ 2

በአገልግሎት የላቀ መሆን እንዴት እንደሚቻል

በአገልግሎት ከፍተኛ ችሎታ ማግኘት ትችላለህ! አገልግሎትህ ተራ መሆን የለበትም። ቢሆንም፣ ከፍተኛ ችሎታ ልታገኝ የሚገባህ፣ በእግዚአብሔር ደረጃ (Standards) እንጂ በሰው ደረጃ (Standards) መሆን የለበትም በእዚህ አጭር ምዕራፍ ውስጥ፣ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ከፍተኛ ችሎታን ያስገኙ አራት ቁልፎች ላሳይህ እፈልጋለሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁላችንም ታላቅ ምሳሌ ነው። እርሱ ለእኛ የተሰጠው እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ማየት እንድንችል ነው። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ከሁሉም ይበልጥ ልንከተለው የሚገባ ምሳሌ አለን።

> እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፣ . . .
>
> ዕብራውያን 1፡3

ይህን አስታውስ! ምን ማድረግ እንደሚገባህ ማወቅ ሲያቅትህ፣ ኢየሱስ ያደረገውን አድርግ። ኢየሱስ መልካም እረኛ ነው(ዮሐንስ 10፡11)። ፈፅሞ ሊኖርህ የሚችል ከሁሉ የላቀ የመጋቢ ምሳሌ እርሱ ነው። መልካም መጋቢ ነህ? አገልግሎትህን ያጸደቀልህ ማን ነው? እግዚአብሔር ወይስ ሰው? ኢየሱስ "መልካም አደረግህ መልካምና ታማኝ ባሪያ" ይልህ ይሆን?

ኢየሱስ የልቀት አርዓያ

ኢየሱስ የከፍተኛ ችሎታ ምሳሌ ስለሆነ፣ ለአገልግሎት ምሪት ኢየሱስን እንመልከት፡፡ የመልካም እረኛ አገልግሎትን አራት ዋነኛ ክፍሎች እንድትመለከት እፈልጋለሁ፡- ጸሎት፣ ጉብኝት፣ ማስተማር እና ሕብረት ማድረግ (መቀራረብ) (P.V.T.I)፡፡ እነኚህን አራት የኢየሱስ አገልግሎት ገጽታዎች በጥሩ ሁኔታ መረዳት የመጋቢነት አገልግሎትህን ይለውጣል፡፡

1. ጸሎት

ማለዳም ገና ጎሕ ሳይቀድ፣ ኢየሱስ ተነሥቶ ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራም ሄዶ ይጸልይ ጀመር፡፡

ማርቆስ 1፡35
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

2. ጉብኝት

ወዲያው ከምኩራብ እንደ ወጡ፣ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና ወደ እንድርያስ ቤት ገቡ፡፡

ማርቆስ 1፡29-30
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

3. ማስተማር

እርሱም፣ “ከዚህ ተነሥተን በአቅራቢያ ወዳሉት መንደሮች እንሂድ፤ እዚያም **ልስበክ**፣ የመጣሁት ለዚሁ ነውና” አላቸው፡፡ ስለዚህ ወደ ምኩራባቸው እየገባ **በመስበክና** አጋንንትን በማስወጣት በመላዋ ገሊላ ይዘዋወር ጀመር፡፡

ማርቆስ 1፡ 38-39
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

4. ሕብረት ማድረግ

ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ፣ ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ
ዓሣ አጥማጆች ስለ ነበሩ፣ መረብ ወደ ባሕር ሲጥሉ **አዩአቸው**። ኢየሱስም፣ “ተከተሉኝ፤ ሰው አጥማጆች አደርጋችኋለሁ” አላቸው።

ማርቆስ 1፡16-17
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

እነኚህ ጥቅሶች ኢየሱስ የጸሎት፣ የስብከት፣ የጉብኝት እና ከሰዎች ጋር ሕብረት የሚያደርግ ሰው እንደነበር ያሳዩናል።

ክፍል ፪

ጸሎት

ምዕራፍ 3

አገልጋይ ሁሉ መጸለይ የሚገባበት አሥር ምክንያቶች

ጸሎት የእውነተኛ አገልግሎት ሁሉ መሠረት ነው። ጸሎት በእርግጥ አገልግሎት ነው። ይህን የተገነዘበ ማንኛውም ሰው ታላቅና ፍሬያማ አገልግሎት ይኖረዋል። ማንኛውም አገልጋይ እንዲጸልይ ግድ የሚሉት አሥር ምክንያቶች ልስጥህ።

አሥር ምክንያቶች

1. ጸሎት የትልቅ እምነት መገለጫ ስለሆነ ጸልይ

ጸሎት የታላቅ እምነት መገለጫ ስለሆነ ጸልይ። እንዲህ ብዬ በፍፁም አላስብም ነበር! ሁልጊዜ ጸሎትን ከእምነት ልምምድ የተለየ እንደሆነ አድርጌ አስብ ነበር። አሁን ግን ጸሎት እምነትን የሚያሳይና እምነትን እንደሚጨምር ተረድቼአለሁ። ለዚህ ምክንያት ቀላል ነው፦ በምትጸልይበት ጊዜ ሁሉ፣ በሥጋ ክንድ እምነት እንደሌለህ እየገለጽህ ነው። ጸሎት በምትጀምርበት ጊዜ ሁሉ፣ "ልታደርጋቸው" የሚያስፈልጉህ አንድ ሺ ዓይነት ነገሮች ወደ አእምሮህ እንደሚመጡ አስተውለሀል?

የሆነ ነገር ስልክ እንድትደውል ይነግርሃል። የሆነ ነገር 'ተነስተህ ሂድ' ይልሃል። የሆነ ነገር ስብሰባ ብታዘጋጅ ስኬታማ እንደምትሆን ይነግርሃል። ለመጸለይ ስትወስን፣ ልታደርጋቸው ከሚገቡ ነገሮች ሁሉ በላይ ጸሎት የበለጠ

ውጤት አለው እያልክ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ለአገልግሎትህ የእግዚአብሔር ጣልቃ መግባት በጣም አስፈላጊ ነው ማለትህ ነው፡፡ ያ በእግዚአብሔር ክንድ መታመን ነው፡፡

> ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፣ እንዲህ ሲል፡- በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበር፡፡ በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፣ ወደ እርሱም እየመጣች፡- ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር፡፡ አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ፡- ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፣ ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜ እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ፡፡ ጌታም አለ፡- ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ፡፡ እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮሁ ለሚታገስላቸውም ምርጦቹ አይታገሳቸውምን? እላችኋለሁ፣ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?
>
> ሉቃስ 18፡1-8

ከዚህ ትልቅ የጸሎት ትምህርት በኋላ፣ ኢየሱስ በጣም አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ ጠየቀ፡፡ በምድር እምነትን አገኝ ይሆንን? የጠየቀው “በምድር ላይ የሚጸልዩ ሰዎች አገኝ ይሆንን?” ብሎ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ኢየሱስ የተደነቀው ይህን የእምነት መገለጫ(ጸሎት) ወደ ምድር ስመለስ አገኝ ይሆን? በማለት ነው፡፡

ጸሎት የእምነት መገለጫ ነው

ታላቅ የእምነት ሰው መሆን ትፈልጋለህ? የእምነት ሰው የታላላቅ ድንቆች ሰው ነው፡፡ የጸሎት ሰው በመሆን ታላቅ የእምነት ሰው ሁን፡፡ ጸሎት በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ከምንገልጽባቸው ታላላቅ ነገሮች አንዱ ነው፡፡

> ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡
>
> ዕብራውያን 11፡6

ከዚህ ጥቅስ ማየት እንደምትችለው፣ እግዚአብሔርን ያለ እምነት ደስ ልታሰኝ አትችልም፡፡ ያ ማለት በአገልግሎት ውስጥ ያለ ጸሎት እግዚአብሔርን ደስ

ልታሰኝ አትችልም ማለት ነው። እግዚአብሔርን አስተዳዳሪ፣ የሂሣብ ሹም ወይም የኮምፒዩተር ጠበብት በመሆን ልታስደስተው አትችልም። እግዚአብሔርን ደስ የምታሰኘው በጸሎትና በእርሱ ያለህን እምነት በማሳየት ነው።

2. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት ሥልጣን ያለው ሰው ያደርግሃል

> ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፤ እንደ ጻፎቻቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና።

ማቴዎስ 7፡28-29

ኢየሱስ ሥልጣን ያለው ሰው እንደ ነበረ ታስታውሳለህ። ሥልጣን እንዲህ ተብሎ ሊብራራ ይችላል፣ "በቀላሉ ሊገለፅ የማይችል፣ የማይታይ፣ የእግዚአብሔርን ሰው የከበበ ኃይል።" ሥልጣን የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ መጠጋጋት(ህብረት) ነው። ከአንድ ሰው በተጠጋህ መጠን፣ ስለዚያ ሰው በይበልጥ በሥልጣን መናገር ትችላለህ። ስለ እርሱም በይበልጥ በመተማመን መናገር ትችላለህ።

ለምሳሌ፣ ታላቅ የሆነ ሰው ሲሞት፣ ሞቱ በቶሎ ላይገለጥ ይችላል። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ፣ ከናይጄሪያ መሪዎች አንዱ የነበሩት፣ ጄኔራል አጉዬ ኢሮኒስ፣ ጁላይ 28 1966 እ.ኤ.አ ተገደሉ፣ ግን እስከ ጃኑዋሪ 14, 1967 አልተገለጠም ነበር። የሆነ የቅርብ ቤተሰብ ብትሆን ኖሮ ስለ መኖራቸውና ስለ መሞታቸው በሥልጣን መናገር ትችላለህ። ሰውየው ሞቷል ብትል፣ ከቅርበትህ የተነሳ ሰዎች ያምኑሃል። **በቀረብክ መጠን፣ የበለጠ ሥልጣን አለህ።**

ይበልጥ በጸለይህ መጠን ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር ትጠጋለህ። ወደ እግዚአብሔር የተጠጋህ ከሆንህ በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ የበለጠ ሥልጣን አለህ ማለት ነው። በጸለይህ ጊዜ ሁሉ የማይታይ የሚስብ ኃይል በዙሪያህ ይከማቻል። ለምን ሰዎች እንደሚከተሉህ ሳይገባህ እንኳ ተከታዮች

ይኖሩሃል! ለምን እንደሆነ መግለፅ ባትችል እንኳ ተከታዮች ይኖርሃል! ትምህርትህ ይበልጥ ኃይል ይኖረዋል! መመሪያዎችህ ተቀባይነት ይኖራቸዋል! እነኚህ ሁሉ የሥልጣን ሰው የሚያደርጉህ የአገልግሎት ጸሎት ውጤቶች ናቸው።

ኢየሱስ እንዴት የሥልጣን ሰው ሆነ

ኢየሱስ ለዚህ ዓለም በማንም አልተዋወቀም። በመምህርነትም በማንም አልተሾመም። ይልቁን፣ ማንነቱ አጠያያቂና ብዙዎችም በወላጆቹ ማንነት ላይ ጥያቄ ነበረባቸው። ኢየሱስ ግን በሰው ዘንድ ሥልጣን ያለው ስለመሆን ምስጢር የሚያውቅ ነበር። ወደ ምድረ በዳ በመሄድም እግዚአብሔርን ጠበቀ።

> ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ ስለ እርሱም በዙሪያው ባለችው አገር ሁሉ ዝና ወጣ።

ሉቃስ 4፡14

"ኃይል" የሚለው ቃል **ዱናሚስ** (Dunamis) ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። ዱናሚስ (Dunamis) ማለት *ታዕምራታዊ ኃይል፣ ችሎታ፣ መትረፍረፍ፣ ጥንካሬ፣ ብርታት፣ ኃይለኛ አሰደናቂ ሥራ እና የሚያስችል ኃይል ማለት ነው።* ኢየሱስ የሥልጣን ሰው ሆኖ መጣ! አዲስ ብርታት ነበረው፣ መትረፍረፍና ኃይል ነበረው። ይህ በኢየሱስ ዙሪያ የነበረ አዲስ፣ የማይታይና የሚስብ ኃይል ከጸሎት የመነጨ ነበር። የመጀመሪያው የናዝሬት ስብከቱ ምላሽ አስደናቂ ነበር ::

> ሁሉም ይመሠክሩለት ነበር፣ ከአፉም ከሚወጣው ከጸጋው ቃል የተነሣ እየተደነቁ . . .

ሉቃስ 4፡22

ኢየሱስ በቅፍርናሆም የዚያኑ ያህል ውጤት አግኝቶ ነበር። ሰዎች በስብከቱና በአገልግሎቱ በቀላሉ ተደንቀው ነበር።

> ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ። በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤ ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ።

ሉቃስ 4፡31-32

ይህ ሥልጣንና ስኬት ከየት የመጣ ይመስልሃል? ይህ ሁሉ ሕዝብ ከየት መጣ? ለምን ሰዎች ይህን የሠላሳ ዓመት ሰው በድንገት ማድመጥ ያዙ? ይህንን ነው "በቀላሉ ሊብራራ የማይችል፣ የማይታይ፣ የጸሎት ሰዎችን የሚከብ የሚስብ ኃይል ብዬ የምጠራው።" ምናልባት በአገልግሎት ውስጥ የሚያስተዋውቅህ ማንም ሰው የለህ ይሆናል። እንደ ኢየሱስ የሥልጣን ሰው እና እውቅናን የምታገኝ ሰው ልትሆን ትችላለህ።

3. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት የተቀባ ሰው ያደርግሃል

ወደ አንድ ሰው የተጠጋህ ከሆንህ፣ የሆነ ነገር በንክኪ ይተላለፍብሃል። ጊዜህን በጸሎት በምታሳልፍበት ጊዜ ሁሉ፣ ጊዜህን ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር እያሳለፍህ ነው። ከአንድ ሰው ጋር ይበልጥ በተነጋገርህ ጊዜ፣ ከዚያ ሰው ጋር ይበልጥ ትቀራረባለህ። ከአንድ ሰው ጋር በተጠጋህ፣ መጠን ብዙ ነገሮች በንክኪ ወደ አንተ ይተላለፋሉ። የእግዚአብሔር ክብር በአንተ ላይ እንዲሆን ትወዳለህ? በሕይወትህ ላይ ቅባቱ እንዲኖ ትፈልጋለህ?

ቀላል መንገድ ብሰጥህ ደስ ባለኝ ነበር፤ ግን ወደ እግዚአብሔር የሚያስጠጋህ ጸሎት ብቻ ነው።

የሙሴ ምሳሌ ይህን ነው የሚያሳየው። ሙሴ ወደ ተራራው በመሄድ በጌታ መገኘት ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቆየ።

> ሙሴም ወደ ደመናው ውስጥ ገባ ወደ ተራራውም ወጣ፤ ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀን አርባ ሌሊትም ቆየ። ዘጸአት 24፣18

ሙሴ ከጌታ ጋር ብዙ ሰዓቶች ያሳለፈ ሰው እንደነበር ታስተውላለህ። በተራራውም ላይ ብዙ በመቆየቱ፣ የጌታ ክብር በእርሱ ላይ መታየቱ ማረጋገጫ ነበር። ውድ መጋቢ፣ ከጌታ ጋር ሰዓታትን ስታሳልፍ ለአንተም የሚሆነው ይኸው ነው፤ በሕይወትህና በአገልግሎትህ ላይ የጌታ ክብር ይገለጣል።

ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ **ክብር የሙሴን ፊት** ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ፣ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፣

2ኛ ቆሮንቶስ 3፡7

4. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት በአገልግሎትህ ውስጥ ያለውን የአጋንንት ሥራ ያስራል

ውድ መጋቢ፣ ቤተ ክርስቲያን ዓለማዊ ድርጅት አይደለችም። ሰይጣንን በተለያዩ አስፈላጊ ምክንያቶች ልታስረው ይገባሃል።

ሀ. በመሪዎች መካከል መለያየትን እና ታማኝ አለመሆንን የሚያመጣውን የሰይጣን ሥራ ማሰር ይገባሃል።

ለ. በአባላቶች ሕይወት ውስጥ ማፈግፈግ፣ ምግባረ ብልሹነት እና ኃጢዓት እንዲያደርጉ የሚያደርገውን ተፅዕኖ ማሰር ይገባሃል።

ሐ. አባላቶችህን እንዲጎሳቁሉ፣ ተስፋ እንዲቆርጡ እና እንዲጨነቁ የሚያደርጉትን አጋንንት ማሰር ይገባሃል።

መ. በቤተ ክርስቲያን ላይ ክስን እና ስም ማጥፋት የሚያስነሳውን መንፈስ ማሰር ይገባሃል።

ወደድህም ጠላህም፣ ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠቁና የሚያጠፉ አጋንንትን ይመድባል። በአገልግሎትህ ላይ የሚነሳውን የአጋንንት ሥራ (እንቅስቃሴ) የበለጠ መረዳት ትችል ዘንድ፣ *"መሪዎችና ታማኝነት"* የሚለውን መጽሐፌን እንድታነብ እመክራለሁ።

ሰይጣንን ባታሰረው እርሱ በገዛ ቤተ ክርስቲያንህ ያሰርሃል። ማገልገል ይሳንሃል። ማንም ከአንተ አይቀበልም እናም ምን እየሆነ እንደሆነ ግራ ይገባሃል። ሰይጣን ጉባዔህን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበተነ ይሄዳል። ቤተ ክርስቲያንን ያለማቋረጥ የሚከፋፍል የወሬ፣ የክስ፣ ስም ማጥፋት እና የውይይት ውስብስብ

መረብ ይኖራል። ዛሬ ንቃ እና ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ሰይጣንን እና አጋንንቶችን እሰር።

5. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት በአገልግሎት ውስጥ አዲስ አቅጣጫን ይፈጥራል፣ ይወልዳል

በጣም አስፈላጊ የሆነው የጸሎት መገለጥ ጸሎት የመፍጠር ኃይል ያለው መሆኑ ነው። አገልግሎት የምትጀምር ከሆነ፣ ከዚህ ቀደም ያልነበረ ነገር ወደ መኖር እስኪመጣ መጸለይ ይኖርብሃል። አንድን ነገር መፍጠር፣ ያለውን ከማጽናት ይለያል። ብዙ ሰዎች የነበረውን ነገር ማጽናት ይችላሉ ግን አዲስን ነገር ለመፍጠር የጸሎት ሰው መሆንን ይጠይቃል።
ፈር ቀዳጅ ለመሆን ከተላክህ፣ የጸሎት ሰው ሁን።
የጸሎት ሰው አዲስ መንፈሳዊ አቅጣጫዎችን የሚፈጥር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የጸሎት ሰው ነበር። እንዲህ አለ፦

> **የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደ ገና ምጥ ይዘኛል፤**
>
> ገላቲያ 4፡19
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ጳውሎስ በእነኚህ ክርስቲያኖች ውስጥ ክርስቶስ እስኪቀረጽ ማማጥ ነበረበት። ጳውሎስ ይህን በሌላ መንገድ ለማድረግ አልሞከረም። **ኮሚቴ መመስረት፣ ስብሰባ ማዘጋጀት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማካሄድ እና ፍቅር ማሳየት አዲስ አቅጣጫን አይፈነጥቅም።** ለብዙ ዓመታት አዲስ ቤተ ክርስቲኖችን፣ ሕብረቶችን እና አገልግሎቶችን በመመስረት አሳልፌአለሁ። ካገኘሁት ልምድ ልመክርህ የምችለው ጥቂት ነው። የመጀመሪያው ምክሬ፣ ጸልይ ነው። ሁለተኛም ጸልይ። እና ሦስተኛውም ጸልይ ነው።

6. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት ለአገልጋይ ሁሉ የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ትዕዛዝ ነው

ሐዋርያው ጳውሎስ ለልጁ ጢሞቴዎስ ብዙ ጥሩ ምክርና ትምህርት ሰጥቶታል። ለአገልግሎት ስለሚያስፈልገው ጠቃሚ ነገር ሁሉ ተምሯል። ጳውሎስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ስለ መጋቢዎች ሥልጠና እና እንዴት አመጸኞችን መያዝ እንደሚገባው ሁሉ አስተምሮታል። ቢሆንም ግን፣ ጳውሎስ ለልጁ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን መመሪያ በደንብ ላጤነው የመጀመሪያው ትዕዛዝ እንዲጸልይ እንደሆነ ግልጽ ነው።

> እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ፤ ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር ነው። ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው፤
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፣1-3
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ይህ ጥቅስ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት ስለ መጸለይ ስታስተምር ነው። ይህ ጥቅስ ስለ መሪዎቻችን እንድንጸልይ በማስተማሩ ላይ እስማማለሁ። ነገር ግን ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በመጀመሪያ የሰጠው ዋነኛ መመሪያ መሆኑን እንድታስተውል እፈልጋለሁ። እናም ደግሞ የጸሎት መመሪያ ነበር። የመጀመሪያው ጢሞቴዎስ መልዕክት አንደኛ ምዕራፍ ለጢሞቴዎስ የተሰጠን ዋነኛ ትዕዛዝ አልያዘም። በዚህ በጣም አስፈላጊ በሆነ ደብዳቤ ውስጥ፣ ሐዋርያው ዋነኛና ተቀዳሚ ሆኖ ያገኘውና ለጢሞቴዎስ የነገረው እንዲጸልይ ነው።

አንድ አገልጋይ ብዙ ማድረግ የሚገባው ነገሮች አሉ፣ ግን ከሁሉ በፊት መጸለይ ይገባዋል!

7. ጸልይ ምክንያቱም ሐዋርያት የአስተዳደራዊ ኃላፊነት ጫና ቢበዛባቸውም መጸለይ ለማቆም አልፈቀዱም

አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም፡፡ ወንድሞች ሆይ፣ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፤ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን፡፡

የሐዋርያት ሥራ 6፡2-4

የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ስታድግ ሐዋርያት አስተዳዳሪዎች እንዲሆኑ ጫና ተደርጎባቸው ነበር፡፡

የአገልግሎት ምስጢር ይህ ነው፡- በምትጸልይበት ጊዜ ብዙ ነፍሳትን ትወልዳለህ ብዙም ፍሬ ታፈራለህ፡፡ እነኚህ አዲስ ፍሬዎች ደግሞ ከአንተ ጥበቃን እና ጊዜ ማግኘትን ይፈልጋሉ፡፡ ፍላጎታቸውም ሥራ እንዲበዛብህ ያደርጋል፡፡ እነኚህን በመርዳት ስትጠመድ ደግሞ፣ ለመጸለይ የሚኖርህ ጊዜ ያንሳል፡፡ ጥቂት ብቻ በምትጸልይበት ጊዜ ደግሞ፣ አገልግሎትህ ይዳከማል፡፡ **ስለዚህ የአንተ ዋነኛ ኃላፊነት፣ ነፍሳትን የመንከባከብ እና የጸሎት ጊዜህን ሚዛናዊ ማድረግ መቻል ነው**፡፡ እኔ ራሴን ሁል ጊዜ በዚህ ላይ ስታገል አገኘዋለሁ፡፡

ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት ትክክለኛውን ውሳኔ በመውሰድ አገልግሎታቸውን አቆዩ፡፡ ዛሬ በትረ መንግሥቱ በእጃችን ተሰጥቶናል፡፡ የእኛ ተቀዳሚ ፍላጎት ረጅም ሰዓት በጸሎት ማሳለፍ መሆን አለበት፡፡ የመማለድ ታላቅ ኃላፊነታችንን ቸል እንድንል ለሚፈልጉ ግፊቶች አንሸነፍ፡፡ ጸሎትን ቸል ካልን፣ ማን ይጸልያል?

ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ሙት በሆነው አካልና ሕያው በሆነው አካል መካከል ያለው ልዩነት ምንድር ነው? ጸሎት ነው! ሕያው የሆነው ክፍል የኢየሱስ ደም እየፈሰሰበትና ሰዎች እየዳኑ ያለበት ክፍል ነው፡፡ በሕክምና አነጋገር፣ አንድ ሰው በሕይወት አለ የሚባለው የልብ ምት ሲኖር እና ደሙ በሰውነቱ

ውስጥ ሲዘዋወር ነው። አንድ ሰው ሕያው ነው የሚባለው ዶክተር በሳንባው አየር መተንፈሱን ሲሰማም ጭምር ነው።

በመንፈሳዊ አነጋገር፣ የኢየሱስ ደም በሰውነት ውስጥ ሲፈስ እና ሰዎች ሲድኑ፣ ቤተ ክርስቲያን ሕያው ነች ማለት እንችላለን። መንፈስ ቅዱስ በአካል ውስጥ ሲነፍስም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በሕይወት አለች ማለት እንችላለን።

ነፍሳት የማይድኑባቸው ወይም ማንም ሰው በመንፈስ የማይሞላባቸው ቤተ ክርስቲያኖች አሉ። እነኚህ የቤተ ክርስቲያን ሙት አካል ናቸው። ሁሌም ቢሆን የቤተ ክርስቲያን ሙት አካል የሆኑ አሉ። ቤተ ክርስቲያንህ እንድትሞት ትፈልጋለህ? ሙት ከሚባሉ ቤተ ክርስቲያናት ልትመደብ ትፈልጋለህ? አይመስለኝም!

. . . ሥራህን አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።

ራእይ 3፣1

ሰዎች መንፈሳዊ መነቃቃት (ሪቫይቫል) ብለው የሚጠሩት አንደኛው መለያ ጸሎት ነው። ሌሊቱን ሙሉ ጸሎት እና ጩኸት የምትሰማው የት ነው? ረጅም የጸሎት ፕሮግራም የሚካሄድበት እና ሰዎች በልሳን ሲናገሩ የምትሰማው የት ነው? እንደዚህ ባሉ ስፍራዎች ሰዎች ሲድኑና አለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ታያለህ።

የጸሎትን ጉዳይ አቅለህ አትያዝ! ጸሎት የአገልግሎትህ ሕይወት ውል ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያት ጫና ውስጥ በነበሩበት ወቅት እንኳ የጸሎት አገልግሎታቸውን ያልተውት።

8. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት የክርስቶስ አገልግሎት ትልቁ ክፍል ነው።

1 መስፈሪያ ስብከት፡ 571.4 መስፈሪያ ጸሎት

አስበው፣ ኢየሱስ ለሦስት ዓመት ተኩል ሰበከ እና አስተማረ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ስለ እኛ እየማለደ ነው። የሦስት ዓመት ተኩል ትምህርት ከሁለት ሺ ዓመት ጸሎት ጋር ሲነፃፀር! ይህ ንዕዕር አንድ መስፈሪያ ስብከት አምስት መቶ ሰባ አንድ መስፈሪያ ጸሎት ይሰጠናል። ያ አስደናቂ የሆነ የንዕዕር አሀዝ ነው! **ብዙ አገልጋዮች ያሳቸው ግን ከአስር በላይ የሆነ የስብከት መስፈሪያ ስለንድ መስፈሪያ ጸሎት ነው!**

ምናልባት ኢየሱስ ወደ እኛ ያለውን አገልግሎቱን እስካሁን እንደቀጠለ አታውቅ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ እረኛችን እንደሆነና እንደሚጠነቀቅልን በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስተምረናል። ራስህን፣ አንድን ጉባኤ የሚንከባከብ መጋቢ እንደሆነና ወደ ውጭ አገር እንደምትጓዝ አድርገህ አስብ። ልብህ ጥለኸው ከሄድኸው ሕዝብ ጋር አይቀርም? ስለ እነርሱስ አትጸልይላቸውም? መልዕክተኞችንስ ወደ እነርሱ አትልክም? ለጉባኤው ለመንገዱ የሚረዳውን ስጦታ አትልክም? ኢየሱስም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው። ለእኛ መልዕክቶችን፣ ስጦታዎችን እና ባርኮቶችን እየላከልን ነው። እነኚህን የመገለጥ ጥቅሶች ልብ በል።

> ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።
>
> ዕብራውያን 7፡25
>
> . . . የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፤ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፤ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።
>
> ሮሜ 8፡34

ኢየሱስ ሕያው ነው! እርሱ ፈዕሞ ሊያድነን ይቻለዋል። በሌላ አነጋገር፣ ከማንኛውም ጽኑ እና አስጨናቂ ሁኔታ ሁሉ እያዳነን ነው። በኢየሱስ ጸሎት ምክንያት ፈጽመን እየዳንን ነው። በኢየሱስ ምልጃ ምክንያት የሕይወታችን ክፍል ሁሉ ድነት እያገኘ ነው። ኢየሱስ እንደ ጸለየ ብትጸልይ ኖሮ፣ ወደ ጌታ ያመጣሃቸው ምን ያህል ፈጽመው ይድኑ እንደ ነበር አስበው።

በአገልግሎት ውስጥ ታላቅነት በምልጃ ችሎታ ይወሰናል

በብሉይ ኪዳን እንኳ፣ ኢየሱስ አማላጅ ስለሚሆን ስለ ታላቅ አገልግሎቱ ተተንብዮአል። አማላጅነት በእውነት ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ያደርግሃል፣ እኔ የጸሎት ሰው ያልሆነ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም ማለት እችላለሁ። ዐይቱ እንዲህ ነው፡- *የጸሎት ሰው ማለት የእምነት ሰው ማለት ሲሆን ያም ደግሞ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ማለት ነው።*

> ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፤ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።

ኢሳይያስ 53፡12

በእግዚአብሔር ሠራዊት ውስጥ ከታላላቆችና ብርቱዎች ጋር ልትቆጠር ትወዳለህን? ከክርክር፣ ከጭቅጭቅና ማለቂያ ከሌለው ውይይት ፈቅ በል። ዛሬ ማላጅ ሁን።

9. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት ምርኮኞችን ነፃ ያወጣል

መንፈሳዊ ዓይኖችህ ቢገለጡ ኖሮ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምርኮኞችን በድንገት ባየህ ነበር። በምድር ላይ ላሉ ደካማ የአጋንንት ኃይሎች ምርኮኛ ናቸው።

> . . . ለታሰሩትም መፈታትን . . . እሰብክ ዘንድ፤

ሉቃስ 4፡18

በእኔ አመለካከት፣ በጠንካራ ቀንበር ስር ያሉ ሰዎች በአውሮፓ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። እንደ አገልጋይ የእኛ ኃላፊነት በዚህ ምድር ያሉ ነፍሳት ላይ ያለውን የአጋንንት ኃይል *ማዳከም* ነው። ባለን መንፈሳዊ ጦርነት ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት በወቅቱ ይሰፋ ዘንድ አጋንንታዊ ኃይሎችን ማስለቀቅ፣ ስፍራ ማሳጣት ወይም ወደ ሌላ ስፍራ እንዲሄዱ ማድረግ ይኖርብናል።

. . . ምሽግን ለመስበር ግን. . . 2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4

በጌርጌሴኖን በነበሩ እብድ ሰዎች ውስጥ የነበሩት አጋንንቶች በአካባቢው ለመቆየት ፈለጉ እናም በመጨረሻ መንገድ አገኙ። ኢየሱስ በጌርጌሴኖን አካባቢ ስፍራ እንዲቀይሩ ብቻ ነው ያደረገው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን በአካባቢው የመቆየት መብት እንዳለው ያስተምረናል። ሰይጣንን ከምድር ለማስወጣት መሞከር ምንም ጥቅም የለውም።

ሰይጣን ሙሉ በሙሉ እየተጠቀመበት ያለ የኮንትራት ጊዜ አለው። ኮንትራት እንዳለውና የመቆየት መብት እንዳለው ለኢየሱስ አሳሰበ። እርሱ ወይም ሰራዊቱ ከምድር የሚወገዱበት ጊዜ ገና እንዳልደረሰ ኢየሱስን አስታወሰው።

> . . . ኢየሱስ ሆይ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፡- ከእንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን ወደዚህ መጣህን?
>
> ማቴዎስ 8፡29

ሰይጣን ከምድር ፈጽሞ የሚወገድበት ጊዜ ይመጣል። እኛ ያንን ተግባር ልንፈጽም አይገባንም። ይህ የሚፈጸመው ከሰማይ በሚመጣ ኃይለኛ መልአክ ነው። የእኛ ድርሻ ምርኮኞች ያመልጡ ዘንድ ምሽጉን ማዳከም ነው። የሰይጣንን ምሽግ በጸሎት ማዳከም እንችላለን።

ለዚህ ነው ሰይጣን እንዲህ ያለው፡- “ጊዜው ሳይደርስ መጣህን?” ሰይጣንም ማንበብ መጻፍ እና ወደፊት የሚመጣበትን ፍርድ ጥርት አድርጎ ማየት ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከዚያ በኋላ በምድር ላይ ያሉ ሰዎችን የሚያስተበት እና የሚያጠፋበት አንዳች ኃይል አይኖረውም። ለራስህ አንብበው።

> የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፣ ሺህ ዓመትም አሰረው፣ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ መጎተም አደረገበት ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።
>
> ራእይ 20፡1-3

ከአንድ ሺህ ዓመት በኋላ

. . . ያስታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፣ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሠቃያሉ።

ራእይ 20፡10

ለአሁን፣ ማድረግ የምንችለው ብቸኛ ነገር የሰዎችን ነፍስ ጨምድዶ የያዘውን የሰይጣንን ኃይል ማዳከም ነው። ይህ የመያዝ ኃይሉ ሲዳከም፣ ምርኮኞች በነፃነት ይሄዳሉ። በምትጸልይበት ጊዜ፣ ሰይጣን የማያምኑ ሰዎችን የመያዝ ኃይሉ ይዳከማል። የእኛ ትልቁ መሣሪያችን ጸሎት ነው። ለዚያ ነው ጸሎት በማይኖርበት ጊዜ ምንም ነገር የማይፈጠረው። ለዚያም ነው ሰዎች ሲጸልዩ ብዙ ነገር የሚሆነው! ለዚያ ነው ከጸሎት ሊከለክልህ የሚቻለውን ሁሉ የሚያደርገው።

የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፣ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤

2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4

ሰይጣን ተፈጥሮአዊ የሆነ ምንም መሣሪያ አንደሌለን ስለሚያውቅ፣ በተቻለው መጠን ሁሉ ገሀድ በሆነው ተፈጥሮ እንድንቀሳቀስ ሊያደርገን ይሞክራል። በገሃዱ ዓለም ላይ ብቻ በዋነኝነት መንቀሳቀስ እንዴት ያለ ስህተት ነው። ባልታጠቅንበትና "የጦር ዕቃ አልባ" በሆንህበት ዓለም መንቀሳቀስ ትልቅ ስህተት ነው! ጌታ ዓይኖችህን አብርቶ ይህን የጸሎት መገለጥ እንድትረዳ ያድርግህ!

10. ጸልይ ምክንያቱም ጸሎት እጅግ ታላቅ ነገርን ያደርጋል

ስለዚህ ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ። የጻድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው፤ ታላቅ ነገርም ያደርጋል

ያዕቆብ 5፡16

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

መጽሐፍ ቅዱስ ጸሎት ታላቅ ውጤት እንዳለው ያስተምራል። በአጠቃላይ ክርስቲያን ሁሉ ይህን እውቅ ጥቅስ ያውቃል ማለት ይቻላል። “ታላቅን ነገር ያደርጋል” የሚለው አባባል ለብዙዎቻችን ብዙም ግልጽ አይደለም። የዚህን አገላለጽ አሥር የተለያዩ ፍችዎች እነሆ፡-
ታላቅን ነገር ያደርጋል ማለት፣

1. መሳካት
2. ማየል
3. ማሸነፍ
4. አንድን ነገር ማድረግ መቻል
5. በተቃራኒ ኃይል ላይ መበርታት
6. ለመረዳት የተዘጋጀ
7. ተጽዕኖ ማሳደር
8. ስሜት መፍጠር
9. ውጤታማ መሆን
10. ብዙ መሥራት

በተጨማሪ የዚህ ጥቅስ (ያዕቆብ 5፡16) የተለያዩ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች ደግሞ ደስ ያሰኙናል

> በመልካም ሰው ቅን ጸሎት ከፍተኛ ኃይል ይገኛል
>
> ያዕቆብ 5፡16 (Philips translation)

> የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይለኛ ውጤት ያመጣል
>
> ያዕቆብ 5፡ 16 (Olaf M Norlie)

> የጻድቅ ሰው ጸሎት፡- በሥራውም ፈጣን የሆነ፣ ከፍተኛ ኃይል እንዲኖ ያደርጋል
>
> ያዕቆብ 5፡ 16 (Amplified translation)

> የትክክለኛ ሰው ጸሎት፣ በሥራ ላይ ሲውል በጣም ኃይለኛ ነው
>
> ያዕቆብ 5፡16 (Williams translation)

ምዕራፍ 4

አሥራ ስምንት የመንፈሳዊ ውጊያ እውነቶች

መንፈሳዊ ውጊያ በምድር ላይ ከመንፈሳዊ ኃይሎች ጋር የመዋጊያ ስልት ነው። እነኚህ ኃይሎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ነፍሳትን ይዘዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል፣ ሰይጣን ዓለምን ሁሉ አስቷል። ምናልባት አሁን ፈጽመን ልናስወግደው አንችል ይሆናል፣ ግን በእርግጥ በጸሎታችን በብዙዎች ላይ ያለውን ይዞታ ልናዳክም እንችላለን። አንድ ቀን ፈጽሞ ዋጋውን እንደሚያገኝ እናውቃለን።

> የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፤ ሺህ ዓመትም አሰረው፣ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።
>
> ራእይ 20፣1-3፣

> . . . ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፣ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሠቃያሉ።
>
> ራእይ 20፣10

አሁን በምድር ላይ ከአጋንንት መንጋዎች ጋር ስላለብን ጦርነት ማወቅ የሚገባንን አስራ ስምንት እውነታዎች ላካፍልህ።

1. ቀንደኛ ጠላታችን ሰይጣን እንጂ ሌሎች የሰው ልጆች አይደሉም

ሰይጣን በዚህ ምድር ላይ ያሉ የአጋንንት ጭፍራ ኃይል መሪ ነው። ሰይጣን ከከበረ ስፍራ የወደቀ ኃይለኛ ፍጡር ነው።

> አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፣ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ! አንተም በልብህ፦ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፣ በልዑልም እመሰሳለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ። የሚያዩህ ይመለከቱሃልና፦ በውኑ ምድርን ያንቀጠቀጠ፤ መንግሥታትንም ያናወጠ፤ ዓለሙን ባድማ ያደረገ፤ ከተሞችንም ያፈረሰ፤ ምርኮኞቹንም ወደ ቤታቸው ያልሰደደ ሰው ይህ ነውን? ብለው ያስተውሉሃል። የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ በየቤታቸው በክብር አንቀላፍተዋል። አንተ ግን እንደ ተጣለ ቅርንጫፍ ከመቃብርህ ተጥለሃል፤ በሰይፍም የተወጉት፣ ተገድለውም ወደ ጕድጓድ ድንጋዮች የወረዱት ከድነውሃል፤ እንደ ተረገጠም ሬሳ ሆነሃል።
>
> ኢሳያስ 14፡12- 19

2. ብልህ የሆነው ፍጡር የሆነው ሰይጣን፣ ሌላ ምርጫ ስለ ሌለው ወደ ማሳት፤ ማጭበርበር እና ከእውነት ወደ ራቀ የውጊያ ስልት ገብቷል

ሰይጣን፤ ቀንደኛው ጠላታችን፤ የቤተ ክርስቲያንን ኃይል ሊቋቋም እንደማይችል ያውቃል።

> የዲያብሎስን **ሽንገላ** ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቅ ጦር ሁሉ ልበሱ።
>
> ኤፌሶን 6፡ 11

3. ጠላታችንን ማሸነፍ ይቻለን ዘንድ፣ ስለ ጠላታችን ለማወቅ የሚቻለንን ሁሉ ልናውቅ ይገባናል

ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነ የጦርነት ሕግ ነው። ለዚህ ነው ምድራዊ የጦር ኃይሎች በቅኝትና በስለላ ሥራ ላይ የሚሰማሩት። ያለዚህ እውቀት በቀላሉ ትሸነፋለህ። የአሜሪካን ሠራዊት በቬትናም ምን እንደ ደረሰበት ጠይቅ!

4. ሰይጣን ወደ ተከታዮቹ የሚተላለፍ የወረርሽኝ ተፈጥሮ/ባህሪ አለው

የሰይጣን ሃያ ስሞች እና ማዕረጎች በመመርመር ስለ ጠላታችን ብዙ መረጃ መልቀም ይቻላል። ጠላትህን ታሸንፈው ዘንድ እወቀው።

5. ሰይጣን በምድር ላይ የመኖር መብት አለው

ሰይጣን ለኢየሱስ ይህን ነግሮታል። መንግሥታትን ለኢየሱስ አሳይቶ እሰጥሃለሁ ብሎታል። ኢየሱስ ሰይጣንን እየዋሸህ ነው አላለውም። ኢየሱስ ሰይጣን መንግሥታትን የመስጠት ኃይል እንደነበረው ያውቅ ነበር። በዚህ ላይ አልተከራከረውም። እንዲያ ባይሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ ባልተፈተነ ነበር።

> ዲያብሎስም፦ ይህ ሥልጣን ሁሉ . . . ለአንተ እሰጥሃለሁ፤
>
> ሉቃስ 4፡6

6. ሰይጣን በምድር ላይ ሊዝ እንዳለው ያውቃል

ይህ ሊዝ በቅርቡ ያበቃለታል ደግሞ ሰይጣን ይህንኑ ያውቃል። በመንፈሳዊው ውጊያ ጠላታችን ሰይጣን ነው። ሰይጣን ሊዙ የሚያበቃበትን ጊዜ ጠንቅቆ ያውቃል።

> እነሆም፦ ኢየሱስ ሆይ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፤ ከአንተ ጋር ምን አለን? **ጊዜው ሳይደርስ** ልታሠቃየን ወደዚህ መጣህን? እያሉ ጮኹ።
>
> ማቴዎስ 8፡29

7. ሰይጣንን እና አጋንንቱን ከምድር የማስወገድ ኃላፊነት የእኛ አይደለም

ኢየሱስ እንኳ ያንን ለማድረግ አልሞከረም! ሊዝ ጊዜ ሳያልቅ ተከራይን ከቤትህ ለማስወጣት አትሞክርም። በችሎት እንደሚፋረድህ ታውቃለህ። እንደ አገልጋይ የእኛ ኃላፊነት በዚህ ምድር ላይ ነፍሳትን የያዘውን የአጋንንት ኃይል ማዳከም ነው።። የመንፈሳዊ ውጊያችን ብቃት የአጋንንትን ኃይል ይዞታ ማስለቀቅ፣ ስፍራ ማሳጣት ወይም ወደ ሌላ ስፍራ እንዲሄዱ በማድረግ በጊዜው የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰፋ ማድረግ ነው።

. . . ምሽግን ለመስበር

2ኛ ቆሮንቶስ 10፡4

8. ሰይጣን በጣም ክፉ የሆነ ተከራይ ነው

ተከራይ ማለት አንድን ንብረት በኮንትራት የሚይዝ ነው። ሰይጣን ለጊዜው የዚህ ዓለም አምላክ ነው። በዚህም ምክንያት ዓለም ሁሉ በሰይጣን ክፉ ክንድ ስር እንደወደቀ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን **ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ** እናውቃለን፤፤

1ኛ ዮሐንስ 5፡19

ሰይጣን የተከራየው ንብረት በክፉ ገዥ ስር እየተንቀጠቀጠ ነው። አንድ ቀን ኃይል ሁሉ ለዘለዓለም ይሰበራል።

9. ምንም እንኳ ዲያብሎስን ፈጽመን ማስወገድ ባንችልም፣ በተለያዩ የጦርነት ዓይነቶች ልንጠምደው እንችላለን

ልንታገለው እንችላለን (ኤፌሶን 6፡12)። ከሰዎች ውስጥ *ልናስወጣው* እንችላለን (ማርቆስ 5፡13)። *ልናስረው* እንችላለን (ማቴዎስ 18፡18)። ምሽጉን *ልናፈርሰና*

ልናዳክመው እንችላለን (2ኛ ቆሮንቶስ 10:4) *ሸንገላውን በቃሉ ልንዋጋው* እንችላለን (ዕብራውያን 4፡ 12)

10. የሰይጣን ዋነኛ ስልት ዓለምን እርሱ በሚያስበው መንገድ በተለያዩ ቡድኖች "ምሽግ" ከፋፍሎ መያዝ ነው

የሰይጣን ስልት ዓለም በሆነ ዓይነት አመለካከት እንዲመራና እርስ በርሱ እንዲጠፋፋ ማድረግ ነው። የዓለም *ታላላቅ* ፍልስፍናዎች፡- ሐይማኖት የለሽነት (ሂዩማኒዝም) (Humanism)፣ እግዚአብሔርን መካድ(Atheism) እና ማርክዚም የዲያብሎስ አስተሳሰብ *መገለጫዎች* ናቸው። እነኚህ አስተሳሰቦች ናቸው ሰዎችን ወደ እርስ በእርስ እልቂት የሚመሩት።

> የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፣ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ **የሰውንም አሳብ** በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፣
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 10፡ 4-5

11. አገልጋዮች የእግዚአብሔር ቃል በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የሚኖረውን ሚና ሊገነዘቡ ይገባቸዋል

ቤተ ክርስቲያን በግዛቶች፣ አገሮች፣ ሰዎች እና በቤተ ክርስቲያን ላይ የጠላት ኃይል እንዳይንሰራፋ ምሽጉን ማዳከም አለባት። አገልጋዮች ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉ በላይ መሆን(መላቅ) ሊያረጋግጡ ይገባል። የእግዚአብሔር ቃል ሲበዛ፤ በነፍሳት ላይ ያለው የሰይጣን ይዞታ ይላላል። ይህን አስደናቂ ጥቅስ አንብብና በእግዚአብሔር ቃል ኃይል አመን።

> የእግዚአብሔርም **ቃል እየሰፋ** ሄደ፣ በኢየሩሳሌምም **የደቀ መዛሙርት ቍጥር እጅግ እየበዛ** ሄደ፤ . . .
>
> የሐዋርያት ሥራ 6፡ 7

የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ ሲሄድ፣ የክርስቲኖች ቁጥር ይበዛል። ለዚያ ነው መጽሐፍትን የምጽፈውና በተቻለኝ መጠንና በተደጋጋሚ የምሰብከው። በጨለማው ሥልጣን ላይ የሚያደርገውን አውቃለሁ።

12. ክርስቲያን መሪዎች በመንፈሳዊ ውጊያ ሰይጣንን ለማሸነፍ ሁለት ደርዝ ያለውን መሣሪያ "ጸሎትና ቃሉን" መጠቀም አለባቸው

የጸሎት አገልግሎት እና የቃሉ አገልግሎት እውነተኛ አገልግሎት ነው። ያ ነው እግዚአብሔር የሰጠን ሁለት ጠርዝ ያለው መሣሪያ። ሐዋርያት ይህን ተጠቅመዋል! ከጸሎት እና ቃሉን ከማገልገል መወሰድን አሻፈረኝ ብለዋል።

> አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው፦ የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ፣ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፣ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን **በጸሎትና ቃሉን ስማገልገል** እንተጋለን።
>
> ሐዋርያት ሥራ 6፡ 2-4

13. የመንፈሳዊ ውጊያ መልካም ምሳሌ ክርስቶስ ኢየሱስ ነበር አስተምሯልም ጸልዮአልም

> ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄደ በዚያ ጸለየ። ሰምዖንና ከእርሱ ጋር የነበሩትም ገሥግሠው ተከተሉት ባገኙትም ጊዜ፦ ሁሉ ይፈልጉሃል አሉት። እርሱም፦ በዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ስፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ ወጥቻለሁና አላቸው።
>
> ማርቆስ 1፡ 35-38

ኢየሱስ የነበረውን ውጤት ለማግኘት ከፈለግን፣ እርሱ የተጠቀመባቸውን መንገዶች ልንጠቀም ይገባናል። እናም የእርሱ መንገድ ደግሞ መጸለይ እና ማስተማር ነበር።

14. ምሽግን ከማዳከም በተጨማሪ አገልጋዮች የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰፋ ዘንድ የአጋንንትን ኃይላትን ማስለቀቅ፣ ስፍራ ማሳጣት ወይም ለጊዜው ስፍራ እንዲለቁ ማድረግ ይችላሉ

በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ፣ አጋንንቶች ከሰዎች ውስጥ ወጥተው ዓሣማዎች ውስጥ እንዲገቡ አድርጓል፡፡

> ኢየሱስም ፈቀደላቸው፡፡ ርኩሳን መናፍስቱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ገቡ፣ ሁሉት ሺህም የሚያህል መንጋ ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና በባሕር ሰጠሙ፡፡
>
> ማርቆስ 5፡13

15. ዲያብሎስን ባሸነፍህ (ባዳከምህ ወይም ባስለቀቅህ) ቁጥር መልሶ ማጥቃት እንደሚሰነዘርብህ መጠበቅ ይገባሃል

ኢየሱስ ዲያብሎስን በምድረ በዳ በአሸነፈ ጊዜ፣ ሰይጣን ለጊዜው እንደተለየው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ሰይጣን እስከ መጨረሻው አልተለየውም፡፡ ዲያብሎስ ብትሆን ጠላትህን እስከ መጨረሻው ትተወዋለህ? በፍፁም! ታፈገፍጋለህ፣ ትደራጃለህ እናም በሌላ ቀን እንደገና ታጠቃለህ፡፡

> ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ **እስከ ጊዜው** ከእርሱ ተለየ፡፡
>
> ሉቃስ 4፡13

16. ጸሎትና ጾም የአጋንንትን ኃይል የሚያዳክሙ እና የሚያስለቅቁ መሣሪያዎች ናቸው

ኢየሱስ አጋንንቶችን በጸሎት እና በጾም ስፍራ ማስለቀቅ እንደሚቻል አስተምሯል፡፡

> ይህ ዓይነት **ግን ከጸሎትና** ከጾም **በቀር አይወጣም** አላቸው፡፡
>
> ማቴዎስ 17፡ 21

17. የእግዚአብሔር ቃል በተጨማሪ፣ ሰይጣንን ያዳክመዋል፣ ያሰቃየዋል

ኢየሱስ ቃሉን በሚያስተምርበት ጊዜ አጋንንቶች እንዴት ይጮኹ እንደነበር ታስተውላለህ፡፡

> በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ እርሱም፡- የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፣ ከእኔ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፣ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ፡፡ ኢየሱስም፡- ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው፡፡
>
> ማርቆስ 1፡23-25

በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ ኢየሱስ አልጸለየም ወይም ዲያብሎስን አላስረገም፡፡ ዲያብሎስ ግን እንዲህ አለ፣ “አቁም! አታሰቃየኝ! እየጎዳኸኝ ነው!” መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ሰይፍ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በተናገርህ ጊዜ ሁሉ፣ ኃይለኛ ሰይፍ ይለቀቃል፡፡ ማንኛውም መጋቢ ሁሉ በአገልግሎቱ ስኬታማ ለመሆን ይህን ታላቅ ሰይፍ መጠቀም አለበት፡፡

18. ማንኛውም አገልጋይ በሥጋው እንዳያገለግል ሊጠነቀቅ ይገባዋል

መጽሐፍ ቅዱስ ምድራዊ መሣሪያ እንደሌለን አስጠንቅቆናል፡፡

> የጦር ዕቃችን **ሥጋዊ አይደለምና**፣ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 10፡ 4

ዲያብሎስም በተፈጥሮአዊው ዓለም እንዳልታጠቅን ስለሚያውቅ በሰብዓዊ፣ ዓለማዊ እና ተፈጥሮአዊ ነገሮች እንድንጠመድ ለማድረግ ይሞክራል፡፡ ለዚያ ነው ዛሬ ብዙ የወንጌል አገልጋዮች መምህራን፣ አስተዳዳሪዎች፣ ሥራ አስኪያጆች ወዘተ የሆኑት፡፡ በዚህ ወጥመድ ውስጥ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ፡፡

ምዕራፍ 5

ጠላትህን ታሸንፈው ዘንድ የጠላትህን ማንነት እንድታውቅ የሚረዱ ሃያ መንገዶች

ጠላትህን ታሸንፍ ዘንድ ስለ እርሱ ማወቅ የሚቻልህን ያህል ልታውቅ ይገባሃል። ይህ በጣም የተለመደ አንዱ የጦርነት ህግ ነው። ለዚህም ነው ዓለማዊ ሠራዊቶች በቅኝትና በስለላ ሥራዎች የሚሠማሩት። ቅኝት የጠላትን ጥንካሬ፣ ድካም፣ እቅድ እና አቀማመጥ የማወቅ ጥበብ ነው። ካለዚህ ጦርነቱን መጀመር እንኳ አይቻልም።

ስለ ጠላታችን ልናውቅ ከምንችልባቸው መንገዶች ውስጥ አንደኛው በስሞቹና በማዕረጎቹ ላይ ፈጣን የሆነ ምርመራ (ትንተና) ማካሄድ ነው። ለነገሩማ፣ ስም ስለ አንድ ሰው ብዙ ይናገራል። የሚከተሉትን ሃያ የሰይጣን ስሞችና ማዕረጎች ካጠናህ በኃላ ከምን ጋር እየተፋለምህ እንደሆን ታውቃለህ።

1. **ዲያብሎስ**

   ኢየሱስም፦ እኔ እናንተን አሥራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን? ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ መለሰላቸው።

   ዮሐንስ 6፡ 70

ይህ **ዲያብሎስ** የሚለው ቃል ከግሪክ የተወረሰ ቃል ነው። ዲያቢሎስ የሚለው ቃል የሚገልጠው የዚህን ክፉ ፍጡር ዋነኛ ተፈጥሮ ነው። ትርጓሜውም

ሰብዓዊነት የጎደለው ጨካኝ ወይም ክፉ ማለት ነው። ደግሞም አሰቃቂ ወይም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ መጥፎ የሆነ ማለት ነው።

2. ሰይጣን

ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህ ሆነ የአምላክ ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መጡ፣ **ሰይጣንም** ደግሞ በመካከላቸው መጣ።

ኢዮብ 1፡6

ሰይጣን የሚለው ቃል ከዕብራይስጥ ቋንቋ የመጣ ቃል ነው። ቀጥተኛ ትርጓሜው ጠላት (ባላጋራ) ማለት ነው። የሚናገረውም **ዲያብሎስ** ወይም **የሲኦል** ስለመሆን ነው። ይህ ስም በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ነው። የሚገልጠውም የኢዮብን ጠቅላላ ቤተሰብ እና ሀብት ስላወደመ እጅግ ክፉ ስለሆነ ፍጡር ነው።

ሰይጣን የእግዚአብሔር እና የሰው ቀንደኛ ጠላት ነው። በዚህ አስደናቂ ንባብ ውስጥ፣ ሰይጣን ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት የሚችል እውነተኛ ሰው የሚመስል ተደርጎ ተገልጧል። በተጨማሪም ደግሞ ወንድሞችን የመክሰስ ኃይል ያለውና ውድመታቸውን የሚፈልግ ነው።

3. የወንድሞች ከሳሽ

ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው **የወንድሞቻችን ከሳሽ** ተጥሎአልና።

ራእይ 12፡10

ይህ ስያሜ የሚገልጠው በእግዚአብሔር አገልጋዮች ላይ አለማቋረጥ የሚሰነዘረውን ክስ እና ስም ማጥፋት ነው።

4. ባላጋራ

በመጠን ኑሩ ንቁም፣ **ባላጋራችሁ** ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ ነኛ ጴጥሮስ 5፡8

ይህ ስም ሰይጣን በምናደርገው ነገር ላይ ሁሉ የሚዋጋን ተቃዋሚ ተፈጥሮውን የሚያሳየን ነው። **ስወንጌል እንዲህ ያለ ተቃውሞ፣ ጥላቻ እና ማግለል ቢኖር አይደንቅም።**

የሰይጣን ወኪሎች የማያምኑ፣ በቤተ ክርስቲያን እና በመሪዎቿ ላይ የተቃውሞ መንፈሳቸውን ያስተጋባሉ። ብዙ አገሮች ለቤተ ክርስቲያን ምስረታ ፀር የሆኑ ህጎች አሏቸው። ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያኖች ለአንድ አገር ብዙ የጤና እና የትምህርት ጥቅሞችን ቢያበረክቱም፣ የፖለቲካ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ከጥላቻ(ተቃውሞ) ውጭ ምንም ምርጫ የላቸውም።

5. የጥልቁ መልአክ

> እነርሱም ላይ ንጉሥ አላቸው እርሱም **የጥልቅ መልአክ** ነው፣ ስሙም በዕብራይስጥ አብደን በግሪክም አጶልዮን ይባላል።

ራእይ 9፡11

ይህ ስም የሰይጣንን እና የጭፍሮቹን መጨረሻ የሚገለጥ ነው። ይህ ሰይጣን ከጭንቀት የተነሳ የምድርን ዳርቻ ሁሉ ለመያዝ የሚያደርገውን ጥረት ያሳየናል። እኛም አሁን ልንነቃና ይህን ተስፋ ቢስ ሰይጣን በየአቅጣጫው መልሰን ልናጠቃው ይገባናል።

6. ቤልሆር

> ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?

2ኛ ቆሮንቶስ 6፡15

ቤልሆር ማለት ዋጋ የሌለው ማለት ነው። ሰይጣን ሊያዋርድ ወጥቷል። እንዲያው እስኪ በሰይጣን ተፅዕኖ ስር ያለን አንድ ሰው ተመልከት። ምን ያህል ዋጋ ቢስ እንደሆነ ታስተውላለህ።

ሰይጣን ወጣቶችን የዕፅ ሱሰኛ፣ ትምህርታቸውን ያቋረጡ፣ ዕፅ አዘዋዋሪ፣ ወዘተ በማድረግ ዋጋ ቢስ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ቤልሆር ወጣት ሴቶችን ክብርን በሚነካ የሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ውስጥ ይዘፍቃቸዋል።

7. ብዔልዜቡል

ፈሪሳውያን ግን ሰምተው፡- ይህ በብዔልዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ።

ማቴዎስ 12፡24

“የዝንቦች ጌታ” ማለት ነው። የዝንቦች ጌታ እንደሚታወቀው የበሽታ እና የሞት ተቆጣጣሪ ነው። ሰይጣን የድርቅ፣ የበሽታ እና ዛሬ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች ሞት ምክንያት የሆነው መዓት ምንጭ ነው።

8. የዚህ ዓለም አምላክ

ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፣ የዚህ ዓለም አምላክ የሚያደርጉትን አሳብ አሳወረ።

2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4

“እርሱ(እግዚአብሔር) ዓለምን ሁሉ በእጁ አግብቷል።” ይህን መዝሙር ነው ሁላችንም በሰንበት ትምህርት ቤት የተማርነው፣ ግን በእርግጥ ሁኔታው እንዲያ ነው? ዓለምን ሁሉ በእጁ ካደረገ፣ ለምን ታዲያ በየስፍራው ብዙ ጦርነት እና ድርቅ ይኖራል? ለምን በዓለም ላይ ደስታ ማጣት ይኖራል? ለምን ገሚሱ ዓለም በጣም ሀብታም ሌላው ደግሞ በጣም ድሃ ይሆናል?

በእርግጥ፣ ይህ ዓለም በያህዌ አስተዳደርና አመራር ስር አልሆነም። ታያለህ፣ ሰይጣን በእርግጥ የዚህ ዓለም አምላክ ነው። ያህዌ ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠረው(በመንግሥተ ሰማይ)፣ መንገዶች የተሠሩት ከወርቅ ነው እናም ሰዎች የሚኖሩት በደስታ እና በተድላ ነው።

አንድ ቀን ጌታ የዚህን ዓለም ገዥነት ሲወስድ፡- ፍቅር፣ ሰላም እና ደስታ ያለው የተለየ ምድር ይሆናል።

9. ነፍሰ ገዳይ

እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ **ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ** ነበረ፣ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ ሐሰትኛ የሐሰትም አባት ነውና።

ዮሐንስ 8፡44

ይህ ለሰይጣን ተገቢ የሆነ ስያሜ ነው። እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው። እርሱ ገዳይና በዓለም ላይ ያለው ደም መፋሰስ ምንጭ ነው። የአንድን አገር መሪ ሲቆጣጠር ይህ ፕሬዘዳንት አገሩን ምንም ትርጉም ወደ ሌለው እና ግብ ወደ ሌለው ጦርነት ውስጥ ሊመራ ይችላል።

የብዙዎች አባቶች፣ ባሎችና ወንድሞች ሲታረዱ፣ ነፍሰ ገዳዩ ግን ዝነኛ እንደሆነ ይኖራል።

10. የአጋንንት አለቃ

ፈሪሳውያን ግን ሰምተው፦ ይህ በብዔልዜቡል **በአጋንንት አስቃ** ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ።

ማቴዎስ 12፡ 24

ይህ ስያሜ የሚያመለክተን የጨለማውን ኃይሎች የተደራጀ ተፈጥሮ ነው። አጋንንቶች በሠራዊት ክፍሎች የተደራጁ ናቸው። የአጋንንት አለቃ የተባለ ጠቅላይ አዛዥ አላቸው። ወደ መንፈሳዊ ውጊያ ስንገባ የምንዋጋው ከተደራጀ እና አስተዋይ ከሆነ ጠላት ጋር ነው።

11. በአየር ላይ ያለው ኃይል መንፈስ አለቃ

በእነርሱም፣ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፣ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው **በአየር ላይ ሥልጣን እንዳስው አስቃ** ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።

ኤፌሶን 2፡2

ይህ የሚያሳየው ሰይጣን በማንኛውም ሀገር ውስጥ ከባቢ አየሩን ወይም የአየር ሞገድ እንደሚቆጣጠር ነው። የማንኛውንም አገር የሬድዮ እና ቴሌቪዥን ሞገድ ልብ ብለህ ተመልከት። ሰይጣን እነዚህን መስኮቶች ምን ያህል እንደተቆጣጠራቸው ታያለህ። ለክርስቲያኖች የአየር ሞገዶችን ለመቆጣጠር መዋጋት በጣም አስፈላጊ ነው። የአገራችንን ጥበብ፣ ባህል እና ሙዚቃ ለመቆጣጠር መዋጋት አለብን። ይህ በአየር ላይ ያለው አለቃ ግዛት ነው እናም እርሱን ማስለቀቅ የእኛ ኃላፊነት ነው።

12. የዚህ ዓለም ገዥ

> ከእንግዲህ ወዲህ ከአንተ ጋር ብዙ አልናገርም፣ **የዚህ ዓለም ገዥ** ይመጣልና፣ በእኔ ላይም አንዳች የለውም፤
>
> ዮሐንስ 14፡30

ይህ የሚያሳየው ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ መሆኑን እና የዚህን ዓለም ሥርዓት ተቆጣጣሪ መሆኑን ነው። ዓለም እያደገች በሄደች ቁጥር ሁሉ ነገር ይበልጥ አምላክ የለሽ ይሆናል። በቅርብ ጊዜ ለአንድ ወዳጄ እንዲህ አልኩት፡- “አውሮፓ ውስጥ በምሆንበት ጊዜ ሰዶም ውስጥ የሆንሁ ይመስለኛል።” እንዲህም አልኩት፣ “አውሮፓ አዲሱ ጴርጋሞን ናት!” ጴርጋሞን የሰይጣን መቀመጫ እና ለአጋንንታዊ አሠራር ዋና ጽሕፈት ቤት ነበረች፣ (ራዕይ 2፡13)

13. የቀድሞው እባብ

> **እባብም** ለሴቲቱ አላት፡- ሞትን አትሞቱም፤
>
> ዘፍጥረት 3፡4
>
> ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፣ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም **የቀደመው እባብ** ተጣለ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።
>
> ራእይ 12፡ 9

በመጀመሪያ የተገለጸው እንደ እባብ ነበር። በመጨረሻም፣ እንደ እባብ ነበር የተገለጸው። እባቦች የመጨረሻ አደገኛ ፍጡሮች እንደሆኑ ነው የምናውቀው። በአንድ ጭረት፣ የሰውን ልጅ መግደል ይችላሉ። ሆኖም፣ እባቦች ሳይታወቅባቸው ከሰው ልጆች በቅርብ መኖር ይችላሉ። ሰይጣን ልክ እንዲህ ነው የሚሠራው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለ ግን ሰዎች ይህን አያውቁም። በቅርብ ሆኖ ጥፋት እያደረሰ ነው ግን አይታይም።

ከሰይጣን ጋር ስንዋጋ፣ ምንም እንኳ የማይታይ ቢሆንም፣ በእርግጥ መኖሩን ያለማቋረጥ ልናውቅ ይገባናል። ረጅም ሳር ባለበት ስፍራ በማልፍበት ጊዜ ሁሉ አደገኛ እባብ በቅርብ ሊኖር እንደሚችል አውቃለሁ። ማንኛውም መጋቢ የማይታይ አጋንንታዊ አሠራር በአካባቢው ሊኖር እንደሚችል ሊገነዘብ ይገባዋል።

14. ፈታኝ

ፈታኝም ቀርቦ፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው።

ማቴዎስ 4፡3

ሰይጣን የፈተና ምንጭ ነው! እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የወሰነውን ውሳኔ የሚፈታተኑ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ኢየሱስን ፈትኗል፣ አንተ እና እኔንም ይፈትናል። ግን እግዚአብሔር ሊያድንህ ይመጣል። እርሱ ለፈተና ሁሉ መውጫውን ያዘጋጃል።

15. ርኩስ መንፈስ

ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፣ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፣ አያገኝምም።

ማቴዎስ 12፡43

ርኩስ የሚለው ቃል ሰይጣንን ለመግለጽ በተደጋጋሚ ተጠቅሟል። ይህ የሆነበትም ምክንያት ሰይጣን እንደዚያው ስለሆነ ነው። የምንዋጋው ተላላፊ ተፈጥሮ ካለውና ርኩስ ሊያደርግህ ከሚፈልግ ፍጡር ጋር ነው።

ርኩስ የሚለው ቃል የመጣው እካርታርቶስ (akarthartos) ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ትርጓሜው ንፁህ ያልሆነ፣ ባለጌ፣ የሚበክል እና ርኩስ የሚል ነው። የሰይጣን መገኘት ሁሉን ነገር ንፁህ እንዳይሆን እስካደረገ ድረስ ይህ የእርሱ አጠቃላይ አጠራር ነው። ንፁህ የሆነው ግንኙነት ርኩስ መንፈስ ጣልቃ ሲገባበት ንፁህ ያልሆነ ይሆናል። ንፁህ ባልንጀርነት ከሳሹ ጣቱን ሲቀስርበት ያደፈ ይሆናል።

16. ክፉ የሆነው

> የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፣ **ክፉው** ይመጣል፣ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።

ማቴዎስ 13፡19

የዲያቢሎስ ክፋት ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነው። አልፎ አልፎ፣ ሰዎች ሰይጣን በከፍተኛ ሁኔታ ተዕእኖ ሲያድርባቸው ይህ ክፉ የሆነውን ባህሪ ያንጸባርቃሉ። የሴራሊዮን ጦርነት፣ የሩዋንዳ እና የኮሶቮ ዘርን ማጥፋት የሰይጣንን ክፋት የሚመሰክሩ ናቸው። ይህንን ጠላት ነው ለማስለቀቅ እና ለማዳከም የምንፈልገው። በኢየሱስ ስም ክፉውን እናሸንፋለን።

17. ሉሲፈር

> አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፣ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ! አንተም በልብህ፦ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፣ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ።

ኢሳይያስ 14፡12-15

ሉሲፈር(የንጋት ኮከብ) የሚለው ስም የተሰጠው ከጸጋው ለወደቀ መልአክ ነው። ሉሲፈር በሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ በይበልጥ ተገልጿል።

> የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ። በእግዚአብሔር ገነት በዔድን ነበርህ፤ የከበረ ዕንቁስ ሁሉ፣ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፣ ወርቅ፣ ልብስህ ነበረ፣ የከበሮህና የእንቢልታህ ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፤ በተፈጠርህበት ቀን ተዘጋጅተው ነበር። አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ፤ በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ። ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ።
>
> ሕዝቅኤል 28፡ 13-15

አስደናቂ ፍጡር እንደ ነበር ማየት ትችላለህ! የክብሩ አገላለጾች ምን ዓይነት ፍጡር እንደሆነ ያሳያሉ። እንዲህ ያለው ፍጡር ከተበላሸ፣ ምን ዓይነት ጭራቅ እንደተለቀቀ መረዳት ትችላለህ።

ሰይጣን በሙዚቃ ሙያ (በእንቢልታ እና በከበሮ) ያለው ችሎታ በዚህ ምንባብ ውስጥ ተገልጿል። በሚሊዮን የሚቆጠሩትን መጥፎ በሆነው የሙዚቃ ኃይል ማርኮ ቢይዝ የሚደንቅ አይደለም።

18. የውሸት አባት

> እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ አውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ **ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና**።
>
> ዮሐንስ 8፡44

ሳዳም ሁሴን ኩዌትን በወረረበት እና በሌላው ዓለም ላይ ጦርነት ባወጀበት ወቅት፣ "የጦርነቶች ሁሉ እናት ይኖረናል።" በማለት አሜሪካንን አስፈራርቶ ነበር። አንድ ሰው "እናት" ወይም "አባት" ተብሎ ሲገለጽ፣ የሆነ በጣም አስፈላጊ ነገር እንደሆን ይገባናል። ሰይጣን የሐሰት አባት ከሆነ የሸንገላ ሁሉ ወላጅና ፈጣሪ ነው። የሰይጣን የማሳት ኃይል ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነው።

19. አብዶን

> በእነርሱም ላይ ንጉሥ አላቸው እርሱም **የጥልቅ** መልአክ ነው፤ ስሙም በዕብራይስጥ **ሸብዶን** በግሪክም አጶልዮን ይባላል።

ራእይ 9፡11

ይህ የጥልቁ መልአክ ነው። በኢዮብ መጽሐፍ ቃሉ ጥፋት ተብሎ ተተርጉሟል። *ልታገኘው ካልቻልህ አጥፋው!* ይህ ደንበኛ የዲያብሎስ ተፈጥሮ ነው። የአንዳንድ አገር መሪዎች በሥልጣን ላይ መቆየት እንደማይችሉ ሲያውቁ፣ አገራቱን ሁሉ በጦርነት በማጥፋት ይደሰታሉ። ይህን ሀሳብ የሚያገኙት ከአለቃቸው ከአብዶን ነው።

20. አለቆች፣ ሥልጣናት፣ የጨለማ ዓለም ገዦች፣ ክፉ መናፍስት

> መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር ሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።

ኤፌሶን 6፡12

በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ ጳውሎስ ሰይጣን የሚያሰራጫቸውን ወኪሎቹን በአራት ዋነኛ ቡድኖች ከፋፍሏል። አለቆች የሚወክሉት አንድ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ የሚቆጣጠሩ መናፍስትን ነው። የተለያዩ ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎችን የሚቆጣጠሩ የተለያዩ መናፍስት መኖራቸው ግልጽ ነው። ለምሳሌ አመስተርዳምን ብንወስድ የሥነ ምግባር ብልሹነት አለቃ አላት። እንዲህ የሚል አባባል አለ መልካም ልጆች ወደ መንግሥተ ሰማያት መጥፎ ልጆች ወደ አምስተርዳም ይሄዳሉ ይባላል።

ሥልጣናት ግለሰቦችን በተናጠል የሚቆጣጠሩ ናቸው። ሌላ ልትሰጣቸው የምትችለው ስም "ተጽዕኖ የሚያደርግ መንፈስ" የሚል ነው።

በከፍታ ስፍራ ያሉ ክፉ መናፍስት የሚናገረው በሰማያዊ ስፍራ ስለሚገኙ ክፉ አካላት ነው። እንዲህ ያለው ነበር የዳንኤል የጸሎት መልስ ይዞ የመጣውን መልአክ የተቃወመው (ዳንኤል 10 ፡ 13)

የጨለማው ዓለም ገዦች የሚገልጸው በዓለም ውስጥ ያለውን ጨለማ ስለሚቆጣጠሩ መናፍስት ነው። ወንበዴዎች እና የማያምኑ ሁሉ ሳያውቁት በእነዚህ መናፍስት ቅጥጥር ሥር ናቸው።

ምዕራፍ 6

መጋቢዎች ውጤታማ ጸሎት እንዲጸልዩ የሚያደርጉ አምስት መንገዶች

. . . የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፡፡

ያዕቆብ 5፡16

ጸሎት ሁሉ ውጤታማ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጸሎቶችን ከጣራ የማያልፉና ጊዜ ማባከን ናቸው፡፡ በአገልግሎት ውስጥ ውጤታማ ጸሎት መጸለይ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ጸሎቶችህ የማይሠሩ ከሆኑ የምታደርጋቸውም ነገሮች ብዙም መፈንፈሳዊ ያልሆኑ ነገሮች ይሆናሉ! ጸሎቶችህ የማይሠሩ ከሆነ፣ የምትናገረው ነገር ሁሉ የመንደር ህጻናት **"ፀሀዬ ውጪ ውጪ ዳመና ኮሶ ጠጪ"** ብለው እንደሚጫወቱት ይሆናል፡፡
ቀጥሎ ውጤታማ ጸሎት የምትጸልይባቸውን አምስት ደረጃዎች አካፍልሃለሁ፡፡

1. ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን ጸልይ

ጸሎትህ በእግዚአብሔር ቃል የሚመራ ይሁን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡትን ጸሎቶች ጸልይ፡፡ ለምሳሌ በኤፌሶን 1 ፡ 17-19 አገልጋይ ሊጸልያቸው ከሚገቡ ኃይለኛ ጸሎቶች ውስጥ አንዱ ይገኛል፡፡ ይህን ጸሎት ለብዙ ዓመታት ለራሴ ጸልያለሁ፡፡ አንተም እንድታደርገው እመክርሃለሁ፡፡

ሌላ አስፈላጊ የሆነ ጸሎት በኤፌሶን 3 ፡ 15-19 ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ "ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎት" ጸሎትህ በፍቅር ላይ የተመሠረተ

እንዲሆን ያደርጋል። ይህ ለማንኛውም መጋቢ አስፈላጊ ነው። መጋቢዎች ለአገልግሎት ከፍተኛ መስዋዕትነት ይከፈላሉ ግን ፍቅር ከሌላቸው፣ ሰማያዊ ሽልማታቸውን ያጣሉ። በሰማይ የአገልግሎትህን ሙሉ ፍሬ እንድታጭድ የእግዚብሔር ፈቃድ ነው።

> . . . ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።

1ኛ ቆሮንቶስ 13፡ 3

በሚቀጥለው ምዕራፍ፣ ጸሎትህ ለምን በእግዚአብሔር ቃል መመራት እንደሚገባው በጥልቀት አካፍልሃለሁ። የቃል ሰው ሁን። ራስህን ለእግዚብሔርና ለቃሉ ስጥ። በራስህ ከምታመን ይልቅ በቃሉ ታመን።

2. በጋለ ስሜት ጸልይ

በጋለ ስሜት መጸለይ ውጤታማ ጸሎት እንድትጸልይ ከሚያደርጉህ ሁኔታዎች አንዱ ነው። በጋለ ስሜት መጸለይ ማለት በጽናት፣ በፍቅር እና ከልብ የመነጨ ጸሎት መጸለይ ነው። የጋለ ስሜት ማለት ፍቅር፣ ጉጉት፣ ቀናኢ፣ የከረረ፣ ጥልቅ ስሜት ንቁ፣ ጉጉ፣ የሚያቃጥል፣ ጽኑ እና ዝግጁ ማለት ነው።

አንድ ሰው ስትጸልይ ከተመለከተህ፣ ከዚህ በላይ ካነበብካቸው ቃላት በአንዱ ሊገልጽህ መቻል አለበት። ጸሎትህ እንዲያ ከሆነ ትልቅ ውጤት እንደምታገኝ አረጋግጥልሃለሁ። በእርግጥ ዝም ብሎ ማነብነብ የጋለ ስሜትን አያሳይም!

3. በልሳን ጸልይ

ሁሉም አገልጋይ በልሳን በመጸለይ ሰዓታትን ማሳለፍ አለበት። ልሳን እግዚአብሔር የሰጠን ስጦታ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስላለው የልሳን ስጦታ በጣም ይመካ ነበር። እንዲህም ሲል በኩራት ተናግሯል "ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤" (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡ 18)። በዚህ ስጦታ መለኮታዊ በሆነ መንገድ ለእግዚአብሔር እንናገራለን።

የመንፈስ ሥጦታዎች ስንፈልግ ልንጠቀምባቸው አለበዚያ ደግሞ ልንተዋቸው የተሰጡን ተቀጥላ የሆኑ አላስፈላጊ ማጌጫዎች አይደሉም። **እግዚአብሔር የሰጠህን ተጠቀምበት እናም በአገልግሎትህ ትባረካለህ።**

4. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተነጋገር

ጸሎት በሁለት አቅጣጫ የሚሆን ጉዳይ መሆን አለበት። **በአገልግሎት ማደግ ከፈለግህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መነጋገር መማር አለብህ**። የእርሱንም ድምጽ መስማት አለብህ። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደ ነበረ የመንፈስ ቅዱስ አብሮነት ከእኛ ጋር ነው። በሚያስፈልገን ጊዜ ልናናግረው እንችላለን። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚነጋገሩ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው አረማመድ የላቀ ነው።

> ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ አመጣለሁ። አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።
>
> ዮሐንስ 14፡ 18፣26

ጸሎትህን አንድ እርምጃ ወደፊት አራምደው። ለመንፈስ ቅዱስ ተናገረው ደግሞም መልሶ ሲናገርህ ስማው። አስበኽው ከምታውቀው በላይ መለኮታዊ ምሪት ይኖርሃል።

5. ለረጅም ሰዓት ጸልይ

የሁለት ደቂቃ ጸሎት ከሰዓታት ጸሎት ይለያል። እግዚአብሔር ስለሚሰማህ ለረጅም ሰዓት አትጸልይ የሚል ጥቅስ የለም። ይልቁን፣ ኢየሱስ፣ ታላቁ አገልጋይ ለረጅም ሰዓት ጸልዮአል። የኢየሱስን ምሳሌነት ልትከተለው ግድ የሚል ነው።

> **ማለዳም ገና ጎሕ ሳይቀድ**፣ ኢየሱስ ተነሥቶ ከቤት ወጣ፤ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራም ሄዶ ይጸልይ ጀመር።
>
> ማርቆስ 1፡ 35
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ከእነዚያም ቀናት በአንዱ ኢየሱስ ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፤ **ሲቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።**

ሉቃስ 6፡12
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ማየት እንደምትችለው፣ ኢየሱስ ለሰዓታት ጸልዮአል። ጳውሎስም ለብዙ ሰዓቶች የሚጸልይ ሰው ነበር በመልዕክቱ ላይ ምን እንዳለ ተመልከት።

እንደ ገና ልናያችሁና በእምነታችሁ የጎደለውን ለማሟላት **ሌሊትና ቀን እጅግ ተግተን እንጸልያለን።**

1ኛ ተሰሎንቄ 3፡10
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ምዕራፍ 7

ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን እንድንጸልይ የሚያደርጉ ስድስት ምክንያቶች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጸሎት አገልግሎትህን ውጤታማ ማድረግ እንደምትችል ላካፍልህ እፈልጋለሁ። ይህ ትምህርት ቀላል ነው። ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎት ብዬ የምጠራውን ጸሎት ጸልይ! የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶች ስል ምን ማለቴ ነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የጸሎት ንድፎች ናቸው። በቃሉ ውስጥ የተዘረዘሩ የተለያዩ የጸሎት ርዕሶች ይገኛሉ።

i. **የጌታ ጸሎት**

እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤ እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤ ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፣ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን።

ማቴዎስ 6፡9-13

ii. **አንደኛ የኤፌሶን ጸሎት**

ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማስብን አልተውም፤ የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤

ኤፌሶን 1፡ 16-19

iii. ***ሁለተኛ የኤፌሶን ጸሎት***

ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፣ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፣ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፣ እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ፡፡

ኤፌሶን 3፡14-19

iv. **የጢሞቴዎስ ጸሎት**

እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ፣ ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ እድንኖር ነው፡፡ ይህ በእግዚአብሔር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው፤

1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-3

ስለ እነዚህ ነገሮች ብቻ መጸለይ አለብህ እያልኩ አይደለም፡፡ ግን እነኚህን ዋነኛ የጸሎትህ መስመር ብታደርግ በአገልግሎትህ ላይ ለውጥ ታያለህ፡፡ በዚህ ትምህርት ላይ ተጨማሪ ግንዛቤ እንዲኖርህ፣ ስልታዊ ጸሎት(strategic prayer) የሚለውን መጽሐፌን ተመልከት፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶች ጋር እንድትጣበቅ ግድ የሚሉህን ስድስት ምክንያቶች ልስጥህ እፈልጋለሁ፡፡

ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን እንድንጸልይ የሚያደርጉ ስድስት ምክንያቶች

1. የሰው ልጆች በአእምሮአችን፣ በአስተሳሰባችን እና በልባችን የተበላሸን ነን

አብዛኛውን ጊዜ ፍላጎታችን በተበላሸው ማንነታችን የተበላሸ ነው። የፈለገውን ያህል አንድ የእግዚአብሔር ሰው መንፈሳዊ ቢሆን፣ የመጨረሻ ደረጃ ላይ ቢደርስ፣ ያው ሰው ነው!

> ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 15፣ 53

2. እንዴት ልንጸልይ እንደሚገባን አናውቅም

የፈለገውን ያህል መንፈሳዊ ብንሆንም ነገሮችን አጥርተን ማየት አንችልም፡፡

> . . . እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን **አናውቅምና**፣
>
> ሮሜ 8፡26

> ዛሬስ በመስተዋት **በድንግዝግዝ** እንደምናይ ነን . . .
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 13-12

ይህ ጥቅስ ነገሮችን አጥርተን ማየት እንደማንችል ያስተምረናል። ራእይ በምታይበት ጊዜ፣ በእርግጥ የሚሆነው ምንድነው፣ ወደ መንፈሳዊው ዓለም ተሳብክ ማለት ነው። ይበልጥ እየተሳብክ ስትሄድ፣ ራእዩ ይበልጥ ግልፅ እየሆነ ይመጣል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በእርግጥ ከሥጋህም ትወጣለህ። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፣ እርሱ እስከ ሦስተኛው ሰማይ የተወሰደን ሰው ያውቃል፡፡

> ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፣ . . . እንዲህ ያለው ሰው . . .
>
> እስከ ሦስኛው ሰማይ ድረስ **ተነጠቀ**። ወደ ገነት **ተነጠቀ** . . .
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡ 2፣3 ፣4

ይህ ሰው በሥጋው ይሁን አይሁን እንኳ አላወቀም። አብዛኞቹ ሰዎች ብዙ ርቀው አይወሰዱም እናም ራእያቸውም ደብዛዛ እና እርግጠኛ ያልሆኑበት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ብዙ ሰዎች ራእይ ወይም ትንቢት ብለው የሚጠሯቸው በድንግዝግዝ የተመለከቷቸውን ነገሮች ነው።

በጸሎት እንኳ፣ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እርዳታ ያስፈልገናል። በልሳን ስንጸልይ ጸሎታችንን መንፈስ ቅዱስ ይቆጣጠራ። ቢሆንም፣ መንፈስ ቅዱስ የጸሎትን ምሪት በጌታ ቃል እና በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ሰጥቶናል። እነኚህን መመሪያዎች ብንከተል ልክ በልሳን የመጸለይ ያህል ነው ምክንያቱም ቃሉ ስለ ምን እንድንጸልይ እንደሚገባን ይመራናል።

3. ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን ጸልይ ምክንያቱም የእኛ መንገድ የእርሱ መንገድ አይደለምና

አሳቤ እንደ አሳባችሁ መንገዳችሁም እንደ መንገዴ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር።

ኢሳይያስ 55፡8

ምንም ያህል መንፈሳዊ ብንሆን በሥጋ ውስጥ የምንኖር ሰዎች ነን። አውቃለሁ የምላቸውን ነገሮች እግዚአብሔር ሲያስተምረኝ አይቼአለሁ። ከብዙ ዓመታት በፊት በአገልግሎቴ ሙት ባስነሳሁ ነበር። ነገር ግን የእርሱ መንገድ የእኔ መንገድ አይደለም። እግዚአብሔር እኔን ተጠቅሞ የጓደኛዬን አባት ከሞት እንዲያስነሳ በጸሎትና በጾም ጠየቅኹት። ግን እግዚአብሔር ልብ ያለኝም አልመሰለኝም። የተጣልሁና የተዋረድሁ መሰለኝ። ወደዚያ በእምነት የሄድሁት ሙት በኢየሱስ ስም ይነሳ ብዬ በማወጅ ነበር!

አሳዛኙ እድሌ፣ የእኔ መንገዶች የእርሱ መንገዶች አይደሉም። ያ የሞተ ሰው ቢነሳ ኑሮ፣ ጠቅላላ ሕይወቴ እና አገልግሎቴ ሁሉ በተበላሸ ነበር። እግዚአብሔር የራሱ መንገድ ነበረው። መንገዱም እኔን መጠበቅ እና ረጋ ባለ ሁኔታ ወደ እውነተኛ አገልግሎት ውስጥ ማስገባት ነበር።

ወደ ሃያ ዓመት ካለፉ በኋላ፣ አንዲት ሴት ክሩሴድ በማካሂድበት መድረክ ላይ ቆማ የሞተ ልጇ እኔ በማገለግልበት ሰዓት ከሞት እንደተነሳ ስትመሰክር፣ ምንም ዓይነት ስሜት አልተሰማኝም። የተሰማኝ ነገር እግዚአብሔር የሞተን ማስነሳት ከፈለገ፣ ሙሉ በሙሉ የእርሱ ጉዳይ ነው። እኔ የማውቀው በክሩሴዱ መድረክ ላይ ተመልካች መሆኔን ነው። ይህ ከሃያ ዓመት በፊት ሆኖ ቢሆን ኖሮ ምናልባ በትዕቢት የተነሳ ከእምነት ባፈገፈግሁ ነበር።

ለዚህ ነው በአብዛኛው ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን መጸለይ የሚኖርብን። እግዚአብሔር እኛ የማናውቃቸውን ነገሮች ያውቃል። ራሳችንን ለእርሱ ጥበብ እንስጥ።

4. ኢላማችንን እንዳንስት ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶችን መጸለይ አለብን

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጸሎቶች ኢላማቸውን እንደሚስቱ ያስተምራል። ቀስትህ ኢላማውን ሲስት፣ ያሰብከው ቦታ አልደረሰም ማለት ነው! ጸሎቶችህ ወደ አብ ካልደረሱ ለምን ትጸልያለህ? ጸሎቶችህ የተፈለገውን ውጤት ካላስገኙ ለምን ትጸልያለህ? አሁን ኢላማን መሳት መቆም ያበለት ጊዜ ነው።

> ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና።
>
> ያዕቆብ 4፡3
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ለምን ብዙ ጸሎቶች ኢላማቸውን ይስታሉ? አሁንም እንደገና፣ እኛ ሰዎች በመሆናችን ነው። አጥርተን ማየት ስለማንችል ኢላማችንን በብዙ ርቀት እንስታለን። ራስህን ለስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶች ስጥ።

5. ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶች ለሕይወትህ በጣም ጠቃሚ የሆኑ አካባቢዎችን በሙሉ ይሸፍናሉ።

የጌታን ጸሎት ሙሉውን ብትመለከት፣ አስፈላጊ የሆነው አካባቢ ሁሉ እንደተጠቃለለ ታያለህ። በጌታ ስልታዊ ጸሎት ሥር፣ ስለ ዕለት ፍላጎትህ፣ ስለ ይቅር ማለት፣ ስለ ጥበቃ እና ስለ እግዚአብሔር ሥራ ትጸልያለህ።

በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የጳውሎስ ጸሎቶችን ለመረዳት ትንሽ ያስቸግራል። ርዕሳቸው እንኳ ምስጢራዊ ይመስላል። ምናልባት ለዚያ ይሆናል በጣም የሚያስፈልጉን። ምናልባት ስለ መገለጥ መንፈስ እና ጥበብ የመጸለይን ውጤት አታውቅ ይሆናል (ኤፌሶን 1 ፡ 17)። ለምሳሌ ሁለተኛው የኤፌሶን ጸሎት (ኤፌሶን 3 ፡ 17) በፍቅር ሥር እንድንሰድ እና እንድንተከል ያስተምረናል።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ለክርስቲያን ፍቅር መመስረት የሚለው ነገር በአብዛኞቻችን ጸሎት ውስጥ አይመጣልንም። ግን ከክርስቲያን ፍቅር ውጭ የሚሠራ መልካም ሥራ ሁሉ ውጤቱ ባዶ እንደሆነ ስትረዳ፣ ምናልባት መንፈስ ቅዱስ ለምን ያንን ጸሎት እንደሰጠን ትረዳ ይሆናል። ይህን በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ፡ 3 ላይ የሚገኝ ጥቅስ ልብ በል።

> ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፣ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ **ምንም ሰይጠቅመኝም**።

1ኛ ቆሮንቶስ 13፡3

ለአገልግሎት የሚከፈለውን ከፍተኛ ዋጋ ከፍለህ ቢሆንም እንኳ፣ እግዚአብሔርን ብታገለግል መልካም ነገር ነው። ይሁን እንጂ ካለ ፍቅር የሆነ መልካም ሥራችን ሁሉ ከባዶ እንዲቆጠር በአንድ የብዕር ጭረት ማስጠንቀቂያ ተነግሮናል።

6. ስልታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሎቶች በጣም አስፈላጊ የሆኑ የጸሎት አካባቢዎችን እንዳትተው ይጠብቁሃል

እነኚህን ጸሎቶች ስትጸልይ የሕይወትህን አስፈላጊ ነገሮች በሙሉ ታጠቃልላለህ፤ ምናልባት ለመንግሥት መጸለይ ላትፈልግ ትችል ይሆናል። አንዳንድ መንግሥታት አንድ ሰው ከሚጸልይላቸው ይልቅ ቢረግማቸው ይመርጣሉ። ቢሆንም፣ የመጽሐፍ ቅዱስን የጸሎት ዘይቤ ከተከተልክ እነርሱን ከመርገም ይልቅ ትጸልይላቸዋለህ።

> እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ እንዲደረግ አሳስባለሁ፣ ይህም በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር ነው።
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፣1-2
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

እነኚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስልታዊ ጸሎቶችን በመከተል ዋነኛ የጸሎት አካባቢዎችን ከመተው ራስህን አድን።

ምዕራፍ 8

ከልብ በመነጨ ስሜት የመጸለይ ሰባት ምሳሌዎች

1. **ኤልያስ አጎንብሶ ዝናብ እንዲመጣ የጠየቀበት ጽኑ ጸሎት፣ ከልብ የመነጨ ጸሎት ታዋቂ ምሳሌ ሆኖ ይኖራል።**

   ኤልያስ አክዓብን የዝናብ ውሽንፍር እጅግ ነውና ተነስተህ ውጣ ብላም፣ ጠጣም አለው። አክዓብም ሊበላና ሊጠጣ ወጣ፤ **ፊቱንም በጉልበቱ መካከል አድርጎ በግንባሩ ተደፋ።** ብላቴናውንም፦ ወጥተህ ወደ ባሕሩ ተመልከት አለው። ወጥቶም ተመልክቶም፦ ምንም የለም አለ። እርሱም ሰባት ጊዜ ተመላለስ አለው። ብላቴናውም ሰባት ጊዜ ተመላለሰ። በሰባተኛውም ጊዜ፦ እነሆ፣ የሰው እጅ የምታህል ታናሽ ደመና ከባሕር ወጣች አለ። እርሱም ወጥህ አክዓብን፦ ዝናብ እንዳይከለክልህ ሰረገላ ጭነህ ውረድ በለው አለ። ከጥቂትም ጊዜ በኋላ ሰማዩ ከደመናውና ከነፋሱ የተነሳ ጨለመ፣ ብዙም ዝናብ ሆነ፣ አክዓብም በሰረገላው ተቀምጦ ወደ ኢይዝራኤል ሄደ። የእግዚአብሔርም እጅ በኤልያስ ላይ ነበረች፤ ወገቡንም አሸንፍጦ ወደ ኢይዝራኤል እስኪገባ ድረስ በአክዓብ ፊት ይሮጥ ነበር።

   1ኛ ነገሥት 18፡ 41-46

ይህ በያዕቆብ የተነገረው የቅንዓት ጸሎት ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። በቅንዓት በመጸለይ የእግዚአብሔርን የበረከት ዝናብ በአገልግሎትህ ላይ ስታስለቅቅ ይታየኛል! የኤልያስን ምሳሌ ተመልከት፣ ስለ ዝናብ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ።

2. **እንባና ስሜት የተሞላው የሐና ልጅ የመጠየቅ ጸሎትም አስደናቂ ውጤት አምጥቷል።**

በሴሎ ከበሉና ከጠጡ በኋላም ሐና ተነሳች። ካህኑም ዔሊ **በእግዚአብሔር** መቅደስ መቃን አጠገብ በመንበሩ ላይ ተቀምጦ ነበር። እርስዋም በልብዋ ትመረር ነበር፤ **በእግዚአብሔርም** ፊት ጸለየች፤ ጽኑ ልቅሶም አለቀሰች።

እርስዋም፦ አቤቱ፤ የሠራዊት **ጌታ** ሆይ፤ **ስባሪያህም ይህን መዋረድ ተመልክተህ ብታስበኝ፣ እኔንም ባትረሳ ስባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ፤ ዕድሜውም ሁሉ ስእግዚአብሔር አሰጠዋለሁ፣ ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም** ብላ ስእለት ተሳለች። ጸሎትዋንም **በእግዚአብሔር** ፊት ባበዛች ጊዜ ዔሊ አፍዋን ይመለከት ነበር።

ሐናም በልብዋ ትናገር ነበር፤ ድምፅዋም ሳይሰማ ከንፈርዋን ታንቀሳቅስ ነበር፤ ዔሊም እንደ ሰከረች ቆጠራት። ዔሊም፤ ስካርሽ እስከ መቼ ነው? የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው አላት። ሐናም፦ ጌታዬ ሆይ አይደለም፣ እኔስ ልብዋ ያዘነባት ሴት ነኝ፤ ጠጅና ሌላ የሚያሰክር ነገር አልጠጣሁም፣ ነገር ግን **በእግዚአብሔር** ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ፤ ጎዘኔና ጭንቀቴ ስለ በዛ አሁን ድረስ ተናግሬአለሁና ባሪያህን እንደ ምናምንቴ ሴት አትቁጠረኝ ብላ መለሰችለት።

ዔሊም፦ በደህና ሂጂ፤ የእስራኤልም አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ ብሎ መለሰላት። እርስዋም፦ ባርያህ በዓይንህ ፊት ሞገስ ላግኝ አለች። ሴቲቱም መንገድዋን ሄደች በላችም፤ ፊትዋም ከእንግዲህ ወዲያ አዘንተኛ መስሎ አልታየም። ማልደው ተነስተው በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ፤ ተመልሰውም ወደ አርማቴም ወደ ቤታቸው መጡ። ሕልቃናም ሚስቱን ሐናን አወቃት፤ እግዚአብሔርም አሰባት፤ የመፀነስዋም ወራት ካለፈ በኋላ ሐና ወንድ ልጅ ወለደች እርስዋም፦ ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው።

1ኛ ሳሙኤል 1፡9-20

ሐና በከባድ ችግር ውስጥ ነበረች። እስከፊ በሆነ ሁኔታ ጥሶ መውጣት አስፈልጓት ነበር። ዝም ብላ አቡነ ዘሰማያት አልደገመችም። መድገም ወይም ማነብነብ ማለት ማንገዋለል፣ ጊዜ ማጥፋት እና ተዕዕኖ ማሳደር የማይችል

ነው። ከእግዚአብሔር ለመቀበል ቆርጣ ነበር። ውድ መጋቢ፣ ከልብ የመነጨ ጸሎት በአገልግሎትህ ውስጥ አዲስ አቅጣጫ እንዲወለድ ያደርጋል።

3. የያዕቆብ የትግል አዳር ጸሎት አስገራሚ ውጤት አስገኝቷል

ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፤ አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር።

ዘፍጥረት 32፡24

ያዕቆብ እና ዘሩም የተባረከ ነበር። ብዙ ሺህ ዓመታት ቢቆጠሩም ይህ ከልብ የመነጨ ጸሎት ፍሬ ለሁሉም የሚታይ ነው። እስራኤል እስከ ዛሬ ድረስ በምድር ላይ ከታደሉ አገሮች አንዷ ናት።

4. *ሙሴ አማሌቃዊያንን ድል ለማድረግ የጸለየው የተቀጣጠለ ጸሎትም ሌላው ከልብ የመነጨ ጸሎት ምሳሌ ነው።*

አማሌቅም መጥቶ ከእስራኤል ጋር በራፊዲም ተዋጋ። ሙሴም ኢያሱን፦ ጎልማሶችን ምረጥልኝ ወጥተህም ከአማሌቅ ጋር ተዋጋ፤ እኔ ነገ የእግዚአብሔርን በትር በእጄ ይዤ በኮረብታው ራስ ላይ እቆማለሁ አለው። ኢያሱም ሙሴ እንዳለው አደረገ፣ ከአማሌቅም ጋር ተዋጋ፤ ሙሴና አሮንም ሑርም ወደ ኮረብታው ራስ ወጡ። እንዲህም ሆነ፤ ሙሴ እጁን ባነሳ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር፤ እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር። የሙሴ እጅ ግን ከብደው ነበር፤ ድንጋይም ወሰዱ፤ በበታቹም አኖሩ፤ እርሱም ተቀመጠበት፤ አሮንና ሑርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ።

ዘጸአት 17፡8-12

የልጆችህ ሕይወት በአስጊ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ዝም ብለህ ልታይ አትችልም። የማነብነብ ጸሎት ማንንም ጠቅሞ አያውቅም!

5. **ዳዊት መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ እንዳይወሰድበት በጥልቅ ስሜት ያቀረበው ጥያቄ ሌላው ከልብ የመነጨ ጸሎት ነው።**

> አቤቱ፣ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፣ ከኃጢአቴም አንጻኝ፤ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፣ ኃጢአቴም ሁል ጊዜ በፊቴ ነውና። አንተን ብቻ በደልሁ፣ በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፤ ለነገርህ ትጸድቅ ዘንድ በፍርድም ንጹሕ ትሆን ዘንድ። እነሆ፣ በዓመፃ ተፀነስሁ፣ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ። እነሆ፣ እውነትን ወደድህ፤ የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ። በሂሶጵ አርጨኝ፤ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ፣ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ። ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፤ የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል። ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፤ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ። አቤቱ፣ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። **ከፊትህ አትጣለኝ፣ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።** መዝሙር 51፡1-11

ዳዊት መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ተለየ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል። ያ እንዲሆን ሊፈቅድ አይችልም።

እግዚአብሔር በጥልቅ ስሜት የሚጸለዩ ጸሎቶችን ይሰማል። እግዚአብሔር የጸሎት ፕሮግራም ከመቼው ባለቀ ብለው የሚጠባበቁ ክርስቲያኖችን በመጸየፍ ይመለከታቸዋል።

6. **የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሪዎቻቸው ላይ እንዲለቀቅ በጋለ ስሜት ጸልየዋል።**

> ተፈትተው ወደ ወገኖቻቸው መጡና የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአቸው። እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ እንዲህም አሉ፦ ጌታ ሆይ፣ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ፣ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድድቅ ሲደረግ፣ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው። ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

> የሐዋርያት ሥራ 4፡23, 24, 30, 31

እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰማ ውጤቱንም ተመልከት፡፡ ቤተ ክርስቲያን በቅንዓት መጸለይ ስትጀምር ሁልጊዜ ውጤት ይኖራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የጸሎት ፕሮግራም አለን የሚሉ ሰዎችን እመለከታለሁ፡፡ አንዳንዶች ይተኛሉ ሌሎች ደግሞ ጊዜውን እንዲሁ ያሳልፋሉ፡፡ አንድ ሰው እያነጋገረህ እንቅልፍ ቢይዘው ምን ይሰማሃል? አያከብረኝም ወይም ስለ አንተ ምንም ስሜት እንደማይሰጠው ታስባለህ፡፡

7. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱ እንዲፈጸም ጥልቅ በሆነ ስሜት ጸልዮአል፡፡

> እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤
>
> ዕብራዊያን 5፡7

የዚህ ማረጋገጫ የደም ላብ ሲያልበው ነበር፡፡ ከልብ የመነጨ ጸሎት ሁልጊዜ ይሠራል፡፡ የኢየሱስ አገልግሎት ታላቅ ስኬት ነበር! በአገልግሎትህ ትልቅ ስኬት የሚኖርህ እንዴት በጥልቅ ስሜት መጸለይ እንደሚገባህ ስትማር ነው፡፡ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ሳታውቅ ስትቀር፣ ኢየሱስ ያደረገውን አድርግ፡፡ ኢየሱስ ሲጸልይ ድምጹን ከፍ አድርጓል! ኢየሱስ እስኪያልበው ጸልዮአል! ራስህ አንብበው!

> እጅግ ተጨንቆም በብርቱ ይጸልይ ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነበር፡፡
>
> ሉቃስ 22፡44
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ምዕራፍ 9

በቅንዓት የመጸለይ ሰባት ምልክቶች

ወጤት ለማግኘት በቅንዓት መጸለይ በጣም አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ፣ በቅንዓት መጸለይህን እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? በቅንዓት የመጸለይን ሰባት ምልክቶች ላካፍልህ እፈልጋለሁ። እንደተለመደው፣ ምርጥ የሆኑ ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ።

1. የሰውነት አቋም

የኤልያስ አገልግሎት የቅንዓት ጸሎት ምርጥ ምሳሌ ነው። በሚጸልይበት ጊዜ የሰውነቱን አቋም ማስተዋል ስሜትን ይስባል።

> . . . ኤልያስም ወደ ቀርሜሎስ አናት ወጣ፤ **ፊቱንም በጉልበቱ መካከል አድርጎ በግንባሩ ተደፋ።**
>
> ነኛ ነገሥት 18፡42

በጸሎት ክፍለ ጊዜ ራስህን እና በዙሪያህ ያሉትን መመልከት ጀምር። የሰውነት አቋም ምንድር ነው? የሰውነትህ አቋም በምን ዓይነት ጸሎት ውስጥ እንዳለህ ይናገራል።

2. ከፍ ያለ ድምፅ

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በመጮህ እና በእንባ ጸልዮአል። ጸሎቶችህ ዝግ ያሉ ወይስ በጩኽት ናቸው? ኢየሱስ በብርቱ ጩኽትና በእንባ ጸልዮአል። የኢየሱስን ምሳሌ መከተልን እመርጣለሁ!

> እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል **ከብርቱ ጩኽትና ከእንባ** ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፣ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤
>
> ዕብራዊያን 5፡7

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትርጉም የለሽ የሆነ ሀተታ የለም። እነኚህ ነገሮች የተጻፉት ለምሳሌአችን ነው። ከእምነት ጀግኖች እንማር።

3. ማንባት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ሰዎች በሚጸልዩበት ጊዜ አልቅሰዋል። ጌታችን ኢየሱስ ምርጥ ምሳሌ ነበር። ኢየሱስ ጸሎቶቹን ከእንባ ጋር አቅርቧል። በምትጸልይበት ጊዜ ብታነባ ምንም ችግር የለበትም። ኢየሱስ የቅንዓት ጸሎቶችን ጸልዮአል ደግሞም በአባቱ ተሰምቷል።

ሌላዋ ዝነኛ የጸሎት ተፋላሚ ሐና ነበረች። ሐና የሳሙኤል እናት ነበረች። መጽሐፍ ቅዱስ የጸሎት ጊዜዋን በስዕል አስቀምጦታል።

> እርስዋም በልብዋ ትመረር ነበር፤ **በእግዚአብሔርም ፊት ጸሰየች፣ ጽኑ ልቅሶም አስቀሰች።**
>
> 1ኛ ሳሙኤል 1፡10

4. ኃይልን ማሟጠጥ

በምትጸልይበት ጊዜ የሰውነትህ ኃይል ሊሟጠጥ ይችላል። ያዕቆብ ሌሊቱን በሙሉ ጸልዮአል። ያ የሚያደክም መሆን አለበት። ኢየሱስም በዙሪያው የነበሩትን ሁሉ እንቅልፍ እስኪጥላቸው ጸልዮአል።

> (ከጸለየ በኋላ) ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፣ ተኝተውም አገኛቸው. . .
>
> ማቴዎስ 26፡40

ሙሴ ሰዎች እጁን ከፍ ለማድረግ እስኪረዱት ድረስ በብርቱ ጸልዮአል።

> የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር፤ ድንጋይም ወሰዱ፤ በበታቹም አኖሩ፤ እርሱም ተቀመጠበት፤ አሮንና ሐናም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ . . .
>
> ዘጸአት 17፡12

5. በጸጥታ መቃተት

> ጸሎትዋንም በእግዚአብሔር ፊት ባበዛች ጊዜ ዔሊ አፍዋን ይመለከት ነበር። ሐናም **በልብዋ ትናገር ነበር፤ ድምፅዋም ሳይሰማ ከንፈርዋን ታንቀሳቅስ ነበር፤**
>
> 1ኛ ሳሙኤል 1፡12፣13

ይህ ሙሉ በሙሉ የቅንዓት ጸሎት ምሳሌ ነው። ይህች ሴት ልጅ እንድታገኝ ጥልቅ በሆነ ስሜት ጸለየች። ጩኸት ወይም ከፍ ያለ ድምፅ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ ዔሊ ስለምን ትጸልይ እንደነበር መስማት አልቻለም ይላል። እንዲያውም እንደ ሰከረች አስቦ ነበር። ይህንን ነው በጸጥታ መቃተት የምለው።

ሌላኛው በጸሎቱ የቃተተ ሰው ምሳሌ ኢየሱስ ነበር።

> ኢየሱስም እርስዋ ስታለቅስ ከእርስዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ **በመንፈሱ አዘነ(ቃተተ)** ለራሱም ታወከ፤
>
> ዮሐንስ 11፡33

6. ውስጣዊ ቁርጠኝነት

ቁርጠኝነት በቀላሉ አይገለጥም። አንድ ነገር እስኪፈጸም ድረስ መጸለይ ነው። አንድ ነገር እስኪፈጸም ድረስ በቁርጠኝነት የሚጸልይ ማንኛውም ሰው የጥልቅ ስሜት ወይም የቅንዓት ጸሎት ተዋጊ ነው።

> እንዲህም አለው። ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ። እርሱም፦ **ካልባረከኸኝ አልለቅህም አለው።**
>
> ዘፍጥረት 32፡26

ከእግዚአብሔር አንድ ነገር ለመቀበል ወደ ጸሎት ክፍለ ጊዜ በቁርጠኝነት የማይመጡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የጸሎት ክፍለ ጊዜው እስኪያልቅ የሚያነበንቡ እና የሚደግሙ ሰዎች ናቸው። ለጸሎት ጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ ለማግኘት ቁርጠኛ ሁን!

7. የምሬት ቋንቋ

በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገቡትን የዳዊትን ጸሎቶች ብታጠና ተስፋ የቆረጠን (ያዘነንን) ሰው ቋንቋ ታገኛለህ። ዳዊት የእግዚአብሔርን እርዳታ የሚፈልግ ሰው ነበር። ወደ እግዚአብሔር እጅ ለመድረስ የሚፍጨረጨር ሰው። ይህን አስታውስ፡- *እግዚአብሔር የምትለውን እያንዳንዷን ቃል ይሰማል።* የምትናገራቸው ቃሎች ወሳኝ ናቸው! ከዳዊት ጸሎቶች አንድ ምሳሌ ተመልከት።

> አቤቱ፣ አንተን ታመንሁ፣ **ስዘላስም አልፈራም**፣ በጽድቅህ አድነኝ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፣ **ፈጥነህም አድነኝ**፣ ታድነኝ ዘንድ መታመኛ አምላክና **የመጠጊያ ቤት ሁነኝ**። አምባዬና መጠጊያዬ አንተ ነህ። ስለ ስምህ መንገዴን አቅና ምራኝም።
>
> መዝሙር 31፡1-3

ምዕራፍ 10

ረጅም ሰዓት ለመጸለይ የሚረዱ ዘጠኝ እርምጃዎች

1. ለአንድ አገልጋይ ከአንድ ሰዓት ያነሰ ጸሎት ትርጉም የለሽ የመሆኑን እውነታ ተቀበል

ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት ስንኳ **ልትተጉ** አልቻላችሁምን?

ማቴዎስ 26፡40

ማስታወስ እስከምችለው ድረስ፣ አጭር ጸሎትን የማስበው ትርጉም የለሽ እንደሆነ ነው። ረጅም ሰዓት በጸሎት ካላሳለፍሁ ሁል ጊዜ የሚሰማኝ፣ ብዙ ማከናወን እንደማልችል ነው። ይህ ጥሩ የሆነ ሥነ-ልቦናዊ መመሪያ ሆኖልኛል። አብዛኛውን የሕይወቴን ሰዓቶች በጸሎት እንዳሳልፍ አድርጎኛል።

ከአንድ ሰዓት ያነሰ ጸሎት በቂ እንዳልሆነ ስታምን፣ በአምስት እና በአሥር ደቂቃ ጸሎት በፍፁም አትረካም። ይህ ቀስ በቀስ ወደ ረጅም ጊዜ ጸሎት ይመነጥቅሃል። ረጅም ጊዜ በመጸለይ አንዳች አይጎድልብህም!

2. በምትጸልይበት ጊዜ ሁሉ የጠረጴዛ ወይም የእጅ ሰዓት ለእይታ ምቹ በሆነ ስፍራ በማስቀመጥ ጸልይ

ልክ ጸሎት ስትጀምር፣ ሰዓቱን ተመልከት። ያን በምታደርግበት ጊዜ፣ በቂ ጊዜ በጸሎት ለማሳለፍ ትገደዳለህ። ሰዓትህን የማትመለከት ከሆነ ከጸለይከው በላይ ብዙ ሰዓት የጸለይህ ይመስልሃል። ለራስህ እንዲህ ትላለህ "ኦ፣ ወደ ሁለት ሰዓት ሳልጸልይ አልቀርም" ግን የጸለይኸው ለአሥር ደቂቃ ብቻ ነው።

የጸሎት ልምድ ያለህ ካልሆንክህ በቀር፣ የጸለይህበትን ሰዓት ርዝመት በትክክል መገመት አትችልም። ዛሬ ዛሬ፣ አንድ ሰዓት ስጸልይ ማወቅ እችላለሁ። ቀድሞ ግን፣ አሥር ደቂቃ ጸልዬ አንድ ሰዓት የጸለይሁ ይመስለኛል። ለዚህ ነው ዓይንህን በሰዓት ላይ ማኖር ያለብህ።

3. የስብከት ካሴት እያደመጥህ ጸልይ

ሁል ጊዜ ስጸልይ የስብከት ወይም የሙዚቃ ካሴት እያጫወትሁ እጸልያለሁ። አንድ እንድትረዳው የምፈልገው መርህ አለ። **የስብከት/ሙዚቃ ፍጥነት ከጸጥታ ፍጥነት በመቶ ጊዜ ይፈጥናል**። ይህ ማለት በምትጸልይበት ጊዜ የስብከት ወይም ሙዚቃ ካሴት ድጋፍ ካለ ሰዓቱ በመቶ እጥፍ ይፈጥናል ማለት ነው።

ሰዎች ለአንድ ደቂቃ ጸጥ እንዲሉ በተጠየቁበት ስፍራ ተገኝተህ ታውቃለህ? የጸጥታው ጊዜ ምን ያህል እንደቆየ አስተውለህ ታውቃለህ? ለአንድ ደቂቃ ሙሉ በእርግጥ በጸጥታ እንዳሳለፉ ታውቃለህ? ይህ የሚሆነው አሁን ባካፈልኩህ መርህ ምክንያት ነው፡- *የስብከት/ሙዚቃ ፍጥነት ከጸጥታ ፍጥነት በመቶ ጊዜ ይፈጥናል።* በስብከት ወይም ሙዚቃ ድምጽ ድጋፍ (background) በምትጸልይበት ጊዜ፣ ጊዜው በይበልጥ ይሮጣል! ሳይታወቅህ ለሰዓታት ጸልየሃል!

የእግዚአብሔር ቃል ስብከት ድምጽ ለመንፈሳዊ ነገሮች በጣም አመች የሆነ ከባቢ አየርን ይፈጥራል። ውድ ወዳጄ፣ አምላክ የለሽ በሆኑ ጓደኞቻችን እና

በቴሌቪዥን፣ ዓለማዊ በሆነው የሥራችን አካባቢ ያለማቋረጥ ተደብድበናል። እንዲህ ያለው ከባቢ አየር በእርግጥ ጸሎትን ይከለክላል። በቤታችንም ያለው ከባቢ አየር አብዛኛውን ጊዜ ፀረ-ጸሎት ነው። ቢያንስ ቢያንስ ለአንድ ሰዓት በጸሎት መንፈስ እንድትሆን የሚያደርግ አንድ ነገር ያስፈልግሃል። አንዳንዴ በካሴቱ ላይ ያለ መልዕክት በመንፈስ እንድትቀጥል ይገፋፋሃል! ሞክረው ዳግመኛ እንደነበርህ አትሆንም።

4. በሙዚቃ ድጋፍ ጸልይ

አውንም ባለ በገና አምጡልኝ አለ። ባለ በገናውም በደረደረ ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ መጣችበት።

2ኛ ነገሥት 3፡15

የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሙዚቃ ውብ የሆነ የአምልኮ አካባቢን ይፈጥራል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እጅ ብሎ ይጠራዋል። እኔ ሁል ጊዜ ስጸልይ ሙዚቃ ወይም የስብከት ካሴት አጫውታለሁ። ውድ ወዳጄ ይህ ያለንበት ዓለም ከባቢ አየር በአጋንንቶች ተሞልቷል። በአየር ላይ ያለው አለቃ እና ጭፍሮቹ የምንተነፍሰውን አየር በክለውታል። እንዲህ ባለ አካባቢ መጸለይ አስቸጋሪ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ለረጅም ሰዓት የማይጸልዩት በዚህ ምክንያት ነው። እየተንቀሳቀሱ ያሉት አስቸጋሪ በሆነ አካባቢ ነው።

ግን መልካም የምስራች አለ። ባለህበት ስፍራ የራስህን ትንሿን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማካሄድ ትችላለህ! በመኪናህ ውስጥ ሆነህ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊመጣብህ ይችላል። ይህ በእኔ ላይ ብዙ ጊዜ ሆኗል። መኪናዬን አንደ ጸሎት እልፍኝ አድርጌ ነው የምቆጥረው። የሚያስከፍልህን ዋጋ ከፍለህ ትክክለኛውን የጸሎት አካባቢ ፍጠር።

የተቀባ በገና በሚደረደርበት አካባቢ ስትቆይ የእግዚአብሔር መንፈስ በአንተ ላይ ይመጣል።

5. የስብከት ቪዲዮ እየተመለከትህ ጸልይ

አንዳንዴ፣ የስብከት ወይም የሙዚቃ ድምፅ በጸሎት መንፈስ ውስጥ ለመፍሰስ በቂ አይሆንም። አልፎ አልፎ ወደ ቪዲዮም መሄድ ያስፈልጋል። አንዳንዴ ለስኬታማ ጸሎት ትክክለኛውን የጸሎት አካባቢ ለመፍጠር ሁለቱም፡- ማየትና መስማት ያስፈልጋሉ። እኔ አብዛኛውን ጊዜ የስብከት ቪዲዮ እየተመለከትሁ እጸልያለሁ። በትክክለኛው ከባቢ አየር ውስጥ ስንቀሳቀስ ትልቅ ባርኮትን እቀበላለሁ።

6. የጸሎትህን 90% በልሳን ጸልይ

ልሳኖች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። ይህ ስጦታ አእምሮህ ያለ ሥራ ሆኖ እንድትጸልይ ይረዳሃል።

> በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14

ለሰዓታት በልሳን ስትጸልይ፣ መንፈስህ ይታነጻል ደግሞም በኃይል ይሞላል።

7. በምትጸልይበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ እና ሌሎች የክርስቲያን መጽሐፍትን አንብብ

ለረጅም ጊዜ በልሳን ስለምጸልይ፣ አእምሮዬ ለማንበብ ነፃ ነው። ረጅም ሰዓት በጸሎት ሳሳልፍ ሁል ጊዜ አነባለሁ። መንፈሴ ለእግዚአብሔር ሲጸልይ አእምሮዬ በማነበው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያተኩራል። ይህ ደግሞ እንዲያውም የበልጠ ሰዓት በጸሎት እንዳሳልፍ ረድቶኛል።

8. የስልክ መስመርህን አቋርጥ

ስልክ ሰይጣን ጸሎትህን ስማቂረጥ የሚጠቀምበት ምርጥ መሣሪያ ነው። በአእምሮህ ውስጥ አስፈላጊ የሆነ የስልክ ጥሪ ይኖረኛል የሚል ስሜት ስላለ፣ የስልክ

መስመርህን ለማቋረጥ አትችልም። አብዛኞቻችን የስልክ መስመራችንን መዝጋት አይሆንልንም።

አላስፈላጊ የሆኑ መቋረጦች ውድ የሆነ የጸሎት ጊዜአችንን በየአምስት ደቂቃ ወደ ተከፋፈለ የሠላሳ ደቂቃ ክፍለ ጊዜ ይሰባብረዋል። ይህ አጋጥሞህ እንደሆነ አላውቅም። ግን ልክ ከጌታ ጋር የጠለቀ ሕብረት ውስጥ ስገባ፣ ስልክ ይጮሃል! አንዳንዴ አላስፈላጊ የሆነ ጥሪ ያለ ሰዓቱ ሲመጣ ያማል።

በጸሎት ጊዜ ስልክ መስመሬን ለመቋረጥ ቆርጬ ወስኜአለሁ። ዓለም ሊቆይ ይችላል። ሁሉ ነገር ከጌታዬ ጋር ተነጋግሬ እስክጨርስ ሊቆይ ይችላል። ስልኬን ካላቋረጥሁ፣ ትርጉሙ አንድ ብቻ ነው፡- የጸሎት ጊዜዬን ከልቤ አልያዝሁትም ማለት ነው!

9. "መረበሽ ክልክል ነው" የሚል ማስታወቂያ አኑር

የምትኖረው በደሴት ላይ እስካልሆነ ድረስ፣ አብረሃቸው ከምትኖር ሰዎች ጋር መተባበር ያስፈልግሃል። ውጤታማ የጸሎት ሕይወት እንዲኖርህ ሰዎች የምትጸልይበትን ጊዜ ማወቅ ይኖርባቸዋል። ልክ በመታጠቢያ ክፍል ውስጥ ስትሆን እንደማይረብሹህ ሁሉ፣ በጸሎት ውስጥ በምትሆንበትም ጊዜ ሊረብሹህ አይገባም! ጓደኞችህ እና በቤት ውስጥ ያሉ ሰዎች በጸሎት ላይ እንደሆንህ እና መረበሽ እንደማይገባቸው እንዲያውቁ ለማድረግ እፍረት አይሰማህ።

ትምህርት ቤት በነበርሁበት ጊዜ፣ በአንድ ጓደኛዬ ጠንካራ፣ "መረበሽ ክልክል ነው" ማስታወቂያ ተመሰጥሁ። በክፍሉ በር ላይ ለሌሎች ተማሪዎች የለጠፈውን ማስታወቂያ ሁል ጊዜ አስታውሳለሁ። እንዲህ ይመስላል፡-

ማስታወቂያ

ይህንን በር አንኳኩተህ
ከውስጥ መልስ ካላገኘህ
ማንኳኳትህን እና እኔን መጣራት አትቀጥል
ይህን ቀላል መመሪያ የሚጻረር አንዳች ነገር ብታደርግ
ይህ በአንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን
ይህ በር ሊይከፈትልህም
ማንም ሁን ማ!!!

እንዲህ ያለ ማስታወቂያ በጣም መልካም ነው! በአንድ ወቅት በቤቱ ውስጥ ያሉትን ሠራተኞች ማስጠንቀቅ ነበረብኝ፡፡ እንዲህ ብዬ ነገርኳቸው፡- በምጸልይበት ጊዜ ቢጠሩኝ፣ ወዲያው እንደማባርራቸው ነገርኳቸው፡፡ ይህ በገዛ ቤቱ ውስጥ በነፃነት እንድጸልይ ትልቅ ነፃነት ሰጠኝ፡፡

ምዕራፍ 11

ምልጃን ለመረዳት የሚረዱ ሁለት እርምጃዎች

መማለድ የሚለው ቃል *ኢንተርሲደሪ (intercedere)* ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ነው። የዚህ ቃል ፍች *ጣልቃመግባት፣ በመሃል መግባት ወይም መካከለኛ* ማለት ነው።

> ሰውም እንደሌለ አየ፣ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፤ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት፣ ጽድቁም አገዘው።

ኢሳይያስ 59፡16

እግዚአብሔር ማንኛውንም አገልጋይ ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ በሚያቅደው እቅድ ላይ *ጣልቃ እንዲገባ* ጠርታል። ዛሬ ልንነሳና አዲስ የሆኑ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት በሚነሳው የአጋንንት ጭፍራ *መሃል መግባት* ይኖርብናል። የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያጠፋ በሚወጣ ማንኛውም የአጋንንት አጀንዳ ላይ *ጣልቃ መግባት* አለብን።

1. **መማለድ ማለት በመሃል በመግባት የነገሮችን ሁኔታ መለወጥ ማለት ነው**

የሰይጣን እቅድ የሰው ልጆችን ሁሉ ወደ ሲኦል መምራት ነው። በምልጃ ኃይል፣ ታሪክ እንለውጣለን። ወደ ሲኦል ሊወርዱ የሚገባቸው ሰዎች ይድናሉ። **ኃይለኛ የምልጃ ሰዎች የነገሮችን ሁኔታ ይለውጣሉ።**

2. **መማለድ ማለት በነገሮች መካከል መገኘት ማለት ነው**

እግዚአብሔር አገልጋዮችን ሁሉ የጠራው በሰይጣንና በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል እንዲገቡ ነው። **እረኛ የሚያደርገው ያንን ነው። በተኩላዎች እና በበጎች መካከል ይገባል።** ተኩላዎች እና ቀበሮዎች እረኛ ከመኖሩ የተነሳ በጎችን ማግኘት አይችሉም።

> **ቅጥርን የሚጠግንን፣ ምድሪቱንም እንዳላጠፋ በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፣ ነገር ግን አላገኘሁም።**
>
> **ሕዝቅኤል 22፡30**

መማለድ ማለት በክፍተት መካከል መቆም ማለት ነው። *ያ* ማለት በሰይጣንና በወኪሎቹ ላይ እንቅፋት መሆን ማለት ነው። ውድ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ መልካም ሥራ እየሠራህ ነው። ውድ የወንጌል መልዕክተኛ(ሚሲዮናዊ)፣ ያንተ ባለህበት ሕዝብ መካከል መገኘት ማለት ለብዙ ነፍሳት የማምለጫ አለት መሆን ማለት ነው። ተስፋ አትቁረጥ! በመልካም ሥራህ ግፋበት! እግዚአብሔር ለሰጠህ ሰዎች ጸልይ! *ለንተ ውድ በሆኑት ነፍሳት እና በጠላት መካከል የመጨረሻው ገደብ ነህ።*

ምዕራፍ 12

ለእያንዳንዱ መጋቢ የሚማልድለት ሰው የሚያስፈልግበት ሃያ ምክንያቶች

ምልጃ የሚሠራውን ነገር ስትረዳ፣ ለአገልጋዮች መጸለይህን በፍፁም አታቆምም። የዚህ ምድር ኑሮአችን ሁል ጊዜ ስጋት የተሞላበት ነው። ምንም እንኳ ባንረዳው፣ ከብዙ አቅጣጫ በአደጋ ውስጥ ነን። ምልጃ በአንተ እና በእነኚያ አደጋዎች መካከል ያግዳል። ደካሞች ከመሆናችን የተነሳ አናስተውለውም!

አስታውስ መማለድ ማለት *በመሃል መግባት፣ ጣልቃ መግባት ወይም መካከለኛ መሆን* ማለት ነው። መማለድ ማለት በመሃል መግባት እና *ነገሮችን መለወጥ ማለት ነው።* የሚማልድ ሰው *በነገሮች መካከል ይገባል።*

ጳውሎስ እንደ አገልጋይ ያለፈባቸውን አደጋዎች ሲዘረዝር፣ በእርግጥ ምልጃ የሚስፈልጋቸውን ነገሮች ነው የዘረዘረው።

> የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ እብድ ሰው እላለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ **በድካም** አብዝቼ፣ **በመታሰር** አትርፌ፣ **በመሞት** ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ **አንድ ሲጎድል** **አርባ** **ግርፋት** አምስት ጊዜ **ገረፉኝ**። ሦስት ጊዜ **በበትር** **ተመታሁ**፤ አንድ ጊዜ **በድንጋይ** **ተወገርሁ**፤ መርከቤ **ሦስት** **ጊዜ** **ተሰበረ**፤ ሌሊትና ቀን **በባሕር**

ውስጥ ኖርሁ፡፡ ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፣ በወንበዴዎች ፍርሃት፣ በወገኔ በኩል ፍርሃት በምድረ በዳ ፍርሃት፣ በባህር ፍርሃት፣ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፣ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ፡፡ የሚደክም ማን ነው፣ እኔም አልደክምምን? የሚሰናከል ማን ነው፣ እኔም አልናደድምን?

2ኛ ቆሮንቶስ ፲፡23-27,29

ጳውሎስ ያለፈባቸው እነኚህ ሃያ አደጋዎች በእርግጥም እያንዳንዱ አገልጋይ ጸሎት እንዲያስፈልገው የሚያደርጉ ሃያ ምክንያቶች ናቸው፡፡

አንድ ሐዋርያ የሚያጋጥሙት ሃያ አደጋዎች

1. አብዝቶ መድከም (የረጅም ሠዓት ሥራ)
2. ብዙ ጊዜ መገረፍ (ከአቅም በላይ የሆነ የአካል ጉዳት)
3. በተደጋጋሚ መታሰር (የፖለቲካ እና የመንግሥት ግፊት (ተዕዕኖ))
4. ለሞት መቃረብ (ለመሞት የተቃረበ ገጠመኝ)
5. ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው (በተለየ ሁኔታ በግል የሚደርስ ማስፈራሪያ)
6. በዱላ መደብደብ (ቁሻሻ ሲወረወርብህ)
7. አንድ ጊዜ በድንጋይ መወገር (ከሕዝብ የሚሰነዘር ጥቃት፣ አጥር ማፈራረስ እና ፖለቲካዊ ጥላቻ)
8. ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ (የመኪና፣ የባቡር እና የአውሮፕላን መከስከስ አደጋ)
9. በባህር ውስጥ (የመስጠም አደጋ)
10. ብዙ ጊዜ መንገዝ (በጉዞ ላይ የሚያጋጥም አደጋ)
11. በወንዝ ፍርሃት (ያልለመድከውን ነገር የመመገብ እና የመጠጣት አደጋ)

12. የወንበዴዎች አደጋ (የቤተ ክርስቲያን ንብረት፣ መባ፣ ሞባይል ስልክ ወዘተ ስርቆት)
13. ከተማ ውስጥ አደጋ (የዝሙት አዳሪ፣ የሥነ ምግባር ብልሹነት፣ የአጭበርባሪዎች፣ የታጠቁ ዘራፊዎች)
14. የምድረ በዳ አደጋ (የውጭ አገር ዜጋ በመሆን የሚያጋጥም አደጋ)
15. የባሕር አደጋ (ተጓዥ አገልጋይ በመሆን የሚደርሱ አደጋዎች)
16. ከሐሰተኞ ወንድሞች የሚደርስ አደጋ (በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰላዮች፣ በየሥፍራው ሁሉ ያሉ ስለላ ሠራተኞች፣ ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች)
17. የረሃብ አደጋ (ለምግብ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ማጣት)
18. የመጠማት አደጋ (ለመጠጥ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ማጣት)
19. በብርድ ውስጥ (በቂ ሙቀት ማግኘት አለመቻል፣ በኢንፌክሽን የመያዝ አደጋ)
20. የመታረዝ አደጋ (በቂ ልብስ አለማግኘት፣ የክረምት ልብስ ወዘተ)

ምዕራፍ 13

የዝቅጠትን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ሰዎች የሚማልድላቸው ሰው ማስፈለግ ሁል ጊዜ ግልጽ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ የሰዎችን ክፍተት በመሙላት የሚቆሙ ሰዎች ሁልጊዜ አሉ። አብዛኛውን ጊዜ ምልጃ ክርስቲያኖችን *ከሰይጣን* ጥቃት መከላከል ብቻ እንደሆነ አድርገን እናስባለን። ምልጃ ግን ከዚያ የበለጠ ነገርን ያደርጋል። ምልጃ ዛሬ በምድር ላይ የሚሰለጥኑ ሕጎችን ይቃወማል። እነኚህን ነገሮች ስትረዳ ለቤተ ክርስቲያን አባሎችህ ሁል ጊዜ መጸለይ ትፈልጋለህ።

አሁንም እንደገና የምልጃን ትርጉም አስታውስ፡- መማለድ ማለት *በመሃል መግባት፤ ጣልቃ መግባት ወይም መከከለኛ መሆን* ማለት ነው። መማለድ ማለት በመሃል መግባት እና *ነገሮችን መለወጥ ማለት* ነው።

ምልጃ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የመበላሸት ሕግ ይቃወማል

እኔ የተመረጠች ወይን ፍጹምም እውነተኛ ዘር አድርጌ ተክዬሽ ነበር፤ አንቺ ግን ክፉ የእንግዳ ወይን ግንድ ሆነሽ እንዴት ተስወጥሽብኝ?

ኤርሚያስ 2፡21

ወደድንም ጠላንም፣ ዛሬ በምድር ላይ የመዝቀጥ ሕግ በሥራ ላይ ይገኛል። ማንኛውም የፈጠርነው ነገር ልክ ሥራው ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ መበስበስ ይጀምራ። ህንፃ ሁሉ ዕድሜው በጨመረ ቁጥር ቀስ በቀስ እየተበላሸ ይሄዳል። ከአሥር ዓመት በፊት የተነሳኸውን ፎቶ ግራፍ ተመልከት እና ምን እየተናገርሁ እንደሆን ይገባሀል። ሀብት አንድ ሥፍራ ለዘላለም አይቆይም። ምናልባት ዛሬ ሀብታም ትሆን ይሆናል ከአሥር ዓመት በኋላ ግን ሀብትህ ምንም ወደ አለመሆን ይዘቅጥ ይሆናል። ከዓመታት በፊት በጣም የበለጸጉ ከተሞች ነበሩ። ዛሬ፣ እነኚያ ቦታዎች ወደ ትልቅ ቆሻሻ ሰፈርነት ዘቅጠዋል።

መዝቀጥ ማለት ቀስ በቀስ ደረጃን(ጥራትን) መቀነስ ማለት ነው። ቀስ በቀስ ወደ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ መውረድ ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያንም ልዩነት የላትም። ሁላችንም ያለነው በመዝቀጥ ሕግ ስር ነው። ለዚህ ነው እረኞች የመንጋቸውን ሁኔታ እንዲያጤኑ የሚመከረው። አንድን ንቁ የሆነ የክርስቲያኖች ሕብረት ተጨማሪ ጥረት ሳታደርግ ለሦስት ዓመት ብትተወው፣ ይበሰብሳል። መንፈሳዊ ጥረት ልታፈስበት ይገባል!

በጎችህ በምን ሁኔታ እንዳሉ ደህና አድርገህ ዕወቅ፤ መንጋህንም ተንከባከብ፣ ሀብት ለዘላለም አይኖርምና፤ ዘውድም ከትውልድ ወደ ትውልድ ጸንቶ አይኖርም።

ምሳሌ 27፡ 23-24

የቤተ ክርስቲያን መዝቀጥ እንዲህ ሊተረጎም ይችላል፡፡ *“ቀድሞ ከነበረበት ትክክለኛ ሁኔታ ወይም ባህሪ መውረድ”፡፡ መዝቀጥ ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ ማሽቆልቆል ማለት ነው፡፡* ይህ የዝቅጠት ሕግ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እና በአባላቶችህ ውስጥ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ሁላችንንም ይነካናል፡፡ ለዚህ ነው ለሕዝብህ መማለድ የሚገባህ፡፡ የዝቅጠት ሕግ ቀናተኛ የነበረውን ቅንዓት እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡ የዝቅጠት ሕግ ጣፋጭ የሆነ የጸሎት ሕይወት ባላቸው ክርስቲያኖች ላይ ይሠራል፡፡ ለጸሎት ያላቸውን ፍላጎት እንዲያጡ ያደርጋቸዋል፡፡ የዝቅጠት ሕግ ቅዱስ የሆኑ ክርስቲያኖችን ይቃወማቸዋል፡፡ እያበላሻቸው ወደ ምግባር ብልሹ የሆነ ዓለማዊነት እየመራቸው ነው፡፡ ውድ መጋቢ ከዚህ በኋላ ልትተኛ አትችልም፡፡ የዝቅጠት ሕግ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እየሠራ ነው፡፡ ልትነሳ እና ልትማልድ ይገባሃል!

ሰዎች በክርስትና ሕይወታቸው ጅማሬ ላይ ያላቸውን የመመስከር እና ቃሉን የመስበክ ቅንዓት አስተውለሃል? ብዙም ሳይቆይ፣ አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አታገኛቸውም፡፡ ምን ተፈጠረ? የዝቅጠት ሕግ!

ለዚህ ነው ምልጃ እና ጸሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕያው እንዲሆን በጣም የሚያስፈልገው!

ምዕራፍ 14

የዓለምን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የዓለምን ሕግ ይቃወማል

ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም **በዓለም** ያለው ሁሉ፦ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም። **ዓለምና** ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል።

1ኛ ዮሐንስ 2፡ 15-17

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ዓለም ቤተ ክርስቲያንን የሚበክል ተጽዕኖ አለው። ቤተ ክርስቲያን በአብዛኛው ዓለማዊና ሥጋዊ ሆናለች። ይህ የሆነበት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በዓለም መካከል ስለሆነ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ዓለማዊ እንዳትሆን ምልጃ መቀጠል አለበት። በዓለም ያሉ የሥጋ ምኞት እና የዓይን አምሮት ሳናውቀው ራሳቸውን ከአገልጋዮች ጋር አጣብቀዋል።

ሰው ማላጅ ያስፈልገዋል! ዴማስ ማላጅ ያስፈልገው ነበር። በዓለም ፍቅር ወድቆ ከእምነት አፈገፈገ። ስቤተ ክርስቲያን አባሎቻችን ስንማልድ ጥቂቶች ብቻ ከእምነት ያፈገፍጋሉ። ምልጃ የዓለምን ሕግ ይቃወማል።

ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና . . . 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡10

ምዕራፍ 15

የሥጋን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የሥጋን ሕግ ይቃወማል

አው ማላጅ ያስፈልገዋል! የሥጋ ሕግ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር ሁሉ ይቃወማል። ጳውሎስ የራሱን ሥጋ ይፈራ ነበር። በሥጋዬ አንዳች መልካም ነገር እንደሌለ አውቃለሁ ሲል ተናገረ።

> በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፣ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም
>
> ሮሜ 7፡18

በአንድ ወቅት፣ ጳውሎስ በሥጋው እንደማይታመን ገልጿል።

> እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና
>
> ፊልጵስዮስ 3፡3

ውድ ወዳጄ፡- ጳውሎስ በሥጋው ካልታመነ፣ እኛ ምን ልናደርግ ይገባናል? ሥጋ ወደ ሲኦል ሊወስድህ ዝግጁ ነው። ሥጋ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት እየተቃወመ ነው። ሥጋ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና እየተቃወመ ነው። ሥጋ መንፈሳዊ እድገትህን እየተቃወመ ነው።

ሥጋ የቤተ ክርስቲያን አባላት መልካም ያልሆነውን እንዲመኙ እና ክፉ እንዲያደርጉ እያደረገ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላትን የሚያሰንፍ ሥጋ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች እሁድ እሁድ ቤተ ክርስቲያን እንዳይመጡ የሚያደርገው የሥጋ ነገር ነው። አንድ መጋቢ በጌታ ልጆቹ ስለሆኑ ሲያስብ፣ ልቡ በምልጃ ጸሎት ሊቃጠል ይገባዋል። *አባት ሆይ፣ ልጆችህን እርዳ! በመንገድ ዳር እንዲወድቁ አታድርግ።*

> ነገር ግን ለሌሎች ከሰበኩሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።

1ኛ ቆሮንቶስ 9፡27

ሌላው ምልጃ የሚስፈልግበት ጉዳይ ሕመም እና በሽታ ነው። የምልጃ ጸሎት በሽታ በሰዎች ላይ እንዳይጣበቅ ይከላከላል። አስታውስ፣ በበሽታ ከተጠቁ በኋላ ከመታከም አስቀድሞ መጠንቀቅ ይሻላል። የምልጃ ጸሎት መጋቢዎች አላስፈላጊ ከሆነ የቀብር ሥርዓት ማስፈጸም ይከላከልላቸዋል።

ምዕራፍ 16

የተፈጥሮ ክስተቶችን በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የተፈጥሮ ክስተቶችን ይቃወማል

የተፈጥሮ ክስተቶች የምንላቸው ምንድር ናቸው? የተፈጥሮ ክስተቶች መሬት፣ ነፋስ፣ እሳት፣ እና ውሃ ናቸው። አወቅህም አላወቅህም፣ እነኚህ ክስተቶች በህልውናህ ላይ ሊመጡ ይችላሉ። እነኚህ ነገሮች አደጋ እንዳያመጡ መማለድ እንችላለን። የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት አገልግሎትህ ሊያከትም ይችላል። የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሳት፣ የውሃ መጥለቅለቅ ወይም አውሎ ንፋስ ሲከሰት የሚሆነው ይህ ነው።

በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ጊዜ፣ የተፈጥሮ ክስተቶችን መቃወም ነበረበት። እነኚህ ክስተቶች ሕይወቱን እና አገልግሎቱን ከፍፃሜ ለማድረስ ሞክረው ነበር።

> ወደ ታንኳም ሲገባ ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት። እነሆም፣ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ጌታ ሆይ አድነን፣ ጠፋን እያሉ አስነሱት። እርሱም፦ እናንተ እምነት የጎደላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ? አላቸው ከዚህ በኋላ ተነስቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፣ ታላቅ ጸጥታም ሆነ። ሰዎቹም፦ ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፣ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ።
>
> ማቴዎስ 8፡23-27

ደቀ መዛሙርቱ የተፈጥሮ ክስተቶች እንዴት ለጸሎት ትዕዛዝ መልስ እንደሰጡ በማየታቸው ተደንቀው ነበር። ለሕዝብህ ስትማልድ፣ በምድር ውስጥ ካሉ ተቃራኒ ነገሮች ይጠበቃሉ። አንዳድ ጊዜ አውሮፕላን መከስከስ፣ የመኪና መገልበጥ እና ሌሎች ጥፋቶች ሁሉ በእነኚህ የተፈጥሮ ክስተቶች ሊመጡ ይችላሉ። ለሕዝብህ በምልጃ መንፈስ ስትነሳ ይታየኛል! አገልግሎትህ የተለወጠ ይሆናል።

ምዕራፍ 17

የሰውን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የሰውን ሕግ ይቃወማል

የሰው ሕግ የሰውን ተፈጥሮ የሚመለከት ነው። እዚህ ሁለት ዋነኛ ነገሮች ላይ እናተኩራለን።

ሀ. የሰው ተፈጥሮአዊ እውነታ

ለ. የሰው ስህተት እውነታ

የሰው ተፈጥሮ የተደረገለትን መርሳት፣ መዘንጋት እና ክፋት መሆኑ በደንብ ይታወቃል። እውነተኛ ጦርነት ሲካሄድ ለማየት የሩቅ ተመልካች መሆን አይጠበቅብህም። የሰው ክፋት ለሁሉም የተገለጠ ነው። ዘርን ማጥፋት እና የጭካኔ ግድያዎች ማረጋገጫዎች ናቸው።

ኢየሱስ የሰው ልጆች እንዴት ፊታቸውን ሊያዞሩበት እንደሚችሉ ያውቅ ነበር።

> ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።
>
> **ዮሐንስ 2፡24-25**

የሰው ሞገደኛ ተፈጥሮ በክርስቶስ ላይ ሲነሳ፣ የሠራቸው ተአምራቶች ሁሉ ትርጉም የለሽ ሆኑ። በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ገደሉት። በሰው ውስጥ ያለውን ክፋት አትናቅ።

የምልጃ ጸሎታችን በአገልግሎታችን ውስጥ ያለውን የሰው ሞገደኛ ምስጋና ቢስነት እና ዝንጉነት ይቃወማል። ውድ መጋቢ ለምዕመኑ በምትጸልይበት ጊዜ፣ የሰጠሃቸውን ፍቅር እንዳይዘነጉ ይረዳቸዋል።

የሰው ስህተት አብዛኛውን ጊዜ እንደ ታይታኒክ መስጠም፣ ወይም በለንደን ፓዲንግቶን የባቡር አደጋ ወይም የኮንኮርድ ጥፋት የመሳሰሉትን የሰው እልቂት ያመጣል። የምልጃ ጸሎት የሰው ስህተት ከሚያመጣው ጥፋት ጣልቃ በመግባት ያድንሃል።

ዶክተር እንደመሆኔ፣ ሌሎች ዶክተሮች ስህተት ሲፈጽሙ አይቼአለሁ። በሰው ስህተት ምክንያት ሰዎች ሲሞቱ አይቼአለሁ። በአንድ ወቅት የማህጸን ሕክምና አማካሪ በአሥራ አንድ ዓመት ልጃገረድ ላይ (Laparotomy) ከፍተኛ ቀዶ ጥገና ሲያካሂድ አይቼአለሁ። በሆዷ የታችኛው ክፍል ዕጢ ያለባት መስሎት ነበር። ከከፈቷት በኋላ በውስጧ ያለው በትልቁ አንጀቷ ውስጥ የደረቀ ሰገራ ብቻ ነበር። ይህች ሚስኪን ልጃገረድ ዶክተሩ በትክክል ሳይመረምራት በመቅረቱ ምክንያት ከፍተኛ ቀዶ ጥገና ተካሄደባት። የሚያስፈልጋት ግን ወደ መጸዳጃ ቤት እንድትሄድ የሚያደርጋት መድሃኒት ብቻ ነበር!

ሌሎች በሽተኞች ደግሞ የቀዶ ጥገና ባለሙያዎች ፋሻ ወይም መቀስ በሆዳቸው ውስጥ ረስተው በመስፋታቸው ምክንያት ሞተዋል። መድኃኒት ከመሰጠቱ በፊት እንኳ የሰውን ስህተት በመቃወም (በመከላከል) የምልጃ ጸሎት ያስፈልጋል። ለዚህ ነው ሰዎች ማንኛውንም ዓይነት ሕክምና ሲቀበሉ የምንጸልየው።

በአንድ ወቅት ከሲኦል በረራዎች (Flights from hell) የሚል ጥናታዊ ፊልም አይቼ ነበር። በዚህ ጥናታዊ ፊልም፣ አብራሪው ጎማው እንደማይዘረጋ ተገነዘበ። ይህ የሆነበት ምክንያት አንድ ሰው (የሰው ስህተት) የጎማውን ታኮ ማውጣት ዘንግቶ ስለነበር ነው። በፊልሙ ላይ አውሮፕላኑ ጎማው እንዲወጣ አስደናቂ መገለባበጥ ሙከራዎች አደረገ። በመጨረሻ፣ አውሮፕላኑ በአንድ ጎማ ብቻ ለማረፍ ተገደደ። በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ዕድላቸው ሆኖ ለመትረፍ ቻሉ።

በዚሁ ከሲኦል በረራዎች (Flights from hell) ጥናታዊ ፊልም፣ ከቦጎታ፣ ኮሎምቢያ ወደ ኒው ዮርክ ከተማ የተደረገ በረራ ነበር። አብራሪው ኒው ዮርክ ሲደርስ፣ ለማረፍ ተራው እስኪደርስ በአየር ላይ እያንጎበጎበ እንዲቆይ ተጠየቀ። ለአንድ ሰዓት ያህል በአየር ላይ መቆየት ግድ ሆነበት። የዚህ ታሪክ አሳዛኝ ሁኔታ አብራሪው ነዳጅ እንዳለቀበት እና ፈጥኖ ማረፍ እንደሚገባው ለበረራ ትራፊክ ሠራተኞቹ መግለፅ መዘንጋቱ ነበር።

ይህ አብራሪ *ጠብታ ነዳጅ* እስኪሟጠጥ ድረስ ተሽከርክሮ በመጨረሻ ልክ ከአውሮፕላን ማረፊያው አጠገብ እንደተከሰከሰ ማመን ትችላለህ? አውሮፕላኑ ነዳጅ አልቆበት ተከሰከሰ ሲባል ሰምቶ የሚያውቅ አለ? በመጨረሻም የአደጋው መንስኤ ሲጣራ አብራሪው ነዳጅ እንዳለቀበት ለአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች መግለፅ መዘንጋቱ (የሰው ስህተት) ተደረሰበት። እውነቴን ነው የምልህ፣ በዚያ አውሮፕላን ውስጥ የነበሩ መንገደኞች ከፍተኛ ምልጃ ጸሎት ያስፈልጋቸው ነበር። መንገደኞቹ በጣም አደገኛ በሆነ ሰው እጅ ነበሩ።

የምልጃ ጸሎት ሰዎችን *ከሰው ስህተት* እና *ከሰው ተፈጥሮ* መካከል በመግባት ይጠበቃል።

ምዕራፍ 18

የተፈጥሮ ሕግን በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የተፈጥሮ ሕግን ይቃወማል

ተፈጥሮ ሲቃወምህ፣ ራስህን ስትታገል (ላብህን ስታፈስ) ታገኘዋለህ! ተፈጥሮ ስለ ምድር ወቅቶችና ዑደት የሚናገር ነው። ተፈጥሮ እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ነገሮች የሚያሳይ ነው። የተፈጥሮ ዑደቶች ሲዛቡ ብዙ ዓይነት ችግሮች ይፈጠራሉ። ለምሳሌ ያህል ድርቅ፣ ረሀብ፣ የውሃ መጥለቅለቅ እና አውሎ ነፋስ ናቸው። እነኚህ ነገሮች የሚከሰቱት የተፈጥሮ ዑደቶች ሲዛቡ ነው። ተፈጥሮአዊው የባህር ሞገድ ሲበዛ ማዕበል ይነሳል።

ባህር ውስጥ ገብተህ ማዕበል ከተነሳ፣ በተፈጥሮ እጅ ገባህ ማለት **ነው። የዱር እንስሳት፣ ነፍሳት፣ ቫይረሶች፣ ባክቴሪያዎች እና ጥገኛ ህዋሳት ተፈጥሮ በሰው ላይ ፊቱን የሚያዞርበት ሁኔታዎች መገለጫ ናቸው።**

በአንድ ወቅት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ተፈጥሮን በመጎብኘት ላይ ነበርሁ። በፓርኩ ውስጥ ሁሉም ዓይነት የዱር እንስሳት ነበሩ። ከመኪና ወርዶ በእግር መጎብኘት ይቻል እንደሆን አስጎኚአችንን ጠየቅኹት።

እንዲህ አለኝ፣ “ማድረግ የለብህም!”

ልብ በል፣ በፓርክ ውስጥ በእግሬ ብሄድ ኖሮ፣ የዱር እንስሳቱ ከማርኩህ አይማረኝ ይሉኝ ነበር። ራሴን ለተፈጥሮ አደጋ አጋልጥ ነበር። መዝሙረኛው ተፈጥሮ ስትረዳ እንዴት ያለ ባርኮት እንደሆን ያስተምራል። በጌታ ቃል በሚራመድ ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ዑደቶችና ወቅቶች በትክክል እንደሚሠሩለት ይተነቢያል። አንዲት ሴት መውለድ ሲያቅታት፣ የተፈጥሮ ሂደት ተቋርጧል ማለት ነው።

> ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፤ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፣ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፣ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል። እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች፣ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።
>
> መዝሙር 1፡1-3

ባክቴሪያ እና ቫይረስ ኢንፌክሽኖች ተጨማሪ የተፈጥሮ መዛባቶች ናቸው። ባክቴሪያ፣ በሌላ አገላለፅ፣ በዓይን ሊታዩ የማይችሉ እና ሊገድሉህ የሚችሉ የዱር እንስሳት ናቸው። ድንበርህን አቋርጠው ከገቡ፣ ተፈጥሮ ፊቱን አዞረብህ ማለት ነው።

ምልጃ ተፈጥሮ እንዳያጠፋህ ሊከላከልልህ ይገባል። የምልጃ ጸሎት ሰዎች “የተፈጥሮ ሞት” ብለው የሚጠሩትን እንኳ ሊያቆም ይችላል። የምልጃ ጸሎት ሰዎችን ወደ ቃሉ በመምራት በመዝሙር አንድ ላይ የሚገኘውን በረከት እንዲያገኙ ያደርጋል።

አንድ ሰው እግዚአብሔራዊ ባልሆነ መንገድ ሲመላለስ፣ በተፈጥሮ እጅ ላይ ይወድቃል፣ ተፈጥሮም እንደ ትቢያ ይበትነዋል። ይህን ጥቅስ ራስህ አንብበው!

> ክፉዎች እንዲህ አይደሉም፣ ነገር ግን **ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው** ትቢያ ናቸው።
>
> መዝሙር 1፡4

ምዕራፍ 19

የሰይጣንን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የሰይጣንን ሕግ ይቋቋማል

የሰይጣን ሕግ ሰይጣን በውጭ እንዳለ ያስተምራል። ይህ ሰይጣን እና ወኪሎቹ ሕይወታችንን በመቃወም በፈጣን ሁኔታ እየሠሩ ነው። ሰይጣንን ሁለት ጊዜ አይቼዋለሁ! በሁለቱም ገጠመኞች ሊያጠፋኝ ሲሞክር ነበር። ድንገት ዓይኔ ተገለጠና ጠላቴን በግልፅ ማየት ቻልሁ። በሜቆዶኒያ በጳውሎስ ላይ የሆነው ይኸው ነበር።

ለበርካታ ቀናት በአጋንንቶች እንግልት ደርሶበት ነበር። ድንገት ጌታ መናፍስትን የመለየት ስጦታ ሰጠው። ይህ ደግሞ ምን እየሆነ እንደሆን እንዲያውቅ ረዳው። አጋንንቱንም በማስወጣት እንግልቱ እንዲቆም አደረ።

> ወደ ጸሎት ስፍራም ስንሄድ፣ የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት ለጌቶችዋም እየጠነቆለች ብዙ ትርፍ ታመጣ የነበረች አንዲት ገረድ አገኘችን። እርስዋ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች፦ የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው ብላ ትጮኽ ነበር። ይህንም እጅግ ቀን አደረገች ጳውሎስ ግን ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን፦ ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዛለሁ አለው፤ በዚያም ሰዓት ወጣ።
>
> የሐዋርያት ሥራ 16፡16-18

ሰይጣንን አይቼዋለሁ

መናፍስትን የመለየት መገለጥ በመጣልኝ በሁለቱም ጊዜዎች፣ ሰይጣን በቀኝ ጎኔ ነበር። በአንደኛው ሁኔታ፣ ሰይጣን በትንሽ ጦጣ ተመስሎ አልጋዬ ጎን በነበረ ጠረጴዛ ላይ አየሁት፣ ሰይጣን የዚህን ያህል ቀርቦ በማየቴ በጣም ተደንቄ ነበር! ድንገት ይህ ሊያጠፋኝ የመጣን ነገር ልቃወም ቻልሁ። ያንን አጋንንት ልቃወም ባልችል ኑሮ ዛሬ በሕይወት ባልኖርሁ ነበር።

ሰይጣንን በድጋሚ አየሁት

በሌላ ገጠመኝ፣ ዓይኖቼ ለመንፈሳዊው ዓለም ተገለጡና ስምንት ጫማ ርዝመት፣ ጥቀርሻ የመሰለ ነገር በአልጋዬ ቀኝ ተንጠላጥሎ አየሁ። ተደናግጬ ከአልጋዬ ዘልዬ በመውረድ መጸለይ ጀመርሁ። ጌታም በድንገት በአገልግሎቴ ውስጥ ያሳለፍኩትን ከባድ እና ረጅም ጥቃት ምን ይመስል እንደነበር አሳየኝ።

በእነዚሁ ሁለት ገጠመኞች፣ ሰይጣን ሊያጠፋኝ በጣም ተቃርቦ ነበር። በመጋቢዎች ላይ የሚሆነው ይህ ነው። ለዚህ ነው መጋቢዎች በጸሎት የሚማልዱላቸው ሰዎች የሚስፈልጓቸው።

በቤተ ክርስቲያን አባላቶችህ ላይ እየሆነ ያለው ይኸው ነው። ጠላት ነፍሳቸውን እየፈለገ ነው። ማልድላቸው! በሁኔታዎች ላይ ማልድ! ውጣና በሰይጣን እና እግዚአብሔር በሰጠህ በጎች መካከል ግባ! አገልግሎትህን በምልጃ ጸሎት ለውጥ።

ምዕራፍ 20

የጊዜን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ "የጊዜን" ሕግ ይቋቋማል

ለሁሉ ዘመን አለው፣ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው። ለመወለድ ጊዜ አለው፣ ለመሞትም ጊዜ አለው፣ ለመትከል ጊዜ አለው፣ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው። ለመግደል ጊዜ አለው፣ ለመፈወስም ጊዜ አለው፣ ለማፍረስ ጊዜ አለው፣ ለመሥራት ጊዜ አለው፣ ለመሳቅም ጊዜ አለው፣ ዋይ ለማለት ጊዜ አለው፣ ለመዝፈን ጊዜ አለው፣ ለማልቀስም ጊዜ አለው ድንጋይንም ለመሰብሰብ ጊዜ አለው፣ ድንጋይን ለመጣል ጊዜ አለው ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፣ ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለው ለመፈለግ ጊዜ አለው ለማጥፋትም ጊዜ አለው፣ ለመጠበቅ ጊዜ አለው፣ ለመጣልም ጊዜ አለው፣ ለመቅደድ ጊዜ አለው፣ ለመስፋትም ጊዜ አለው፣ ዝም ለማለት ጊዜ አለው፣ ለመናገር ጊዜ አለው፣ ለመውደድ ጊዜ አለው፣ ለመጥላትም ጊዜ አለው፣ ለጦርነት ጊዜ አለው፣ ለሰላምም ጊዜ አለው።

መክብብ 3፡1-8

የጊዜ ሕግ ለሁሉ ነገር ጊዜ እንዳለው ያስተምረናል። በሕይወትህ ውስጥ የምትዘራበትም የምታጭድበትም ጊዜ ይኖራል። የደስታም ጊዜ ይኖራል የሀዘንም ጊዜ ይኖራል። ከፍ የምትልበትም ጊዜ ይኖራል፣ ዝቅ የምትልበትም

ጊዜ ይኖራል! ሁኔታዎች በሕይወትህ ውስጥ በሚከሰቱበት ጊዜ ያንን ወቅት ትቋቋመው ይሆን? የምትበለጽግበት ጊዜ ሲመጣ፣ ወደ ዓለም ትመለሳለህ ወይስ በጌታ ትጸናለህ? የእስራኤል ልጆች በሚበለጽጉበት ጊዜ እንዲጠነቀቁ ተነግሮአቸው ነበር። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን እንዳይረሱ ሙሴ አስጠንቅቋቸው ነበር። ባጭሩ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ወደ አዲስ ዘመን ውስጥ ስለሚገቡ ምልጃ ያስፈልጋቸዋል።

ብዙ ሰዎች በሚበለጽጉበት ጊዜ ይወድቃሉ። መጋቢዎች በመንፈስ ያላደጉ ልጆች ወይም(በጎች) በፈተናቸው ጊዜ እንዳይወድቁ ለጉባኤው መጸለይ አለባቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክፉ ቀን ይናገራል። ክፉ ቀን ማለት ነገሮች በጎ የማይሆኑበት ቀን ነው። ለአማኞች መማለድ በክፉ ቀን እንዲጸኑ ይረዳቸዋል።

> ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።

ኤፌሶን 6፡13

ለሕዝብህ የማትጸልይ ከሆነ፣ ወደ ክፉ ቀን ሲገቡ ይወድቃሉ! ለበጎች ያለማቋረጥ መማለድ የመጋቢዎችና የእረኞች ኃላፊነት ነው። **እያንዳንዱ በግ ያለው በሕይወቱ አንድ የተለየ ወቅት ውስጥ ነው።** እግዚአብሔር ለሕዝብህ እንድትጸልይ ይጠብቅብሃል ምክንቱም ሁሉም በተለያየ የሕይወት ገጠመኝ ውስጥ ነው ያለው።

አንዳንድ ሰዎች በፈተና እና በሞት ጊዜ ውስጥ ነው ያሉት። አንተ ካልማለድህላቸው በቀር ጸንተው የመቆም እድል የላቸውም!

ምዕራፍ 21

የሚያደቡ ነገሮችን በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የሚያደቡ ነገሮችን ሕግ ይቋቋማል

እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፤ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፤ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ፡፡ እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ አምሳላችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፤ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፤ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ፡፡

ዘፍጥረት 1፡25-26

የሚያደቡ ነገሮች ምንድር ናቸው? የሚያደቡ ነገሮች ሳታውቀው ሹልክ ብሎ የሚወጣብህ ነገር ነው፡፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ በእግዚአብሔር ስለተፈጠሩ የተለያዩ ፍጥረቶች ይናገራል፡፡ አንደኛው የፍጥረት መደብ የምድር ተንቀሳቃሾች ነው፡፡

በመንፈሳዊ አነጋገር፣ በቀስታ በላያችን ላይ የሚወጡ ነገሮች አሉ። በረጅም ጊዜ ውስጥ ታላቅ ለውጦች ይካሄዳሉ። ብዙ ሰዎች እነዚህ ለውጦች ሲካሄዱ በሚገባ አያስተውሉም።

በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደቡ አራት ነገሮችን ልስጥህ።

ሀ. መሳት (ምሳሌ፡- የአውሮፓ ቤተ ክርስቲያናት)

ለ. ትክክለኛ ያልሆነ ዝንባሌ (ምሳሌ፡- ስንፍና በራስ መደሰት እና አለማመን)

ሐ. መላመድ (ምሳሌ፡- በመካከልህ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ስጦታ አለማድነቅ)

መ. ቅደም ተከተልን ማዛባት (ምሳሌ፡- የወንጌል መልዕክተኞች ከመሆን ይልቅ የጤና እና የትምህርት ተቋም መሆን)

መሳት የሚያደባ ነገር ነው

የአውሮፓ ቤተ ክርስትያን እንዴት ከንቁ የወንጌል መልዕክተኝነት አስተሳሰብ ካለው ማኅበረሰብነት ወደ እግዚአብሔርን የካደ እና አምላክ የለሽ ድርጅትነት ተለወጠች? በአንድ ሌሊት አልሆነም። የመሳት መንፈስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የወጣው ቀስ በቀስ ነው። መሳት ቀስ እያለ የሚሳብ ነገር ነው።

መላመድ አድብተው ቤተ ክርስቲያንን ከሚወሩ በጣም አደገኛ ነገሮች አንደኛው ነው። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ባለማስተዋል ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን መጋቢ በክብር አይዙም። በእርግጥ፣ እናደርጋለን ይላሉ፣ ግን በተጨባጭ አያደርጉትም!

መላመድ የሚያደባ ነገር ነው

መላመድ በአገልግሎቴ ላይ ሲያደባ አይቼአለሁ። የመላመድ እያደባ መሄድ ምልክቶች ምንድር ናቸው? መጋቢውን ማድነቅ አለመቻል አንደኛው ነው።

ጉባዔው ተጋባኝር ሰባኪ ሲመጣ አዲስ ነገር ስለሆነ ብቻ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ታስተውላለህ፡፡

ከቤተ ክርስቲያኔ ውጭ በማገለግልበት ጊዜ ምን ያህል ምላሽ እንደማገኝ አስተውላለሁ፡፡ ከራሴ ቤተ ክርስቲያን ውጭ የማገኘው ምላሽ ከቤተ ክርስቲያኔ ይልቅ ከፍተኛ እንደሆነ አስተውዬአለሁ፡፡ ብዙ ተአምራትና ይበልጥ ተቀባይነት አለ፡፡ ይህ በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን በጣም የተለመደ ክስተት ነው፡፡ ከእነኚህ መንፈሳዊ የሚያደቡ ነገሮች ለመጠበቅ የምልጃ ጸሎት አስፈላጊ ነው፡፡ የምልጃ ጸሎት መንፈስ እንዳይፈስ የሚያደርገውን ያንን የሚያደባ መላመድን ይዋጋል፡፡

ምዕራፍ 22

የተቆረጡ ነገሮችን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የተቆረጡ ነገሮችን ሕግ ይቋቋማል

ዓመፃን ይጨርስ፣ ኃጢአትንም ይፈጽም፣ በደልንም ያስተሰርይ፣ የዘላለምን ጽድቅ ያገባ፣ ራእይንና ትንቢትን ያትም፣ ቅዱስ ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥሮአል።

ዳንኤል 9፡24

ዳንኤል ለሕዝቡ ሲጸልይ ነበር። እግዚአብሔር ስለ እነርሱ እንዲንቀሳቀስ ፈለገ። ድንገትም፣ አስደናቂ መልእክት የሰጠው መልአክ ጎበኘው። ታያለህ፣ ዳንኤል እየሞከረ ያለው በሕዝቡ ሁኔታ ላይ ለውጥ ለማምጣት ነበር። ቢሆንም፣ ያ አልሆነም።

ዳንኤል በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሰባ ሱባኤ ቅጣት መለኮታዊ በሆነው ሰማያዊ ሕግ እንደተወሰነ ተነገረው። ሊያደርግ የሚቻለው አንዳች ነገር አልነበረም። በዚህ ጥቅስ ትኩረትህን *የተቆረጡ ነገሮች* ብዬ ወደ ምጠራው ነገር እወስዳለሁ።

እነኚህ ነገሮች ሊለወጡ አይችሉም። ብትጸልይም ባትጸልይም ይፈጸማሉ!

የምልጃ ጸሎት የተቆረጡ ነገሮችን ማስተናገድ እንድትችል ይረዳሃል። ብዙ ሊለወጡ የሚችሉ ነገሮች እንዳሉ ተረዳኝ። ሊለወጡ የማይችሉ ቢሆን መጸለይ ባላስፈለገ ነበር። እያሳየሁ ያለሁት አንዳንድ ሊለወጡ የማይችሉ ነገሮች እንዳሉ ነው (የተቆረጡ ነገሮች)።

አንዳንዴ በአንድ ሕዝብ ላይ ጦርነት ይታወጃል። ምንም ልታደርግ የምትችለው ነገር የለም ሊለወጥ የማይችል ከሆነ ጌታ ሊለወጥ እንደማይችልና ምን ማድረግ እንደሚገባህ ያሳይሃል። ዳንኤል በእስራኤል ላይ ሰባ ሱባኤ ቅጣት እንደሚሆን በእርግጥ ተነግሮት ነበር። በዚያ ላይ ሊያደርግ የሚችለው አንዳች አልነበረም።

ሞት አብዛኛውን ጊዜ ከተቆረጡ ነገሮች ውስጥ አንደኛው ነው። ይህን አስገራሚ ጥቅስ ተመልከት። ከዚህ ምድር የምትለይበት እርግጠኛ ጊዜ እንዳለ ይናገራል። በዚህም ምክንያት፣ ከዚህ በኋላ ስለ ሞቸት መጨነቅ አያስፈልግም።

> በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን? ወራቱም እንደ ምንደኛ ወራት አይደለምን?
>
> ኢዮብ 7፡1

ኢዮብ የሰው ሕይወት እንደ ቅጥረኛ ሠራተኛ እንደሆን ገልጾታል። ኮንትራቱ ሲያልቅ አለቀ ነው።

> . . . ወራቱም እንደ ምንደኛ ወራት አይደለምን?
>
> ኢዮብ 7፡1

ምንም ልታደርግ አትችልም። እዚህ ጋር ልዩነቱ የኮንትራትህን የመጨረሻ ቀን አለማወቅ ነው። ለዚያ ነው ሁልጊዜ ዝግጁ ልትሆን የሚገባህ።

እናም ዳግም ለዚያ ነው መፍራት የማይገባህ። **ምልጃ የተቆረጡ ነገሮችን መስወጥ በማይቻልበት ጊዜ፣ እንዴት አብረኽው ልትኖር እንደምትችል ወይም እንዴት ልትዘጋጅ እንደምትችል ያሳይሃል!**

ጁሊየስ ቄሳር እንኳ ያንን አውቋል! እንዲህ አለ "ሞት ሲመጣ ይመጣል።"

ፈሪዎች ከመሞታቸው በፊት ብዙ ጊዜ ይሞታሉ፤
ጀግና ግን አንዴ ብቻ ይሞታል።
አስካሁን ከሰማኋቸው አስደናቂ ነገሮች፣
ከሁሉ እንግዳ የሆነብኝ ሰዎች መፍራታቸው ነው፣
ያንን ሞት እንደሆነ እያዩ የማይቀር ፍጻሜ፣
ሲመጣ የሚመጣ።

ምዕራፍ 23

የከዋክብትን ሕግ በመቃወም እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ ከዋክብትን ይቋቋማል

ልማድ ሆኖ፣ ዳግመኛ የተወለዱ ክርስቲያኖች ከዋክብት ከሚባለው ጉዳይ ይርቃሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከዋክብት እንድናጠና ወይም እንድንመራባቸው አያስተምረንም። ቢሆንም፣ የከዋክብት ተጽዕኖ ብዬ የምለውን ልጠቅስ እፈልጋለሁ።

ከከዋክብት በምድር ላይ በሚከሰቱ ክስተቶች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ የሚያሳዩ ጥቂት ጥቅሶችን ላሳይህ እወዳለሁ። ለምሳሌ ያህል የኢየሱስ ልደት ከምስራቅ ለመጡት ጠቢባን በኮከብ ታይቷል።

> በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በምሥራቅ **ኮከቡን** አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና" ሲሉ ጠየቁ። ጠቢባኑ ንጉሡ ያለውን ከሰሙ በኋላ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ይህም በምሥራቅ ያዩት **ኮከብ** እየመራቸው ሕፃኑ እስካለበት ድረስ ወሰዳቸው። **ኮከቡንም** ሲያዩ ከመጠን በላይ ተደሰቱ።
>
> ማቴዎስ 2፡1፣2፣9፣10
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

የከዋክብት ተፅዕኖ ወይም ጉልህነት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በክርስቶስ ልደት ጊዜ ተረጋግጧል። በጥቅሉ ለማለት የፈለግሁት ስለ እነኚህ ከዋክብቶች የሆነ ትርጉምና ጠቋሚነት አለ ለማለት ነው። ልክ አንድ የተደራጀ እና የተቆረጠ ነገር በዚያ ያለ ይመስላል።

ይህን ጥቅስ ልብ በል

> ፕልያድስ የተባሉትን **ውድ ከዋክብት** ልትለጉም፣ ወይም የኦርዮንን ማሰሪያ ልትፈታ ትችላለህን? ማዛሮት የተባለውን የከዋክብት ክምችት በወቅቱ ልታወጣ፣ ወይም ድብ የተባለውን ኮከብና ልጆቹን ልትመራ ትችላለህ? የሰማያትን ሥርዓት ታውቃለህ? ይህንስ **በምድር ላይ እንዲሠሰጥን ማድረግ ትችላስህ?**
>
> ኢዮብ 38፡31-33
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ኦሪዮን በዚህ ጥቅስ የሚያሳየው ግዙፍ የተባሉትን ህብረ ከዋክብት ነው።
ፕልያዲስ የሚለው ስም የተሰጠው ታውረስ ለተባሉ ሰባት ህብረ ከዋክብት ነው።
ለክቱራስ በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ውስጥ የሚገኝ ትልቁ ድብ የሚባለው ህብረ ከዋክብት ነው።

ማዛሮት የዞዲያክ አሥራ ሁለት ምልክት ነው

ዘዲያክ የሰማይ መቀነት ሊሆን በውስጡም የፀሐይን፣ ጨረቃ፣ እና ፕላኔቶች አቀማመጥ የሚያሳይ ነው ተብሎ በጥንት የከዋክብት ተመራማሪዎች የሚታወቅ ሲሆን፣ በውስጡም በአሥራ ሁለት እኩል ስፍራዎች ተከፋፍሏል (የዞዲያክ ምልክቶች)።

ከላይ የታየው ጥቅስ ስለ ውብ የፕልያዲስ ከዋክብት *ተፅዕኖ* ይናገራል። ይህ ከዋክብት መሬት በምትባለው ፕላኔት ባሉ ክስተቶች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ነው። እንዲህ ብሎ ይጠይቃል "ይህንስ በምድር ላይ *እንዲሠለጥን* ማድረግ ትችላለህ?" በምድር ላይ እንዲሰለጥን ሲል ይህ ህብረ ከዋክብት

በሰዎች ጉዳይ ላይ ያለውን ተፅዕኖ የሚያሳይ ነው። የማዛሮትን ወይም ፕላሲዲያን አሉታዊ ተፅዕኖ፣ የምልጃ ጸሎትን ኃይል ሊቋቋም እንደማይችል አምናለሁ!

ምናልባት መኖራችንን የሚቋቋሙ ብዙ ነገሮች እንዳሉ አታውቅ ይሆናል። እግዚአብሔር የምልጃ ሰው እንድትሆን ብዙ ተጨማሪ ምክንያቶችን እየሰጠህ ነው። በምትማልድበት ጊዜ በሰማያዊ ስፍራ በከዋክብት ውስጥ የተጻፈ የሚቃወምህ ነገር ሁሉ ለበጎ ይለወጣል።

ምዕራፍ 24

ስለ እግዚአብሔር ሕግጋት እንዴት መማለድ እንደሚቻል

ምልጃ የእግዚአብሔር ሕግጋት በተመለከተ ለውጥ ያመጣል

የእግዚአብሔር ሕግ ስለ እግዚአብሔር የምህረት ወይም የፍርድ ችሎታ ይናገራል። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ፣ ኃያል እግዚአብሔር ሁለት አማራጮች አሉት፣ **ፍርድ ወይም ምህረት**። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ምህረትን እንደሚመርጥ ይናገራል እግዚአብሔር ከፍርድ ምህረትን ማሳየት ይመርጣል!

> በደልን ይቅር የሚል፣ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? **ምህረትን ደመድዳልና** ቁጣውን ለዘላለም አይጠብቅም።

ሚኪያስ 7፡18

ቃሉ እግዚአብሔር በኃጢኣተኛው ሞት ደስ እንደማይሰኝ ያስተምረናል።

> . . .በሕያውነቴ እምላለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ለመንገዳቸው ተመልሰው በሕይወት እንደኖሩ እንጂ በክፉዎች ሞት **ደስ አልሰኝም**።

ሕዝቅኤል 33፡11

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

እግዚአብሔር ፍርድን ሲሰጥ፣ አብዛኛውን ጊዜ የከፋ እና ሊመለስ የማይችል ነው። ምክንያቱም አምላካችን የፍትህ አምላክ ነውና፣ ጊዜው ሲደርስ ፍርድ ከማሳለፍ በቀር ሌላ ምርጫ የለውም።

አብርሃም እና ሙሴ በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ከቆሙ ሰዎች ሁለት ምሳሌዎች ናቸው። ሰዶምና ጎመራ የእሳት ፍርድ በተገባቸው ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳይወጣ ለመከልከል የሞከረ አብርሃም ነበር። የምልጃ ጸሎቱ እግዚአብሔር እንዴት ሰውን ሊሰማ እንደሚችል የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው።

እግዚአብሔር ለምን ኢምንት የሆነውን ሰው ይሰማል? እግዚአብሔር ምህረትን ለመምረጥ ፍርድን ለመተው ምክንያት ይፈልጋል። ማንኛውም መልካም እና እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ያለው መሪ ፍርድን ለመተውና ምህረትን ለማድርግ እድል ይፈልጋል።

> አብራምም ቀረበ አለም፦ በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን?
>
> ዘፍጥረት 18፡23

የሚያሳዝነው፣ አብርሃም ሰዶምና ጎሞራን ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያስመልጥ አልቻለም። እግዚአብሔር በከተማው አምስት ጻድቅ እንኳ ሊያገኝ አልቻለም። እግዚአብሔር ፍርድን ለማስቀረት ሞከረ ግን አልተሳካም!
ሙሴ፣ በሌላ ወገን፣ ለእስራኤል ደህንነትን ሊያመጣ ችሏል።

> ስለዚህ በመቅሠፍቱ እንዳያጠፋቸው ይመለስ ዘንድ፣ እርሱ የመረጠው ሙሴ በመካከል ገብቶ፣ **በፊቱ ባይቆም ኖሮ**፣ እንደሚያጠፋቸው ተናግሮ ነበር።
>
> መዝሙር 106፡23
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ውድ አገልጋይ፣ እግዚአብሔር በመካከል እንድትቆም ጠርቶሃል። በእግዚአብሔር ፍርድ እና በሕዝቡ መካከል ስትቆም፣ የብዙዎችን ሕይወት ታድናለህ። የምትማልድ ሁን! ሕዝቦችን ታድናለህ!

ምዕራፍ 25

በምጥ ጸሎት ውስጥ እንዳለህ የሚያሳዩ ሰባት ምልክቶች

ልጆቼ ሆይ፣ ክርስቶስ በእንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል።

ገላቲያ 4፡19

ኤጳፍራ . . .፤ ሁልጊዜ ስለ እናንተ በጸሎቱ ይጋደላል።

ቆላስይስ 4፡12

የምጥ ጸሎት አዲስ ነገሮች እንዲወለዱ የሚያደርግ ጸሎት ነው። በአገልግሎትህ ውስጥ አዲስ አቅጣጫ እንዲወለድ ከፈለግህ በምጥ ጸሎት ውስጥ፣ ማለፍ አለብህ። በጸሎት የተንበረከክበት ቦታ እስኪጎደጉድ ድረስ በምጥ ጸሎት ውስጥ የነበሩ ሰዎች እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል። ከዚህ ቀድሞ የነበሩ የመንፈስ ቅዱስ መቀጣጠል (ሪቫይቫል) የተወለዱት በምጥ በማለዱ ሰዎች ነው።

የምጥ ጸሎት ልጅ እስኪወለድ ድረስ በጥልቅ ስሜት የሚደረግ የምጥ ጸሎት ነው። ስለዚህ የምጥ ጸሎት ምንድር ነው? እና በምጥ ጸሎት ውስጥ መሆኔን ወይም አለመሆኔን በምን ማወቅ እችላለሁ? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ አንዳንድ ምልክቶችን እንድትመለከት እሰጥሃለሁ። እነኚህ ምልክቶች በምጥ ጸሎት ውስጥ እንደሆንክና እንዳልሆንክ ያሳይኃል። ልጆች ያሏቸው ሴቶች ስለ ምጥ ጸሎት በይበልጥ ሊያስተምሩ ይችላሉ። የማዋለጃ ክፍል ልምዳቸውን በስዕል

ቁልጭ አድርገው ማሳየት ይችላሉ! *ያለ ምጥ ልጅ እንደሌለ ሁሉ፣ ያለ ምጥ ጸሎት ምንም አዲስ መንፈሳዊ ነገር ሊኖር አይችልም።*

የምጥ ክፍል ጸሎት ሰባት ምልክቶች

ሳታምጥ ወለደች፤ ምጥም ሳያገኛት ወንድ ልጅን ወለደች። ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል?

ኢሳይያስ 66፡7

1. የረጅም ሰዓት ጸሎት

አብዛኞቹ ሴቶች ለብዙ ሰዓት ያምጣሉ። ከብዙ ሰዓት ስቃይ በኋላ፣ ሴት አዲስ ሕፃን ትወልዳለች። ለረጅም ጊዜ መጸለይ አዲስ ቤተ ክርስቲያናት እና አገልግሎቶችን ይወልዳል።

2. *መሰቃየት*

ሴቶች በማዋለጃ ክፍል ውስጥ እያሉ የስቃይ ዓይነትን ሁሉ ይቀምሳሉ። ያለ ስቃይ፣ መጣስ የለም። የምጥ ጸሎት በምትጸልይበት ጊዜ ልትጾም እና ሌሎች ደስታዎችህን መስዋዕት ልታደርግ ይገባህ ይሆናል። ይህ የምጥህ አንደኛው ገጽታ ነው። እነግርሃለሁ፣ ሽልማትህ ታላቅ ነው!

3. ሕመም

ልጅ ማግኘት ብዙ ሕመም አለበት። የጾም ስቃይና የመስዋዕትነት ሕመም የምጥ ገጽታዎች ናቸው።

4. እፍረት

ምናልባት በምትጾምበት እና በምትጸልይበት ጊዜ የምትስብ ላትሆን ትችላለህ። በጾም እና ጌታን በመጠበቅ ክብደት ልትቀንስ ትችላለህ።

አንድ ሰው አንድ ቀን በማላገጥ እንዲህ አለኝ፣ “አፅም በመሆን ወደ መንግሥተ ሰማይ የምትገባ ይመስልሃል?” በዚያን ወቅት አንድ ሕብረት ለመመስረት በጾም ጸሎት ላይ ነበርሁ። መጥረጊያ መስዬ ስለ ነበር ጓደኞቹ ያላግጡብኝ ነበር! ቢሆንም አዲስ የክርስቲያን ሕብረት ተወልዶ በማየቴ ትልቅ ደስታ ሰጠኝ። አንድ ቀን ደግሞ በሰማይ ሽልማቴን አጭዳለሁ።

5. መድከም

በጽናት በምትጸልይበት ጊዜ ልትደክም ትችላለህ። ሰነፍ ከሆንህ በምጥ ጸሎት ውስጥ ልትገባ አትችልም። የምጥ ጸሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና ካሴት ከማዳመጥ የተለየ ነው። ረጅም ሰዓት የመጸለይ አካላዊ ጥረትን ይጠይቃል። ሙሴ ሰዎች እጁን ደግፈው እስኪይዙለት ድረስ ደክሞ ነበር።

6. መራብ

ይህም እግዚአብሔርን ስትጠብቅ ከምትከፍላቸው ዋጋዎች አንዱ ነው። በማዋለጃ ክፍል ውስጥ ያለች ሴት በየአምስት ደቂቃው እየተነሳች መቆያ የምትቀማምስ ይመስልሃል? በእርግጥ አይደለም! ሁሉን እስክትፈጽም ረሃቡን ትታገሳለች። ልጅ የወለደችን ሴት ጠይቅና እኔ የምለው እውነት እንደሆነ ትነግርሃለች።

7. አዲሱ ሕፃን

የምጥ ጸሎት ሁሌም አዲስ ነገርን ይወልዳል። ከጊዜ በኋላ፣ ያንን አዲስ ነገር በእጅህ ውስጥ አይተህ ክብሩን ለጌታ ትሰጣለህ። ምናልባት አዲስ ቤተ ክርስቲያን ወይም አዲስ ሕብረት ሊሆን ይችላል። ምናልባትም በአገልግሎትህ ውስጥ አዲስ የእድገት ደረጃ ሊሆን ይችላል። በጸሎት ማማጥ ቀላል ነገር አይደለም፣ ግን ተገቢ ነው!

ምዕራፍ 26

በልሳን የምጸልይበት ሰላሣ - ሁለት ምክንያቶች

ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ

1ኛ ቆሮንቶስ 14 : 18

በእኔ አስተያየት በልሳን የመጸለይ ችሎታ ምናልባት እግዚአብሔር ለአገልጋዮች ከሰጣቸው ስጦታዎች ሁሉ የበለጠ ነው። በዚህ ምዕራፍ በልሳን መጸለይ ለምን ለአገልጋዮች ሁሉ በጣም አስፈላጊ እና ጠቃሚ እንደሆነ አካፍልሃለሁ። ሰላሣ - ሁለቱም ምክንያቶች መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ ለራስህ ስትል እንድታስባቸው እፈልጋለሁ።

በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።

1ኛ ቆሮንቶስ 14 : 14

1. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ራሴን እንደ ባትሪ እሞላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡4)
2. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ እነቃቃለሁ (የሐዋርያት ሥራ 2፡4)
3. ለልሳን በምጸልይበት ጊዜ የምጸልየው ከልቤ (በመንፈሴ) ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
4. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቱ የሚታዘዘውና የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ነው (የሐዋርያት ሥራ 2፡4)
5. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ወዲያውኑ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ መንቀሳቀስ እጀምራለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡1)
6. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ሌሎች ሰዎች የምለውን አይረዱም (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡1)
7. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እጋንንቶች የምለውን አይረዱም (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡1)
8. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ጸሎቴን በመተርጎም የመንፈስን ድምፅ መስማት እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡13)
9. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እንደ ኢየሱስ ለረጅም ሰዓት መጸለይ እችላለሁ (ማርቆስ 1፡35፣ ሉቃስ 6፡12)
10. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ለነፍሳት፣ ለቤተሰቦች እና ለሕዝቦች መማለድ እችላለሁ (ኤፌሶን 6፡18)
11. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ለራሴ እና ለእግዚአብሔር መናገር እችላለሁ፡፡ ይህ ደግሞ በማንኛውም ስፍራ በእግዚአብሔር ላይ እንዳተኩር ይረዳኛል (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡ 28)
12. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ምስጋናና ውዳሴን ማቅረብ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡ 17)

13. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ክርስቶስ በእኔ ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ ምልክት ነው (ማርቆስ 16 : 17)
14. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ ወደ መለኮታዊ ነገሮች ውስጥ እገባለሁ (የሐዋርያት ሥራ 2፡4)
15. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እምነትን እየተለማመድሁ ነው (ገላቲያ 3: 5)
16. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እንደ ጳውሎስ ያሉ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ያደረጉትን እያደረግሁ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡18፣ ዕብራውያን 6፡12)
17. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ በጠላቶቼ ፊት የምለውን ነገር ሳያውቁ እነርሱን በመቃወም መጸለይ እችላለሁ
18. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ማሰብ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
19. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ማጥናት እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
20. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ መጽሐፍ ቅዱሴን ማንበብ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
21. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ሌላ መጽሐፍትን ማንበብ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
22. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ካሴት ማዳመጥ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
23. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ቪዲዮ ማየት እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
24. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ገላዬን መታጠብ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)

25. በልሳን በምጸልይበት እየጸለይሁ ልብሴን መልበስ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
26. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ መዜድ (መራመድ) እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
27. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ አየጸለይሁ መጻፍ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
28. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ምግብ ማብሰል እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
29. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ በቢሮ ውስጥ ሥራ መሥራት እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡1)
30. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ ፀጉሬን መሠራት እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
31. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ መኪናዬን መንዳት እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)
32. በልሳን በምጸልይበት ጊዜ እየጸለይሁ አውቶቡስ መጠበቅ እችላለሁ (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14)

ክፍል ፫

ጉብኝት

ምዕራፍ 27

መጋቢዎች መንጋቸውን ሊጐበኙ የሚገባበት አሥራ ሁለት ምክንያቶች

ወጋቢዎች፣ ጉብኝት የመጋቢነት አገልግሎታችሁን ይለውጣል! ጉብኝት ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን እድገት ያመጣል፡፡ ጉብኝት ወደ ሰዎች መኖሪያ ቤት እና ሥራ ቦታ በመሄድ ማገልገል ነው፡፡ ሰዎችን በቤታቸው ተገኝቶ ማገልገል አገልግሎትን ስኬታማ ከሚያደርጉ ቁልፎች ትልቁ መንገድ ነው፡፡

ጉብኝት የእውነተኛ መጋቢያዊ አገልግሎት ዋነኛ ክፍል ነው፡፡ ጉብኝት የውሸት አገልግሎት አይደለም፡፡ እውነተኛ ነገር ነው፡፡ የፈለገውን ያህል ብትጸልይም በግህን መጐብኘት አለብህ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስህን አንብብ ያን ጊዜ እግዚአብሔር መጋቢዎች በጎቻቸውን መጐብኘት እንደሚጠብቅባቸው ትረዳለህ፡፡

ውድ መጋቢ፣ በጐች በሚሰበሰቡበት ቦታ ብቻ ከመስበክ የሚያልፍ ነገር እንዲኖርህ ምርጫህ ይሁን፡፡ ራስህን እንደ ጦር አዛዥ ወይም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር አትቁጠር፡፡ በጐቹ ሊገኙ የሚችሉበት ቦታ ሁሉ ገብቶ የጠፋውን

በግ የሚፈልግ እውነተኛ እረኛ ሁን። ያ እውነተኛ የመጋቢነት አገልግሎት ነው።

> ስለዚህ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚጠብቁ እረኞች እንዲህ ይላል። በጎቼን በትናችኋል አባርራችኋቸውማል **አልጐበኛችኋችሁምም** እነሆ፥ የሥራችሁን ክፋት እጐበኛባችኋለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፦
>
> ኤርሚያስ 23፡2

መጋቢዎች በጐቻቸውን ሊጐበኙ የሚገባበት አሥራ ሁለት ምክንያቶች

1. ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባል ጉብኝት ያስፈልገዋል
2. ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባል ጉብኝት ይገባዋል
3. ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲጐበኝ ይጠብቃል
4. አንድ በግ ይበልጥ በተጎበኝ ጊዜ፣ ይበልጥ ጤናማ ይሆናል
5. ጉብኝት አንድን በግ ቋሚ የቤተ ክርስቲያን አባል ያደርገዋል
6. እግዚአብሔር እያንዳንዱን መጋቢ በጉን እንዲጎበኝ ይጠብቅበታል
7. በግ ከመጋቢው የተደጋገመ ጉብኝት ያስፈልገዋል
8. ሁሉም በግ ከሌሎች መጋቢዎችና እረኞች ጉብኝት ያስፈልገዋል
9. አለመጎብኘት የቸልተኝነት ኃጢዓት ነው
10. በጎችን ሙሉ በሙሉ ችላ ማለት የመተው ኃጢዓት ነው
11. ብዙ በጎች ካልተጎበኙ ይወድቃሉ
12. ቤተ ክርስቲያን ያለ ጉብኝት አታድግም

ሁሉም ችግር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚካሄደው ፕሮግራም አይፈታም። ብዙ ችግሮች ስልክ በመደወል ሊፈቱ አይችሉም።

የእግዚአብሔርን መንጋ ስትንከባከብ ሰዎች ምን ያህል ችግሮች እንዳሉባቸው ትረዳለህ። የሕዝቅኤል መጽሐፍ ብዙ በጎች እንደሞቱ፣ እንደተሰበሩ እና እንደተበተኑ ይነግረናል።

> የደከመውን አላጸናችሁትም **የታመመውንም** አላከማችሁትም **የተሰበረውንም** አልጠገናችሁትም **የባዘነውንም** አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቈናም ገዛችኋቸው።እረኛም በማጣት ተበተኑ፥ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፥ ተበተኑም።
>
> ሕዝቅኤል 34፡ 4፣5

ከፑልፒት ላይ የሚደረገው ስብከት የበጎችን ችግር ሁሉ ሊፈታ አይችልም። በጎች ሊፈለጉ ይገባቸዋል። “. . . የጠፋውንም አልፈለጋችሁም።” (ሕዝቅኤል 34:4)

የቤተ ክርስቲያን አባላት ጉብኝት ይገባቸዋል ምክንያቱም ኢየሱስ ስለ እነርሱ ሞቷልና። ሕይወቱን ለእነርሱ ሰጥቷል። ዛሬ ሰዎች ግድ የሚላቸው የራሳቸውን ካምፓኒ፣ ንግድ፣ ቤት እና መንግሥታቸውን መገንባት ነው። ማንም ስለ በጉ ግድ የሚለው የለም። ኢየሱስ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ፣ “ትወደኛለህ?” ብሎ ጠየቀው ጴጥሮስም፣ “በእርግጥ እወድሃለሁ” አለ። የእኛም መልስ እንዲሁ ይሆናል። ኢየሱስ ግን ከወደዳችሁኝ በጎቼን መመገብ አለባችሁ ብሎ በግልጽ ተናግሯል።

አንዳንድ ጊዜ፣ ሰዎች ተደጋጋሚ ጉብኝት ያስፈልጋቸዋል ምክንያቱም አንድ ጉብኝት ችግሩን ላይፈታ ይችላል። አንዳንድ ሰዎችን ጎብኝቼ ምንም ለውጥ ያልተፈጠረበት ሁኔታ ነበር። ሌሎች ሰዎች እነኚያን ሰዎች ሲጎበኙ መጣስ ሆኖላቸዋል!

በጎችን አለመጎብኘት ቸልታ ነው! በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በእርግጥ አርግፍ አድርጎ መተው ነው። የእዚአብሔር ቁጣ በእረኞች ላይ ቢመጣ አትደነቅ።

> የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን፣ ሰይፉንም ከደም የሚከለክል ርጉም ይሁን።
>
> ኤርሚያስ 48፡10

ምዕራፍ 28

ከጉብኝት ኃይል ጀርባ ያሉ ሦስት ምስጢሮች

ጉብኝት ሕይወትን የመለወጥ ኃይል አለው! ብዙ መጋቢዎች ከጉብኝት ኃይል ጀርባ ያለውን ምስጢር አያውቁም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ በመጋቢነት አገልግሎት ውስጥ፣ ጉብኝት ያለውን ኃይል እንድትረዳ እፈልጋለሁ!

ጉብኝት የሦስት ኃይሎች ውህደት ኃይል ነው

1. ***ጉብኝት የፍቅር መገለጫ ነው***
2. ***ጉብኝት የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎት ያካትታል***
3. ***ጉብኝት የጸሎትን አገልግሎት ያካትታል***

የእግዚአብሔር ቃል ኃያል እና ሕይወት ለዋጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጨለማ ባለበት ብርሃን እንደሚያመጣ ይናገራል። ስለዚህ በሰዎች ላይ ከፍተኛ ለውጥ ቢያመጣ የሚደንቅ አይደለም።

ጸሎትም ኃይለኛ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጸሎት እጅግ ኃይልን ያደርጋል ይላል። ያ ማለት ከፍተኛ ውጤት ያመጣል ማለት ነው።

ግን መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅር ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖርም ይናገራል! ሁል ጊዜ የምንጠቀምባቸው ብዙ ዓይነት መንፈሳዊ መሣሪያዎች አሉ። የትኛውም

መሣሪያ ግን “ለዘላለም አይወድቅም” ተብሎ አልተገለጸም ይህ ደግሞ ፍቅርን በጣም ኃይለኛ መሣሪያ ያደርገዋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ፣ ቃሉን ብናገለግልም ሰዎች መፈቀር አይሰማቸውም፡፡ በጉብኝት ውስጥ፣ የቃል፣ የጸሎት እና የፍቅር ውህደት አለ፡፡ የተጎበኘው ሰው የመፈቀር ስሜት ይሰማዋል፡፡ እቤቱ ድረስ እንድትሄድ ያደረገህ ስለምታፈቅረው መሆን አለበት! ባልተለመደ ሰዓት ወደ ሰው ቤት የመሄድ እርምጃ ታላቅ ፍቅርን ይገልጣል፡፡ ፍቅርን በቃል ብቻ መግለጽ አትችልም፡፡

ልጆቼ ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ

1ኛ ዮሐንስ 3፡18

በሥራ መውደድ ወደ ሰዎች ቤት መሄድን ይጨምራል፡፡ በሥራ መውደድ ሰዎች ያሉበትን ኑሮ ሁኔታ ማወቅ ይጨምራል፡፡
አንዳንድ ጊዜ የሚጎበኘው ሰው የምትናገረውን ቃል ላይሰማ ይችላል፡፡ በውስጡ የሚቀረው ግን መጥቶ እስኪጎበኘኝ ድረስ ስለ እኔ ግድ ይለዋል የሚለው ነገር ነው፡፡

ውድ አገልጋይ፣ የቃል፣ የፍቅር እና የጸሎትን ውህደት በችልታ አትመልከት!

ምዕራፍ 29

ስምንት የፍሬያማ ጉብኝት መመሪያዎች

1. እያንዳንዱ ጉብኝት ሊያከናውነው የሚገባ ነገር መኖር አለበት፡፡
2. እያንዳንዱ ጉብኝት ዘና ባለ ማኅበራዊ ጉዳይ መጀመር አለበት፡፡
3. መጋቢዎች የእረኝነት ጉብኝት ተራ የሆነ ማኅበራዊ ግንኙነት እንዳልሆነ በሚገባ መገንዘብ አለባቸው፡፡
4. የመጋቢ ጉብኝት መንፈሳዊ ክስተት መሆን እና መንፈሳዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይገባል፡፡
5. የመጋቢ ጉብኝት ሁሉ የቃሉን አገልግሎት ያካተተ መሆን አለበት
6. ጉብኝት ስኬታማ የሚሆነው የእግዚአብሔር ኃይል በጸሎት አማካኝነት ሲለቀቅ ብቻ ነው፡፡
7. የመጋቢነት ጉብኝት ሁሉ በኃይለኛ ጸሎት መጠቃለል አለበት፡፡
8. ጉብኝት ኃይለኛ ዘላቂ ተፅዕኖ ሊኖረው ይገባል፡፡

> **የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፤ . . . ። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፤ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው**
>
> **ዮሐንስ ፤11-12**

ኢየሱስ ምድርን በኅበኘበት ሦስት ዓመት ውስጥ ብዙ ሠርቷል፡፡ ኢየሱስ በአገልግሎት ውስጥ በመንከላወስ ጊዜውን ሲያጠፋ አትመለከትም፡፡ ሰበከ፣ አስተማረ፣ ሰዎችን አገለገለ፡፡

የኢየሱስ ምድራዊ ጉብኝት የመጀመሪያ ክፍል ማኅበራዊ ግንኙነት ነበር። ከማኅበረሰቡ ጋር የተስማማ እና ከእነርሱ እንደ አንዱ ነበር።

> ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን ነገር ሁሉ ነገር በልብዋ ትጠብቀው ነበር። ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።
>
> ሉቃስ 2፡51-52

ኢየሱስ ግን እንዲሁ ለማኅበራዊ ጉብኝት እንዳልመጣ አውቋል። ሰበኮ ሕዝቡን ባረከ። ጸሎቶቹ በጣም ኃይለኛ ከመሆናቸው የተነሳ የሞተውን ያስነሱና አጋንንትን ያስወጡ ነበር። ከዚያ ጉብኝት በኋላ፣ ምድር ከቶውንም እንደነበረች አልቀረችም።

> ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል።
>
> ዮሐንስ 21፡25

ምዕራፍ 30

አሥር የጉብኝት ሕግጋት

1. መጋቢ እንዲጎበኝ የጠየቀን ሰው በፍጹም እንቢ ማለት የለበትም

በግ ሁልጊዜ የድረሱልኝ ጩኽት አያሰማም፣ ድረሱልኝ ካለ ግን ምላሽ መስጠትህን እርግጠኛ ሁን። ጳውሎስ የድረስልን ጥሪን ችላ አላለም።

> . . . አንድ የመቄዶንያ ሰው፡- ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን እያለ ቆሞ ሲለምነው ነበር።
> የሐዋርያት ሥራ 16፡9

2. መጋቢ ሁሉ በቃል ያልተገለጠን የጉብኝት ጥያቄ ማወቅ አለበት

የቤተ ክርስቲያን አባል አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ ትኩረት እንደሚያስፈልገው ማወቅ አለብህ። መዝሙሩ እንዲህ ይላል፣ "ዓይኖቹ በድንቢጦቹ ላይ ነው"። ልክ ዓይኖቹ በ በድንቢጦቹ ላይ እንደሆኑ፣ የአንተም ዓይኖች በበጐችህ ላይ መሆን አለባቸው። ልክ እግዚአብሔር የጸጉርህን ቁጥር እንደሚያውቅ፣ አንተም በጎችህን ልትቆጥር እና ልትጠብቃቸው ይገባሃል። የእግዚአብሔር ቁጣ የበጎቻቸውን ችግሮች ችላ በሚሉ እረኞች ላይ ነው።

የደከመውን አላጽናችሁትም **የታመመውንም** አላከማችሁትም **የተሰበረውንም** አልጠገናችሁትም **የጠፋውንም** አልፈለጋችሁም በኃይልና በጭቆና ገዛችኋቸው።። እረኛም በማጣት **ተበተኑ**፣ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፣ ተበተኑም።።

ሕዝቅኤል 34፡ 4-5

ይህ ጥቅስ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ችግር አጉልቶ ያሳያል፡- መድከም፣ መታመም፣ መሰበር፣ መባዘን፣ መጥፋት ወዘተ . . .። እግዚአብሔር እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ታይ ዘንድ ዓይኖችህን ያብራልህ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ግድ የሚለውን ልብ ይስጥህ።

3. እያንዳንዱ መጋቢ ወይም እረኛ ሁለቱንም "የዘወትር" እና "ልዩ" ጉብኝትን መለማመድ አለበት

እያንዳንዱ እረኛ ዘወትር በጎቹን የሚጎበኝበት ፕሮግራም ሊኖረው ገባል። የአሥራ ስድስት ዓመት ወጣት በነበርሁበት ጊዜ በጎብረታችን ውስጥ ያሉትን አባላት ስም ዝርዝር ካወጣሁ በኃላ በእረፍት ቀናት ልጎበኛቸው ወሰንሁ። የእያንዳንዳቸውን ቤት ካርታ ነደፍሁ። ማናቸው ቢሆኑ የደረሰባቸው አንዳች ነገር አልነበረም። እንደ እረኛ፣ በጎቼን ዘወትር ለመጎብኘት ወሰንሁ። የእረኛ ልብ ሜዳውን ያስላል! እያንዳንዳቸው ወዴት ናቸው? ደህና ይሆኑ ይሆን? ይላል።

እንዲሁም ደግሞ፣ የተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩበት ጊዜ ይኖራል። እነኚህ ልዩ ሁኔታዎች እንደ፡- ሞት፣ ሕመም፣ የዘመድ ሞት፣ ልጅ መውለድ፣ የትዳር ችግር ወዘተ . . . የመሳሰሉት ሌላ ተጨማሪ ጉብኝትን ይጠይቃሉ።

4. በቤተ ክርስቲያን አባላት ሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ ልዩ ሁኔታዎች ፈጣን የሆነ የመጋቢነት ምላሽ ይጠይቃሉ

ዳዊትም ሳኦልን አለው፦ እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፤ ከመንጋውም ጠላት ይወስድ ነበር። **በኋላውም እከተለውና** እመታው ነበር፤ ከአፉም አስጥለው ነበር፤ በተነሳብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ እመታው እገድለው ነበር።

1ኛ ሳሙኤል 17፡34-35

አንበሳ በጎችን በሚያጠቃበት ወቅት ለእረኛው የአስቸኳይ አደጋ ጥሪ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ይህ የዘወትር ክስተት አይደለም። አፋጣኝ ምላሽን ይሻል። በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ልዩ ሁኔታ በሚፈጠርበት በማንኛውም ወቅት፣ መጋቢው ምላሽ ለመስጠት የፈጠነ መሆን አለበት። ምናልባት የቤተ ክርስቲያንህ አባል በሚያገሳ አንበሳ አፍ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ልክ እንደ እረኛው ዳዊት ከኋላው ልትከተለው ይገባል።

በማንኛውም መስክ ውስጥ አስቸኳይ ጉዳዮች ይገጥማሉ። በሕክምና ሙያ ውስጥ እንኳ በክፍል በክፍል የተመደቡ ድንገተኛ ክፍሎች አሉ። ለምሳሌ ያህል፦ የቀዶ ጥገና ድንገተኛ ክፍል፣ የማሕፀን ድንገተኛ ክፍል፣ ወዘተ ... በመባል ይመደባሉ። አንድ ዶክተር እነኚህን ድንገተኛ ሁኔታዎች መለየትና ፈጣን ምላሽ መስጠት እንዲችል ሥልጠና ይሰጠዋል። ሰዎች በሁኔታዎች ስብራት ሲደርስባቸው፣ ይህ መንፈሳዊ ድንገተኛ አደጋ ነው። ሰዎች ሲጠፉና ነፍሳቸው በተኩላ እጅ ስትገባም መንፈሳዊ ድንገተኛ አደጋ ነው። እኔ የእኔ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን አባሌን በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ አየዋለሁ። በአንበሳ አፍ ውስጥ ሆኖ አየዋለሁ። እንዴት አስቸኳይ እርዳታ ያስፈልገዋል። ይህ ብዙ በጎች ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ስዕል ነው።

ደካማውን አላበረታችሁትም፣ **በሽተኛውን** አልፈወሳችሁትም፣ **የተጎዳውንም** አልጠገናችሁትም። **የባዘኑትን** አልመለሳችሁም፤ **የጠፉትንም** አልፈለጋችሁም፣ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው። ስለዚህ እረኛ የለምና **ተበተኑ**፤ በመበተናቸውም ለአራዊቱ ሁሉ መብል ሆኑ።

ሕዝቅኤል 34፡4-5
(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

በአገልግሎት ዓለም ውስጥ እነኚህ ልዩ ሁኔታዎች ድንገተኛ ሁኔታዎቻችን ናቸው። የበጎቻችንን ሕይወት መታደግ ከፈለግን ፈጣን ምላሽ መስጠት አለብን።

5. እያንዳንዱ መጋቢ ሁለቱንም ያልተጠበቀ እና የታቀዱ ጉብኝቶችን መለማመድ አለበት

ያልተጠበቀ እና የታቀደ ጉብኝቶች የተለያዩ ውጤቶች አሏቸው። ሁለቱም አስፈላጊ እና ተፈጻሚነታቸውም ግድ ነው።

6. ያልተጠበቁ ጉብኝቶች የቤተ ክርስቲያን አባሎችህን እውነተኛ የአኗኗር ሁኔታ ይገልጣሉ

ያልተጠበቁ ጉብኝቶች አብዛኛውን ጊዜ የሰዎችን ቤት ትክክለኛ ሁኔታ ያሳያል። ወደ ሰዎች ቤት ድንገት በመሄድ ሲጋራ ሲያጤሱ አግኝቼአለሁ። በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት አብረው መኖር የጀመሩ ሰዎችን እግኝቼአለሁ። የቤተ ክርስቲያን አባሎች አሰቃቂ በሆነ ጉስቁልና እና መከራ ውስጥ መኖራቸውን ተረድቼአለሁ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቆንጆና ወዛሞች ሆነው ይታያሉ። የሰዎችን ቤት ሁኔታ በፍጹም መገመት አትችልም። ያልተጠበቁ ጉብኝቶች የማን መጋቢ እንደሆንህ ያሳዩሃል። እንዲያውም በትክክል እንድትሰብክና እንድታገለግል ይረዱሃል።

7. የታቀዱ ጉብኝቶች የቤተ ክርስቲያን አባላት ምርጥ ነገራቸውን እንዲያሳዩህ እድል ይሰጣቸዋል

አንድ ሰው እንግዳ በሚጠብቅበት ጊዜ፣ ቤቱን ያዘጋጃል። ይህ የቤተ ክርስቲያን አባላት ምርጥ ነገራቸውን እንዲያወጡ ይረዳቸዋል። ይህ ደግሞ ለመጋቢያቸው ምርጥ የሆነ ነገራቸውን በማየቱ የስኬታማነትን ስሜት ይሰጣቸዋል።

8. መጋቢዎች ጥንድ ሆነው በመጎብኘት ራሳቸውን ሊጠብቁ ይገባቸዋል

> . . . ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው።

ሉቃስ 10፡1

ከአንድ ሁለት ይሻላል። አንዱ ሌላውን ያበረታል። ለመስበክ እና ቃሉን ለማካፈል እርስ በርሳችሁ ትረዳዳላችሁ። አንዱ ሺዎችን ሁለቱ አሥር ሺዎችን ያሸንፋሉ። ለዚህ ነው ኢየሱስ "ሁለት ሁለት" እያደረገ የላካቸው።

ተቃራኒ ፆታዎችን በምትጎበኝበት ጊዜ ብቻህን ባለመምጣትህ የተሰወረ ዓላማ ይዞ መጣ ለማለት ቀላል ሆኖ አያገኙትም። ጥንድ ሆኖ የመጎብኘት ጥቅሙ ይህ ነው።

9. አንድ ዓይነት ጾታ ያላቸው አገልጋዮች ለጉብኝት ሲወጡ ይበልጥ አስተማማኝ ነው

በተደጋጋሚ እየጎበኝህ ስትሄድ፣ አብሮህ ለጉብኝት ከሚወጣው ጓደኛህ ጋር በይበልጥ እየተቀራረብህ ትሄዳለህ። ይህ መቀራረብ ግን ፈልገህ ያመጣኸው ላይሆን ይችላል።

10. መጋቢዎች ጉብኝታቸው ትክክለኛ ያልሆነ ግምት እንዳይሰጠው ከሚገባው በላይ ጉብኝታቸውን ማዘውተር የለባቸውም

> እንዳይሰለችህ እንዳይጠላህም፤ እግርህን ወደ ባልንጀራህ ቤት አታዘውትር።

ምሳሌ 25፡17

አንድን ሰው ያለ ማሰለስ ብትጎበኝ፣ የዚያ ሰው ስሜት ከደስተኝነት ወደ ጥርጣሬ፣ ወደ መቆጣትና ንዴት ሊለወጥ ይችላል፡፡ ደጋግመህ በመጎብኘት የቤተ ክርስቲያን አባሎችህ እንዲጠሉህ አታድርግ፡፡ ምን ፈልጎ ነው በማለት ግራ መጋባት ይጀምራሉ፡፡ “መጋቢው እየራበው ይሆን? ምግብ ፈልጎ ይሆን? ከእኛ የፈለገው አንዳች ነገር ይኖር ይሆን?” በማለት ራሳቸውን ይጠይቃሉ፡፡

ምዕራፍ 31

ጉብኝትን ቀላል የሚያደርጉ ሰባት ነገሮች

1. **ወደ ቤተ ክርስቲያን እና ከቤተ ክርስቲያን መልስ የምታደርገውን ጉዞ ጉብኝት አካትበት**

   . . . ዘመኑን ዋጁ . . .

   ኤፌሶን 5፡16

አንድ ሰው ይህንን ጥቅስ በተመለከተ የሰጠውን አስተያየት እወደዋለሁ፡፡ እንዲህ አለ፡- *“ሌሎች የሚጥሉትን ጊዜ መግዛት፡፡”* ሌሎች ሰዎች የሚያባክኑትን ጊዜ ስትጠቀምበት፣ ለእግዚአብሔር ታላቅ ነገሮችን ታከናውናለህ፡፡

2. **ወደ ሥራ እና ከሥራ መልስ የምታደርገውን ጉዞ ከጉብኝት ጋር አቀናጅ**

   . . . አጋጣሚዎችን ሁሉ ተጠቀምባቸው . . .

   ኤፌሶን 5፡16

3. **ሁል ጊዜ በአንድ ጉዞ ብዙ ጉብኝቶችን አካሂድ**

   . . . አጋጣሚዎችን ሁሉ ተጠቀምባቸው . . .

   ኤፌሶን 5፡16

   (ቶምሰን ማጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ)

አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ጉዞ ሊጎበኙ የሚችሉ ብዙ ሰዎች አሉ። እኔ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ጉዞ የተለያዩ ሰዎችን ለመጎብኘት እሞክራለሁ።

4. በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ በአንድ ጉዞ ጎብኝ

መልካም እረኛ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ ማወቅ አለበት። በዚያ አካባቢ በምትደርስበት ጊዜ ሁሉ፣ ልታደርጋቸው የምትችለውን ጉብኝቶች ማወቅ አለብህ።

5. ሰዎችን ቤታቸው ልታገኛቸው ሳትችል ስትቀር ሥራ ቦታቸው ወይም ትምህርት ቤታቸው ጐብኛቸው

እንግዲህ እንደ ጥበበኞች . . . እንዴት እንደምትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ

ኤፌሶን 5፣15

አንዳንድ ሰዎች ሊጎበኝ የሚችል ቤት የላቸውም። አንዳንድ ጊዜ የሚኖሩት ከአጎታቸው እና ከአክስታቸው ጋር ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ በረንዳ የሚያድሩ ይሆናሉ። ምናልባት በሥራ ቦታቸው ወይም በትምህርት ቤታቸው ልትጎበኛቸው ትችላለህ። እኔ ብዙ ስኬታማ የሆኑ ጉብኝቶች በሥራ ቦታዎች እና በትምህርት ቤቶች አካሂጃለሁ።

6. እሁዶችን ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የጉብኝት ቀን በማድረግ ተጠቀምባቸው

. . . ዘመኑን ዋጁ . . . (ጊዜዎችህን ተጠቀምባቸው)

ኤፌሶን 5፣16

እሁዶች ታላቅ የጉብኝት ቀኖች ናቸው። ብዙ ሰዎች እሁድ ከሠዓት በኋላን ቤታቸው ውስጥ በመዝናናት ያሳልፋሉ። እሁዶችህን በደንብ ተጠቀምባቸው። እሁዶች የመጋቢዎች የሥራ ቀኖች ናቸው። መጋቢዎች እሁድ መሥራት እና ሰኞ ማረፍ አለባቸው።

7. በምሽት መጎብኘትን አትፍራ

በምሽቱ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ክፍል ሲሠሩ ጌታቸው የሚያገኛቸው ሰዎች የተባረኩ ናቸው። የምሽት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ክፍሎች ከምሽቱ ሦስት ሰዓት እና እኩለ ሌሊት ናቸው። ይህ የእግዚአብሔርን ሥራ አስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት እና እስከ እኩለ ሌሊት ለሚሠሩ ባሪያዎች ማረጋገጫ ማህተም ነው።

> **ከሌሊቱም በሁስተኛው ወይም በሦስተኛው ክፍል** መጥቶ እንዲሁ ቢያገኛቸው፣ **እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው**
>
> ሉቃስ 12:38

ብዙ ሰዎች በማንኛውም መንገድ አምሽተው ይተኛሉ። ቴሌቪዥን ሰዎችን በቤታቸው ነቅተው እንዲያመሹ ያደርጋቸዋል። **ብዙ ሰዎችን በጣም ከመሸ በኋላ ሄደህ ካልጎበኘኸቸው በፍጹም አታገኛቸውም**። ግን ጥንድ ሆነህ መጎብኘትህን እርግጠኛ ሁን። ይህን ማድረግ የሚጎበኛው ሰው ሌላ ስውር ዓላማ እንዳለህ አድርጎ እንዳያስብ ይጠብቅሃል።

ምዕራፍ 32

ሕይወት የመለወጥ ኃይል ያላቸው አምስት ጉብኝቶች

የያህዌ ጉብኝቶች

1. የጋብቻ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረግ ጉብኝት

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ጎበኘ

> እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ **የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ** ከገነት ውስጥ ሲመላለስ **ሰሙ** አዳምና ሚስቱም **ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት** በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።
>
> ዘፍጥረት 3፡8

ጌታ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በውድቀት ውስጥ ሆነው ጎበኛቸው። ትክክለኛ ያልሆነ ነገር በማድረጋቸው ችግር ውስጥ ነበሩ። አዳም ሔዋን እባቡን አነጋገረች ብሎ ሲወቅሳት ነበር። እውነተኛ የትዳር ችግር ነበር፦ የሚለብሱት ልብስም ሆነ ገንዘብ አልነበራቸውም። ጌታ በሰዓቱ ደረሰ። የሠሩትም ነገር ምን ዓይነት ውጤት እንዳመጣ አሳያቸው። የእግዚአብሔርን ቃል አካፈላቸው። ለቤተሰቡም አዲስ ልብሶችን አዘጋጀ። እንዴት ያለ ጉብኝት ነው! ይህ ጉብኝት የሰውን ልጅ ታሪክ አቅጣጫ ለወጠ።

እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው አለበሳቸውም።

ዘፍጥረት 3፡21

2. ሰዎችን ለማበረታታት የሚደረግ ጉብኝት

እግዚአብሔር አብርሃምን ጎበኘ

አብራምም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነው ጊዜ **እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና፦** እኔ ኤልሻዳይ ነኝ በፊቴ ተመላለስ፣ ፍጹምም ሁን . . . ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፣ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል፣ ለብዙ አህዛብ **አባት** አድርጌሃለሁና።

ዘፍጥረት 17፡1-5

አብርሃም ለብዙ ዘመናት በትዳር ሕይወት ውስጥ ቆይቶ አንድም ልጅ ሊወልድ አልቻለም ነበር። ይህ ደግሞ ለቤተሰቡ ታላቅ ችግር ነበር። በያህዌ በተጎበኘበት ወቅት፣ የሚያበረታታ ቃል መጣለት። አባት ትሆናለህ! ውድ መጋቢ፣ አብርሃም በነበረበት ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆነህ እነኚህ ቃላቶች ምን ዓይነት የማበረታታት ውጤት እንዳላቸው መገመት ትችላለህ?
ሰዎችን በጎበኘሁባቸው ብዙ ጊዜዎች፦ እንዲህ ብለውኛል። "በጣም ተበረታታሁ።" የፍቅር፣ የጸሎት እና የቃሉ ውህደት ወደር አይገኝለትም።

3. የመምከር እና የመምራት ጉብኝት

እግዚአብሔር ይስሐቅን ጎበኘ

እግዚአብሔር ተገለጠለት እንዲህም አለው፦ ወደ ግብፅ አትውረድ፣ እኔ በምልህ ምድር ተቀመጥ እንጂ።

ዘፍጥረት 26፡2

በይስሐቅ ከተማ ውስጥ የኢኮኖሚ ውድቀት ነበር። ለጉዞው ቪዛ ሲጠባበቅ፣ ተነበኘ። በጉብኝቱም ወቅት ምክርን ተቀበለ። ጌታ እንዲህ ብሎ ተናገረው፣ “ሌላው ሁሉ የሚጓዘውን ዓይነት ጉዞ አትጓዝ።” እግዚአብሔር ይጠብቅሃል!

በዚያች ምክር ምክንያት የይስሐቅ ሕይወት ለዘላለም ተለወጠ! የብዙ ሰዎች ሕይወት ምክርን ባገኙበት ጉብኝት ምክንያት ለዘላለም ተለውጧል። ለጉብኝት ስትወጣ፣ ራስህን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ምክርን እና ምሪትን እንደሚያመጣ ሰው ተመልከት።

4. በግን የተሰጠ፣ የተቀባ እና አስራት የሚከፍል የሚያደርግ ጉብኝት

እግዚአብሔር ያቆብን ጎበኘ

> ያዕቆብም ከእንቅልፉ ተነስቶ በእውነት **እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው** እኔ አላወቅሁም ነበር አለ።

ዘፍጥረት 28፡16

ያዕቆብ ከጌታ ጉብኝትን አገኘ። እርሱ ብዙ ሰዎችን ያታለለና ወደ ኋላ ያፈገፈገ ሰው ነበር። በዚያ ምሽት፣ ሕይወቱ ለዘላለም ተለወጠ፣ ጠማማ የሆነው ሰው ተቃና። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ የተሰጠ “ክርስቲያን” ሆነ! አስራቱን ለመክፈል እና የቤተ ክርስቲያንን ግንባታ ለመደገፍ ቆረጠ። ጉብኝት እንዴት ያለ ለውጥ ማምጣት ይችላል! በመጋቢ አገልግሎት ውስጥ ጉብኝት እንዴት ያለ ኃይለኛ መሣሪያ መሆኑን ታያለህ?

> ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ስእለት ተሳለ፦ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፣ በምሄድበትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ፣ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ፣ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ፣ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል፣ ለሐውልት የተከልሁት ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፣ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ።

ዘፍጥረት 20፡20-22

ውድ ወዳጄ፣ ወደ ጉብኝት ስትሄድ፣ ለአባላቶችህ ስለ መስጠት ተናገራቸው። አስራታቸውን እንዲከፍሉ ንገራቸው። ስለ መለኮታዊ ጥበቃ እና የመትረፍረፍን በረከት አስተምራቸው። ጉብኝትህ በሕይወታቸው ውስጥ ዘላቂ ውጤት ይኖረዋል።

5. አንድን አባል እግዚአብሔር ይናገረው ዘንድ ትኩረቱን ለመሳብ የሚደረግ ጉብኝት

እግዚአብሔር መሴን ነበኝ

> የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው፤ እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነደድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ።
>
> ዘጸአት 3፡2

ሙሴ በሕይወቱ "የመቅበዝበዝ" ሕይወት ውስጥ ነበር። ለአርባ ዓመታት ያህል ሕይወቱ መልካም ባልሆነ ሁኔታ ውስጥ ነበር። አንድ ጉብኝት ያንን ሁሉ ለወጠ።

አንዳንድ ጊዜ በመጋቢ የሚደረግ ጉብኝት አንድን የቤተ ክርስቲያን አባል እግዚአብሔር በግሉ እንደሚያውቀው ለማሳየት ትኩረቱን ሊስብ ይችላል። የዚህ ውጤት አብዛኛውን ጊዜ አስደናቂ ነው! ሰዎች በእግዚአብሔር እንደሚታሰቡ ሲረዱ አስደናቂ ለውጥ ይመጣል። በሙሴ ላይ እንደሆነው፣ የረጅም ዘመን የማፈግፈግ ሕይወት በአንድ ጉብኝት ያበቃል።

ምዕራፍ 33

ቋሚ የሆነ ለውጥ የሚያመጡ አምስት ጉብኝቶች

የኢየሱስ ክርስቶስ ጉብኝቶች

1. ለብዙዎች ሕይወት ደህንነት ያመጣ ጉብኝት

ኢየሱስ ዓለምን ጎበኘ

> **ስተቀበሉት ሁሉ ግን፣** በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።

ዮሐንስ 1፡12

ይህ በጣም የምወደው የኃይለኛ ጉብኝት ምሳሌ ነው፡- ዓለምን ለዘላለም የለወጠ ሦስት ዓመት ተኩል። **ይህ በዘመናት ውስጥ ሁሉ ከሁሉም በላይ የሆነ የጉብኝት ክስተት ነው። ይህ የጉብኝቶች ሁሉ እናት ነው ዓለምን ለዘላለም የለወጠ ጉብኝት!**

ኢየሱስ ስለመጣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ደብዳቤ ሊጽፍልን ይችል ነበር። መልአክ መላክ ይችል ነበር። ግን ራሱ መጣ። ያ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ያሳያል። ብዙ ሰዎች ለዚህ ፍቅር ምላሽ ሰጥተዋል። የዚህ ጉብኝት ፍሬዎች በሁሉ ስፍራ ይገኛሉ። የምታየው የቤተ ክርስቲያን

ህንፃ ሁሉ የዚህ ጉብኝት ውጤት ነው። የምታየው ክርስቲያን ሁሉ የዚህ ጉብኝት ውጤት ነው። የወንጌል አገልጋይ ሁሉ የኢየሱስ የሦስት ዓመት ተኩል የዓለም ጉብኝቱ ውጤት ነው።

ጉብኝት ደህንነት ሊያመጣ ይችላል። ክርስቶስ ምድርን መጎብኘቱ ለሚሊዮኖች ደህንነት አምጥቷል። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመራሁበት ብዙ ጉብኝቶች አሉ። ከእነዚህም ሰዎች ውስጥ አንዳንዶቹ በክርስቶስ ጸንተው አይቼአለሁ። ሰዎች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በእንባ ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ሲሰጡ አይቼአለሁ። ለጉብኝት ስትሄድ፣ በቤተሰብ ውስጥ ያልዳኑትን ሁሉ ማገልገልህን እርግጠኛ ሁን። ሁል ጊዜ በጉብኝትህ ወቅት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መምራትን አስታውስ።

2. ፈውስን ያመጣ ጉብኝት

ኢየሱስ የጴጥሮስን ቤት ጎበኘ

> **ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ** አማቱን በንዳድ ታማ ተኝታ አያት እጅዋንም ዳሰሰ፣ ንዳዱም ለቀቃት ተነስታም አገለገለቻቸው።

ማቴዎስ 8፡14-15

በጉብኝት ወቅት፣ ለታመመም ልትጸልይ ትችላለህ። ቅባቱ በውስጥህ እንዲያልፍ እግዚአብሔርን እመን። ምናልባት የፈውስን ስጦታ የምትሞክርበት ብቸኛ እድል ጉብኝት ሊሆን ይችላል።

3. ተአምራትን ያመጣ የጉብኝት ጥያቄ (ጥሪ)

የኢየሱስ የኢያኢሮስን ቤት ጉብኝት

> እነሆም፣ አያኢሮስ የሚባል ሰው መጣ፣ እርሱም የሙከራብ አለቃ ነበር በኢየሱስም እግር ላይ ወድቆ **ወደ ቤቱ እንዲገባ ስመነው**።

ሉቃስ 8፡41

የእግዚአብሔርን ኃይል የለመድነው ጥቅጥቅ ባለ ጉባዔ ብቻ ነው። እግዚአብሔር መንቀሳቀስ የሚችለው በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲኖሩ ብቻ ይመስለናል። አንድ ምስጢር ላካፍልህ። ኢየሱስ ድንቅ የሆኑ ተአምራቶችን ለጥቂቶች ዓይን ብቻ እንዳቆየ ታውቃለህ? ለምን በሺዎች ፊት በውሃ ላይ አልተረማመደም? ማዕበሉን ሲገስፅ፣ ለምን ለእርሱ በተሰጡ አሥራ ሁለት ሰዎች ፊት ብቻ አደረገው? ኢየሱስ የጴጥሮስን ታንኳ በብዙ አሳዎች ሲሞላና መስጠም ስትጀምር ያዩት ጴጥሮስ፣ እንድሪያስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ ብቻ እንደነበሩ ታውቃለህ? ከሙታን ሲነሳ ለምን ራሱን በሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች አላሳየም?

ውድ ወዳጄ፣ እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢርን እወቅ! እግዚአብሔር የማንንም ትኩረት መሳብ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር በአንድ ሰው ቤት ውስጥ ታላቅ ተዓምራትን ማድረግ ይችላል። የእግዚአብሔርን ኃይል ለማገልገል ነፃ ሁን።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲወድቅ ያየሁት በመኝታ ቤት ውስጥ ነው (በቤተ ክርስቲያን አዳራሽ ውስጥ አይደለም)። አንድን ወጣት ሳገለግል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደቀ። የሆነውን ያየ አንድም ሰው አልነበረም ግን በእርግጥ ሆኗል!
ለጉብኝት ስትወጣ፣ ለእግዚአብሔር ኃይል ተዘጋጅ!

4. ትምህርት እና ለቤተሰብ ምክርን ያመጣ ጉብኝት

ኢየሱስ ማርያምን እና ማርታን ጎበኘ

> ሲሄዱም እርሱ ወደ አንዲት መንደር ገባ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም **በቤትዋ ተቀበለችው።**
>
> **ሉቃስ 10:38**

ኢየሱስ ሁሉንም ዓይነት ጉብኝቶች አድርጓል። ሁለት ሴቶችን ጎብኝቶ መልካም የሆነ ቤተሰብአዊ ምክር ሰጣቸው። ማርታን ከሚገባው በላይ የማድቤት ሥራ እንደምታበዛ ነገራት። በሌላ አነጋገር ይበልጥ መንፈሳዊ መሆን እንደሚገባት መከራት። በሰው ቤት ውስጥ በሁሉም ነገር ላይ አስተያየት መስጠት አትችልም። ከዚያ ሰው ጋር ትክክለኛው ግንኙነት ካለህ ልትናገር ትችላለህ። ካልሆነ፣ አፍህን ዘግተህ ቀጥል! በማያገባህ ነገር ውስጥ ገብተህ ብትናገር ችግር ውስጥ ልትገባ ትችላለህ።

. . . ሰነፍ ሰው ቁጣውን ሁሉ ያወጣል. . .

ምሳሌ 29፡11

5. ማኅበራዊ ግንኙነት እና ቀጥተኛ ተግሳፅን ያመጣ ጉብኝት

ኢየሱስ አንድ ፈሪሳዊን ጎበኘ

ይህንንም ሲናገር አንድ ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምሳ ይበላ ዘንድ ለመነው **ገብቶም ተቀመጠ**

ሉቃስ 11፡37

ኢየሱስ ሁሉንም ዓይነት ሰዎች ጎብኝቷል ስለዚህ አንተም ሁሉንም ዓይነት ሰዎች መጎብኘት አለብህ። ይህንን ፈሪሳዊ ሲጎበኝ፣ ብዙ ተግሳጾች ነበሩ። በፊቱ የተዘረጋው ገበታ ኢየሱስን አላስፈራራውም፣ አንተም መፍራት የለብህም።

ከምሳም በፊት አስቀድሞ እንዳልታጠበ ባየው ጊዜ ፈሪሳዊው ተደነቀ። ጌታም እንዲህ አለው አሁን እናንተ ፈሪሳዊያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ **ታጠራላችሁ፣ ውስጣችሁ ግን ቅሚያና ክፋት ሞልቶበታል።**

ሉቃስ 11፡38-39

ይህ ጉብኝት ኢየሱስ ለግብዞች ጠንካራ ተግሳጾችን ያመጣበት ሆነ። ኢየሱስ ጋባዦቹን ሰነፎች እንደሆኑ ነገራቸው!

ምዕራፍ 34

የቤተ ክርስቲያን አባላቶችን ያጸኑ አምስት ጉብኝቶች

የጳውሎስ ጉብኝቶች

1. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ያመጣ ጉብኝት

ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖችን ጎበኘ

> አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ **ወደ ኤፌሶን መጣ፤ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ**። ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፣ ትንቢትም ተናገሩ።
>
> የሐዋርያት ሥራ 19፡1፤6

በጉብኝት ሰዓት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ለማገልገል አታቅማማ። **የሚገበኝ አገልጋይ ተንቀሳቃሽ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነው**። በመንፈስ ቅዱስ ስትቀባ መልካም ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። በአንድ ሰው ቤት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ሳገለግል ትዝ ይለኛል። ይህ ሰው በጣም ተደስቶ ነበር። ከአንድ ሰዓት በላይ በልሳን ተናገረ። ይህ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጣ ብጠብቅ ኖሮ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በምንም ዓይነት ላያገኝ ይችል ነበር።

2. ጎብረት ለማጎልበት የሚደረግ ጉብኝት

ቆጵሮስንም ባየናት ጊዜ በስተ ግራችን ተውናት ወደ ሶርያም ሄደን ወደ **ጢሮስ ደረስን**፤ መርከቡ ሸክሙን በዚያ የሚያራግፍ ነበርና ደቀ መዛሙርቱንም ባገኘን ጊዜ በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጥን፤ እነርሱም ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ በመንፈስ አሉት፤ **ጊዜውንም በፈጸምን ጊዜ** ወጥተን ሄድን . . .

የሐዋርያት ሥራ 21፡3-5

አንዳንድ ጊዜ ጎብረትን ለመገንባት ጉብኝት ማድረግ ያስፈልጋል። ለአንድ መጋቢ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር ግንኙነቱን ማጠንከር አስፈላጊ ነው። ጉብኝት ግንኙነትን ለመገንባት ውጤታማ መንገድ ነው። ጳውሎስ በአንዳንድ ቦታ የተወሰኑ ቀናቶችን ሲያሳልፍ ከዚህ ሌላ ምክንያት አልነበረውም።

3. *መጋቢዎችን ለመመልመል የሚደረግ ጉብኝት*

ጳውሎስ ደርቤንና ልስጥራን ጎበኘ

ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራንም ደረሰ እነሆም፤ በዚያ አንዲት ያመነች አይሁዳዊት ልጅ ጢሞቴዎስ የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ . . . ጳውሎስም ይህ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ ወደደ፤ . . .

የሐዋርያት ሥራ 16፡1፤3

በጉብኝት ወቅት አስገራሚ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። በጉብኝት ወቅት ነበር ጳውሎስ መጋቢ ሊሆን የሚችል ሰው የለየው። ይህ መጋቢ ማን ነበር? ጢሞቴዎስ ሆኖ ተገኘ። ጳውሎስ ደርቤንና ልስጥራን ባይጎበኝ ኖሮ፣ የተወሰኑ ሰዎች ጢሞቴዎስ የሚባል መጋቢ ባልኖራቸው እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጢሞቴዎስ የሚባል መጽሐፍ ባልኖረ ነበረ።

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት፣ ከቤተ ክርስቲያን ሁለት ሰዓት የመኪና ጉዞ በኃላ የሚደርስበት ቦታ የሚኖሩ ሰዎችን መጎብኘቴን አስታውሳለሁ። ይህን ሳደርግ፣ ያ ጉብኝት ወዴት እንደሚያመራ የማውቀው ነገር አልነበረም ዛሬ፣ በዚያ በጉብኝት አማካኝነት ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጣ ሰው የሚመገብ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አለኝ። እኔም በጉብኝት "ጢሞቴዎስን" መልምዬአለሁ። ለጉብኝት ስትወጣ መጋቢዎችን ስትመለምል ይታየኛል!

4. የቤተ ክርስቲያን አባላትን ለማበረታታት የሚደረግ ጉብኝት

ጳውሎስ ገላቲያ እና ፍርግያን ጎበኘ

> ጥቂት ቀንም ቆይቶ ወጣ፣ ደቀ መዛሙርቱንም ሁሉ እያጸና **በገላቲያ አገርና በፍርግያ በተራ አለፈ።**

የሐዋርያት ሥራ 18፡23

ስለ ሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን። ምን ያህል የተለያዩ ቦታዎችንና ሰዎችን እንደጎበኘ ታያለህ? ይህን ሥራ ባይሠራ ኖሮ፣ ከቤተ ክርስቲያን ምን ይወጣ ነበር? ለጉብኝት በወጣ ጊዜ ሁሉ፣ በጎችን ታበረታለህ። ኢየሱስ ግልገሎቹን ስታበረታታ በፍቅር ፈገግታ ይመለከትሃል።

5. ቤተ ክርስቲያንን ለማነቃቃት የሚደረግ ጉብኝት

ጳውሎስ መቄዶንያን እና ግሪክን ጎበኘ

> . . .ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን አስመጥቶ መከራቸው፣ ተሰናብቶአቸውም ወደ መቄዶንያ ይሄድ ዘንድ ወጣ ያንም አገር እያለፈ **በብዙ ቃል ከመከራቸው** በኋላ ወደ ግሪክ አገር መጣ። በዚያም ሦስት ወር ተቀምጦ ወደ ሶሪያ . . .

የሐዋርያት ሥራ 20፡1-3

ጳውሎስ፣ አይነተኛ የሆነ እረኛ፣ መቄዶንያን እና ግሪክን ጎበኘ። አንዳንድ ጊዜ አንድን ቤተሰብ በሙሉ ልትጎበኝ ትችላለህ። አንድ ሰው ብቻ መጎብኘት የለብህም። በዚህ ጉብኝት ወቅት ምን ያህል ማነቃቃት እንደተደረገ

አስተውል፡፡ በምትጎበኝበት ጊዜ ሁሉ ቃል ማካፈልህን አትርሳ፡፡ ቃሉ ኃይል አለው! ሕይወትን ይለውጣል! ከፍልስፍና እና ጥበብ ከሚመስል ሀሳብ ይለያል፡፡ በጉብኝት ጊዜ እንኳ ከቃሉ ጋር ሁን! በጉብኝት ጊዜ የጳውሎስን ምሳሌ ተከትለህ አነቃቂ ሁን፡፡

ክፍለ ፬

ማስተማር

ምዕራፍ 35

ስኬታማ የቃሉ አስተማሪ ለመሆን የሚጠቅሙ አሥራ አምስት ቁልፎች

እንደልቤም የሆኑ፣ በዕውቀትና በማስተዋል የሚመሯችሁን እረኞች እሰጣችኋለሁ።

ኤርምያስ 3፡15

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

1. **በማያቋርጥ ዝግጅት ውስጥ ሁን**

   በማንኛውም ሰዓት ለስብከት ልትጠራ ትችላለህ። ይህን እውነት ስታውቅ ሁል ጊዜ ዝግጁ ትሆናለህ።

2. **በየዕለቱ የጥሞና ጊዜ ይኑርህ**

   አብዛኛቹ መልእክቶቹ በየዕለቱ ከማደርገው የግል የጥሞና ጊዜ የመጡ ናቸው። አገልጋይ ሆነህ በየቀኑ የጥሞና ጊዜ ከሌለህ፣ መሠረትህ ደካማ ነው።

3. **ሁል ጊዜ መጽሐፍቶችን አንብብ**

   የምታነበው መጽሐፍ ሊኖርህ ይገባል። እኔ ሁል ጊዜ እያነበብሁት ያለ መጽሐፍ ሊኖርህ ይገባል። አብዛኛውን ጊዜ የማነባቸው መጽሐፍት ከምሰብከው ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። ይህ ሁል ጊዜ በማያቋርጥ ዝግጅት ውስጥ እንድሆን ይረዳኛል።

4. ሁል ጊዜ የስብከት ካሴቶችን አድምጥ

ሁል ጊዜ በእጄ ላይ የማዳምጣቸው ካሴቶች ይኖሩኛል። ይህን ነው በማያቋርጥ ዝግጅት ውስጥ መሆን ብዬ የምጠራው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እንዴት የተለያዩ የስብከት ኃላፊነቶችን መፈጸም እንደምችል ይገርማቸዋል። ይህን ማድረግ የቻልሁት ሁልጊዜ በማያቋርጥ ዝግጅት ውስጥ ስለሆንሁ ነው።

5. እእያንዳንዱ ስብከት በቃሉ ላይ የተመሰረተ ይሁን

ምንጭህ ወንጌል ይሁን። መጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ማስተማሪያ መጽሐፍ ነው። አገልግሎትህን የመሰረትህበት ዋና ዐለት ይሁን። ወርቅ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ ናስ በሆነ ዓለማዊ ትምህርት አትተካ።

6. ለእያንዳንዱ ትምህርት ግልጽ የሆነ ዓላማ ይኑርህ

ግብህ ምንድር ነው? ሰዎች እንዲድኑ ወይስ እንዲፈወሱ? ግልጽ ዓላማ ካለህ ምን ማለት እንደሚገባህ ይመራሃል።

7. ለመልእክትህ ትክክለኛ ርዕስ ስጥ

ሦስት ዓይነት ዋነኛ ርዕሶች አሉ። የወንጌል *ርዕሶች፣ የማነቃቂያ ርዕሶች እና የትምህርት ርዕሶች።*

የወንጌል ርዕሶች አስደናቂ ይዘት አላቸው። ጉባኤው ደንገጥ እንዲል የታቀዱ ናቸው። አንዳንዴ በኃጢአተኞች ልብ ውስጥ ፍርሃት ያመጣሉ። የእነኚህ ምሳሌዎች፡-

- "አንተ ነጎድጓድ ከዚህ ራቅ"
- "እንደመሰለህ መሆን ትችላለህ"
- "ዝምታ በሰማያት"
- "የፍርድ ቀን እየመጣ ነው 1፣ 2፣ 3"
- "ወደ ሲኦል ወረዱ"

የማነቃቂያ ርዕሶች አጭር እና ቀልብን የሚስቡ ናቸው፡፡ ጉባዔውን ለማበረታታት የታቀዱ ናቸው፡፡

እነኚህም ምሳሌዎች፡-

- “ልጄ ሆይ፣ ትችያለሽ”
- “ልጄ ሆይ የሚያሳሱ ዓይኖች አሉሽ”
- “አንቺ ሴት፣ ነፃ ወጥተሻል”
- “እጄን መታጠብ እችላለሁ?”

የማስተማርያ ርዕሶች ግልፅ መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የተለያዩ ደረጃዎችን፣ መርህዎችን ወይም ቁልፎችን በተራ ቁጥር ያሳያሉ፡፡ **ማንኛውንም የማነቃቂያ መልዕክት ትክክለኛውን ርዕስ በመስጠት ወደ ትምህርት ርዕስ መቀየር ትችላለህ፡፡** ከአንድ የማነቃቂያ ርዕስ ብዙ የተለያዩ የትምህርት ስብከቶችን ማግኘት ትችላለህ፡፡ እስቲ (አንቺ ሴት፣ ነፃ ወጥተሻል) የሚለውን የማነቃቂያ ርዕስ ወደ ትምህርት ርዕስ በመቀየር ልምምድ እናድርግ፡፡

- “ነፃ የወጣች ሴት ለመሆን የሚጠቅሙ *ሦስት አርምጃዎች*”
- “ነፃ የወጣች ሴት ለመሆን የሚጠቅሙ *ሰባት መርህዎች*”
- “ነፃ የሆንሽ ሴት ልትሆኚ የሚገባበት *አራት ምክንያቶች*”
- “ነፃ ሴት የመሆን *አሥር ጥቅሞች*”
- “ነፃ የሆነች ሴት *ሰዶስት ሕጎች*”
- “ነፃ የወጣች ሴት ለመሆን የሚያስችሉ *ሰባት መንገዶች*”
- “ነፃ የወጣች ሴት *አምስት ስህተቶች*”
- “ነፃ ስለወጣች ሴት እያንዳንዱ ክርስቲያን ማወቅ የሚገባው *አሥር ነገሮች*”
- “ነፃ የወጣች ሴት ማለት ምን ማለት ነው?”
- “ነፃ የወጣች ሴት ለመሆን የሚረዱ *ሃያ አምስት ቁልፎች*”
- “ነፃ የወጣች ሴት *አራት የሕይወት ምዕራፎች*”

- “ነፃ የወጣች ሴት *ኣሥራ ሁለት ምሥጢሮች*”
- “ነፃ የወጣች ሴት *ኣሥራ ኣንድ ሰልቶች*”
- “እንዴት ነፃ የወጣች ሴት መሆን ትችያለሽ?”
- “ነፃ የወጣች ሴት *ሰባት ምልክቶች*”
- “ነፃ መውጣት የሚያስፈልጋት ሴት *ኣራት ምልክቶች*”

በይበልጥ የተቀናጁ የትምህርት መልእክቶችን ለማዘጋጀት ይህን እንደ ፎርሙላ ልትጠቀምበት ትችላለህ። በመጀመሪያ የፈለግኽውን ያህል ነጥቦች ምረጥ። ከዚያም አብሮት የሚሄደውን ትክክለኛ ቃል ውሰድ፣ (መርህዎች፣ ሕጎች፣ ቁልፎች፣ ምሥጢሮች) ሊሆን ይችላል። ትክክለኛው ርዕስ ሲኖርህ የማስተማር አገልግሎትህ ወደ ሌላ ደረጃ ተሸጋግሮ ታገኘዋለህ።

8. በስብከትህ ውስጥ ቅደም ተከተል ሊኖር ይገባል

በስብከትህ ውስጥ ቅደም ተከተል መኖሩን ለማረጋገጥ ቀላሉ መንገድ በነጥቦች መስበክ ነው። በሦስት፣ አምስት፣ ሰባት እና እስከፈለግኽው ድረስ ነጥቦችን በመጠቀም ማስተማር ትችላለህ። ሰዎች የምትከተለውን ቅደም ተከተል ማየት እንዲችሉ አድርግ። ይህን አስታውስ፦ አንድ ስብከት ብቻ የምትሰብክ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ሦስት ነጥቦች ይበቃሉ። ለአንድ ጊዜ ስብከት የምትጠቀመው ከፍተኛው የነጥቦች ብዛት ከሰባት መብለጥ የለበትም። በአንድ ስብከት ውስጥ ሃያ አምስት ነጥቦችና ለማስተማር ብትሞክር፣ ያለ ጥርጥር ችግር ውስጥ ትገባለህ።

9. ስብከትህን ጠበቅ ባለ ማሳሰቢያ ደምድም

10. ስብከትህ በጣም ረጅም ወይም በጣም አጭር አይሁን

11. ያለ መስኮት በፍፁም አትስበክ (ማብራሪያዎች፣ ታሪኮች፣ ምሳሌዎች፣ ወዘተ)

ማብራሪያ ወይም የራስህ ምሳሌነት የሌለበት መልእክት ማለት ልክ አንድ ህንፃ ያለ መስኮት እንደ መሥራት ነው። ኢየሱስ ያለ ማብራሪያና ያለ መስኮት በፍፁም አስተምሮ አያውቅም። የብኩኑ ልጅ ታሪክ፣ በኢያሪኮ መንገድ ወንበዴዎች የደበደቡት ሰው፣ የአልአዛር እና የሀብታሙ ሰው ታሪክ የእንዲህ ዓይነቱ የማስተማር ዘይቤ ጉልህ ምሳሌዎች ናቸው። ልጆችም ሆኑ አዋቂዎች እነኚህን ታሪኮች በፍፁም አይረሱም። የማስተማር አገልግሎትህ እያደገ በመጣ ቁጥር፣ ይበልጥ የኢየሱስን አገልግሎት እየመሰለ ይሄዳል።

12. ሁል ጊዜ ለደህንነት የነፍሳት ጥሪ አድርግ

የእግዚአብሔር መንግሥት ዋነኛ ውጊያ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ነው። ከፍተኛው ወንጌልን አለማገልገል ሰዎችን ወደ ኢየሱስ መጋበዝ አለመቻል ወይም መዘንጋት ነው።

13. ሁል ጊዜ ከመገለጥ ጋር ሁን

እግዚአብሔር መገለጦች ስለሰጠህ ነገሮች ስበክ። እንዲያው ዝም ብለህ የግልህ መገለጥ ሳይኖርህ፣ የሰው ስብከት ብትሰብክ፣ ምንም ተፅዕኖ ማምጣት አትችልም! በርግጥም ሰነፍ ልትመስል ትችላለህ! ያልተረዳኸውን ውስብስብ ነገር ለመናገር አትሞክር። አጣብቂኝ ውስጥ ሳይገባ ስለ ብዙ ነገሮች መስበክ ይቻላል!

14. ለቅባቱ ገስግስ

በተደጋጋሚ ስትሰብክ፣ ቅባቱ በላይህ ላይ ሲመጣ ታውቃለህ። ብሎም በስብከትህ ጊዜ ቅባቱ እንዲፈስ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ታውቃለህ። በቅባት ውስጥ ለመስበክ የሚረዱ ሁለት ቁልፎች የሚከተሉት ናቸው

i. ቀዝቃዛ የሆነ አካባቢን ለመስበር እና ወደ ቅባት ለመግባት ጥቂት ቃላትን በልሳንና በግልፅ መናገርን ልመድ

ii. ከመገለጥ ጋር መሆን የተቀባ ስብከትን ያመጣል። የግልህን መገለጥ በመናገር ከድርቀት ወደ ተቀባ ስብከት ግባ

15. በምትሰብክበት ጊዜ አምስት የቅባት ምልክቶችን ፈልግ። በቅባት መስበክ በአምስት ዋነኛ ምልክቶች ይገለጣል

ሀ. በሥልጣን መስበክ (ማርቆስ 1፡22)

ለ. ሕይወትን የመለወጥ ውጤት የሚያመጣ ስብከት (የሐዋርያት ሥራ 4፡4)

ሐ. ብዙ ሰዎች እንዲሰበሰቡ የሚያደርግ ስብከት (ማርቆስ 1፡32)

መ.ቀጥተኛ እና ልብን የሚሰነጥቅ ስብከት ነው (የሐዋርያት ሥራ 2፡37)

ሠ. የጊዜው ስብከት ነው (ሉቃስ 13፡ 4፣5)

ምዕራፍ 36

እያንዳንዱ መጋቢ ጉባኤውን እንደ እግዚአብሔር እርሻ ሊመለከት የሚገባበት አራት ምክንያቶች

የእግዚአብሔር እርሻ(የሕትከልት ቦታ፣ መስክ) ናችሁ፣ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና፣

1ኛ ቆሮንቶስ 3፡9

እያንዳንዱ መጋቢ ጉባኤውን እንደ እግዚአብሔር አትክልት ቦታ፣ መስክ ወይም የእርሻ ቦታ ሊመለከት ይገባዋል። የእግዚአብሔርን ጉባዔ እንደ እግዚአብሔር እርሻ ስትመለከት፣ የስብከት እና የማስተማር አገልግሎት ምን እንደሚያደርግ ይገባሃል። የምትዘራው የዘር ዓይነት የምታጭደውን የመከር ዓይነት ይወስነዋል።

- **እያንዳንዱ መጋቢ በእያንዳንዱ ስብከት ራሱን ዘርን እንደሚዘራ ገበሬ ሊመለከት ይገባዋል**

አንዴ ይህ መገለጥ ከገባህ፣ የሚኖርህ የጉባዔ ዓይነት ምንም ምስጢር አይኖረውም። ነፍሳትን የሚማርክ ጉባዔ ካለህ፣ ያ ለራስህ ያጨድከው መከር ነው። እያንዳንዱ ገበሬ የዘራውን ያጭዳል። በቆሎ ከዘራህ፣ በቆሎ ታጭዳለህ። አናናስ ከዘራህ አናናስ ታጭዳለህ።

መጋቢው ገበሬ ነው። ጉባዔ ደግሞ የእርሻ ቦታ ነው። መጋቢው በሰበከ ጊዜ ሁሉ፣ የሆነ ዓይነት ዘር እየዘራ ነው። **የሚያጭደውም መከር ያንኑ የዘራውን ዘር ዓይነት ነው።**

አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች በበለጸጉ እና ስኬታማ በሆኑ ሰዎች ቢሞሉ የሚደንቅ አይደለም። ይህ የሚሆነው መጋቢው ስለ ብልጽግና እና ስለ ስኬት በቋሚነት ስለሚያስተምር ነው። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች የወንጌል መልዕክተኛ(ሚስዬናዊነት) አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች የተሞሉ ናቸው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት መጋቢው ስለ ወንጌል መልዕክተኝነት(ሚስዮናዊነት) ሁል ጊዜ ስለሚሰብክ ነው።

አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ስለ ተዓምራት ይሰብካሉ። በእነኚህ ቤተ ክርስቲያኖች ተዓምራቶች ቢሆኑ ምንም አይደንቅም። አንዳንድ መጋቢዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን መስፋት ያስተምራሉ እናም ያንኑ ያጭዳሉ።

ውድ መጋቢ፣ አንድ ገበሬ የቲማቲም መከር ቢያጭድ የሚደንቅ ነው? በርግጥ አይደለም! ቲማቲም ተክሎ ነበር ማለት ነው! በእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ ምን እየተከልህ ነው? ጉስቁልናን ፍርሃትን እና ውድቀትን እየሰበክህ ነው? ወይስ ድልን፣ ብልጽግናን እና እምነት?

- **የአጭር ጊዜ የቃሉ መከሮች አሉ**

የአጭር ጊዜ መከሮች ስል ምን ማለቴ ነው? በእያንዳንዱ አገልግሎት፣ ማንኛውም የምትሰብከው ነገር የአጭር ጊዜ መከር ዘር ነው። የጥርጥር እና የፍርሃት ስብከት ብትሰብክ፣ የተዓምራት መከር አታጭድም። ስለ ደህንነት ብትሰብክ፣ ሰዎች ይድናሉ።

መከሩን አየሁ

በአንድ ክሩሴድ የሰበክሁትን አስታውሳለሁ። ስለ ደህንነት እያስተማርኩ እያለ፣ ጉባዔው ረጭ ብሎ ነበር። በቅንነት ሆነው ይህን የደህንነት መልእክት ያደምጡኝ ነበር። የሆነ ሰዓት ላይ፣ ስለ ፈውስ መናገር ጀመርሁ። እግዚአብሔር ይፈውሳችኋል ስል ለጉባዔው ተናገርሁ። ፈጣን የሆነ ምላሽ ከጉባዔው መምጣት ጀመረ! ሽባዎች ከዊልቸር ላይ መነሳት ጀመሩ፣ ስለ ፈውስ በተናገርኩ መጠን የታመሙ ሰዎች ይፈወሱ ጀመር። በዚያ ቅስፈት

የአጭር ጊዜ መከር እያጨድሁ ነበር። ስለ ተዓምራቶች ስናገር የተአምራት መከር እያጨድሁ ነበር።

እግዚአብሔር እግዚአብሔር ከሆነ፣ በየስብከቱ ተመሳሳይ ነገር ማድረግ አለበት ብዬ አስብ ነበር። በአገልግሎት እያደግሁ ስሄድ፣ እንደዚያ እንዳልሆነ ተረዳሁ። የእግዚአብሔር አትክልት ቦታ የመሆናችን እውነታ እየተጫነኝ መጣ። የተዓምራት አገልግሎት እንዲኖረኝ ከፈለግሁ፣ ስለ ተዓምራት እና ስለ ፈውስ ማስተማር አለብኝ ማለት ነው። የሚያደምጠኝ ጉባዔ የእግዚአብሔር መስክ እንደሆነ አውቃለሁ።

ጐረቤትህ ያለው ገበሬ የስንዴ መከር ማጨዱ ካላስደነቀህ፣ ቤኒሂን በአገልግሎቱ የተአምራት መከር ማጨዱ አያስደንቅህ። ሁል ጊዜ ስለ ተአምራት ይሰብካል። ይህ የሚሆነው ከእግዚአብሔር አትክልት ቦታ የፈውስ መከር ማጨድ ስላለበት ብቻ ነው።

- **የቃሉ የረጅም ጊዜ መከሮች አሉ**

እያደረግሁ ያለሁትን ሳላውቅ፣ በእግዚአብሔር እርሻ ውስጥ የሆነ ዓይነት ዘር ስዘራ ነበር። ስለ ታማኝነት አስተምሬ፣ ከእርሻው ታማኝ የሆኑ ሰዎች መከር አጨድሁ። ስለ አገልግሎት እና ስለ ሚስዮናዊ ሥራ ሰበክሁ። ዓመታት እያለፉ ሲመጡ፣ እግዚአብሔር በብዙ ሠራተኞች እና ሚስዮናዊያን ባረከኝ።

- **በእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ መርህ ልታምን ይገባሃል**

ይህ መርህ ትክክለኛውን ነገር እንድትሰብክ ይመራሃል። መከሩን ለማጨድ አትቸኩል። ሁል ጊዜ በመዝራት እና በማጨድ መካከል የሚወሰድ ጊዜ አለ። ከዚህ በኋላ፣ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ስለ ምን እንደምትናገር ተጠንቀቅ። ስላለህ ነገር ሳይሆን ስለምትፈልገው ነገር ስብክ! ዓመታት እያለፉ ሲመጡ፣ ስታስተምር የነበረው ነገር ትክክለኛ ውጤት የሆነ ጉባዔ እንዳለህ ትገነዘባለህ።

ምዕራፍ 37

አንድ መጋቢ ተከታታይ ትምህርት ሊያስተምር የሚገባበት ሰባት ምክንያቶች

አንዳንድ መጋቢዎች በየእሁዱ አዲስ ስብከት አላቸው። በየሳምንቱ መገለጥ እና መነቃቂያ ይዘው ይመጣሉ። ይህ የሚመከር ነው። ይሁን እንጂ፣ በጐች በመገለጥ ሊኖሩ አይችሉም! ቋሚ፣ የማያቋርጥ እና የተመጣጠነ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። ቤተ ክርስቲያንህ እንዲያድግ፣ ለብዙ ዓመታት በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚቆዩ ሰዎች ሊኖሩ ይገባል። በቋሚነት የምትሰጣቸው ነገሮች ሊኖር ይገባል። ለዚህ ነው ተከታታይ ትምህርት ማስተማር እንዳለብህ የማምነው። በእርግጥ፣ ተከታታይ ያልሆኑ የማነቃቂያ መልእክቶች ማምጣት የሚገባህ ጊዜ አለ። የሚከተሉት ለምን ተከታታይ ትምህርት ማስተማር እንደሚገባህ የሚያሳዩ ሰባት ነጥቦች ናቸው።

- ተከታታይ ስብከት *ሁል ጊዜ የሚመጣ ጉባዔ እንዲኖርህ የሚያደርግ ምርጥ መንገድ ነው።* በየሳምንቱ የሚያደምጡህ አንድ ዓይነት ሰዎች እስካሉህ ድረስ፣ ትክክለኛው መልእክት ሊኖርህ ይገባል።

- ተከታታይ ስብከት የተለያዩ ዓይነት መልእክቶችን በየሳምንቱ ከመስበክ *ለመጋቢ ይቀላል።* ለዚህም ምክንያቱ ተከታታይ ስብከት አንድ መልእክት ሆኖ ወደ ትናንሽ ስብከቶች የተቆራረጠ ስብከት ነው። አንድ ረጅም ስብከት ማዘጋጀት ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እና ለመንጋው ደረጃ በደረጃ የሚለቀቅ ነው።

- ተከታታይ ስብከት መስበክ *አባላቶች ለሚመጣው ሳምንት የሚጠባበቁት ነገር እንዲኖር ያደርጋል።* የመጠባበቅ አየርን ይፈጥራል።

- ተከታታይ ስብከት አባላቶች የትምህርቱን መደምደሚያ ለመስማት *ከሳምንት ወደ ሳምንት ተመልሰው እንዲመጡ ያደርጋቸዋል።* ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ሰዎችን ብዛት ያሳድጋል።

- ተከታታይ ስብከት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሰጡ የሚገባቸውን *ረጅም ግን በጣም አስፈላጊ ርዕሶችን ለመሸፈን* ብቸኛ መንገድ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ በአርባ አምስት ደቂቃ ውስጥ ስለ ጋብቻ ማስተማር የሚገባውን በሙሉ አስተምሮ መጨረስ በፍጹም አይቻልም።

- ተከታታይ ስብከት መስበክ መጋቢው *የአገልግሎቱን ሰዓት በተገቢው መጠን ለማሳጠር ያስችለዋል።* መጋቢው ማለት የሚገባውን ሁሉ በአንድ ሳምንት ለመጨረስ ውጥረት ውስጥ አይገባም። መልዕክቱን በሚቀጥለው ሳምንት የመጨረስ እድል እንዳለው ያውቃል።

- ተከታታይ ስብከት በመጋቢው እና በጉባዔው መካከል *ትስስርን ይፈጥራል።* ቋሚ የሆነ ምግብ ለማግኘት በእርሱ ላይ ይደገፋሉ። ሁል ጊዜ ከሚመግብህ ሰው ጋር ግንኙነት ይኖርሃል!

ምዕራፍ 38

የማስተማር አገልግትህን የሚያሳድጉ አራት ቁልፎች

ምናልባት የማስተማር አገልግሎትህ ሊያድግ ይገባዋል። ማደግ ትችላለህ። ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የሚያሸጋግሩህን አራት ደረጃዎች ላካፍልህ።

1. *ያለ ማስታወሻ ስበክ።* ያለ ማስታወሻ መስበክ እያነበቡ ከመስበክ ይልቅ ይበልጥ ይስባል። ምንም እንኳ (ራሴ እንደማደርገው) አንተም ማስታወሻ ቢኖርህም፣ ለምትናገረው እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በማስታወሻህ ላይ የምትደገፍ አትሁን።
2. *ሦስት ዋነኛ ነጥቦችን ከሦስት ዋነኛ ጥቅሶች እና ሦስት ዋና 'መስኮቶችን' በማሰላሰል ያለ ማስታወሻ መስበክን ልመድ።* መስኮቶች የሕይወት ምሳሌነት፣ ማብራሪያ እና ታሪኮች ናቸው። ማስታወሻ ሳታነብ በምትሰብክበት ጊዜ፣ ከአሥር ነጥቦች ይልቅ ሦስት ዋነኛ ነጥቦችን ማስታወስ ይቀላል። እነኚህ ሦስት ነጥቦች ከሦስት ጥቅሶች እና 'መስኮቶች' ጋር ይቆራኛሉ።
3. ከእሁድ ስብከትህ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን የትምህርት *ካሴቶች ያለ ማቋረጥ አድምጥ።* ለሚመጡ የስብከት እድሎች ከዓመት በፊት በመዘጋጀት ጀምር።

4. ***ያለማቋረጥ አሰተምር።*** **ቃሉን የምታገለግልበት ሳምንታዊ እድል ሊኖርህ ይገባል።። ሁል በቋሚነት የሚሰብክ ማንኛውም ሰው የመሻሻል እድል ይኖረዋል።። አለፎ አልፎ ብቻ የምትሰብክ ከሆነ፣ የስብከት አገልግሎትህ በዝቅተኛ ደረጃ ይቆያል።።**

ምዕራፍ 39

የስብከት ካሴቶች ማድመጥ የስብከት አገልግሎትህን የሚለውጥበት ሰባት ምክንያቶች

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

ሮሜ 10፡17

1. ካሴቶችን ማድመጥ የእግዚአብሔርን ቃል እንድታውቅ ይረዳሃል

እያንዳንዱ አገልጋይ ጥልቅ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሊኖረው ይገባል። ቃልን ለማሰላሰል ቀላሉ መንገድ ካሴቶችን ማድመጥ ነው። ሰባኪው ጥቅሶችን ሲጠቅስ ስለምትሰማ ቃሉን ለማስታወስ ይረዳሃል።

2. ካሴቶችን ማድመጥ በእግዚአብሔር ቃል እንድትረሰርስ ይረዳሃል

ካሴቶችን ስታደምጥ ለአገልግሎትህ ምሪቶችን ትቀበላለህ። ሁል ጊዜ በአንድ መልእክት ውስጥ ብዙ መልእክቶች ይኖራሉ። መጋቢ እንደመሆንህ፣ እግዚአብሔር አገልግሎትህን በተመለከተ ስለ ተለያዩ ነገሮች ሲናገረህ ትሰማለህ።

3. ካሴቶችን ማድመጥ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ እንድትሆን ይረዳሃል

አንዴ የእግዚአብሔር ቃል መሰበክ ከተጀመረ፣ የተቀባ ከባቢ አየር ይፈጠራል። መጋቢዎች ሁሉ በዚህ አይነት ከባቢ አየር ውስጥ መቆየት አለባቸው ምክንያቱም በማንኛውም ሰዓት ለአገልግሎት ልትጠራ ትችላለህ።

ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለ ጊዜውም ጽና፣ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርክ፣ ዝለፍ ገሥጽ ምከርም

2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡2

4. ካሴቶችን ማድመጥ ቅባቱን እንድትይዝ ይጠቅምሃል

ጴጥሮስ ሲሰብክ፣ መንፈስ ቅዱስ በጉባዔው ላይ ወረደ (የሐዋርያት ሥራ 10:44) እጅግ በጣም በእርግጠኝነት፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲመጣ፣ ቅባቱ ይወርዳል። ካሴቶችን በብዛት ባደመጥህ ቁጥር፣ ይበልጥ የተቀባ ትሆናለህ (ቅባቱን ተቀበል የሚለውን መጽሐፌን አንብብ)

5. ካሴቶች ማድመጥ የተለየ ዓይነት የአሰባበክ ዘይቤ እንዲኖርህ ይረዳሃል

ካሴቶችን ስታደምጥ፣ የተለየ ዓይነት የአሰባበክ ዘይቤን ታዳብራለህ። የተለየ የአሰባበክ ዘይቤ ማዳበር እግዚአብሔር እንድታገለግለው ለጠራህ ህዝብ የምትሰብ እንድትሆን በጣም አስፈላጊ ነው። በእንግሊዝኛ እንዲህ የሚል አባባል አለ፣ "ለየመንጋው ለራሱ የተለየ ዓይነት በትር ሊኖረው ይገባል።" ሁሉም ሰው ወደ አገልግሎትህ አይሳብም። ግን በእርግጥ እግዚአብሔር ለሰዎች አስነስቶሃል።

6. ካሴቶችን ማድመጥ አንድ አገልጋይ ሊኖረው የሚገባውን መረጃ እንዲኖርህ ይረዳሃል

ካሴቶችን ማድመጥ እግረ መንገዱን የሚመጡ ብዙ ጥቅሞች አሉት። ካሴቶችን ስታደምጥ ሁል ጊዜ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ትለቅማለህ። ስለ ብዙ የሕይወት ገጽታዎች የሚያውቅን ሰባኪ ማድመጥ የተሻለ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ጥሩ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የሳይንስ፣ የሕክምና፣ የሕግ፣ የጂኦግራፊ፣ ስነ ጽሑፍ እና የኢኮኖሚክስ እውቀት የመልእክት አቀራረብን ያሻሽላል።

7. ካሴቶችን ማድመጥ የማያቋርጥ እና ያልታቀደ የአገልግሎት ሥልጠና እንድታገኝ ይረዳሃል

የአገልጋይ ስልጠና የሚያጠነጥነው በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ ነው። በቃሉ ስትረሰርስ፣ ያለማቋረጥ ምክርን ታገኛለህ። ሳትጠይቅ ምክርን መቀበል እንዴት መባረክ ነው።

ምዕራፍ 40

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት አስተምህሮን መመስረት ይቻላል

ዘሪው ዘርን ለመዝራት ሲወጣ፣ ከአራቱ ዘሮች ውስጥ አንዱ ብቻ በመልካም መሬት ላይ ወድቆ አበበ። መጽሐፍ ቅዱስ ያ ዘር የእግዚአብሔር ቃል እንደ ነበር ያስተምረናል (ማርቆስ 4:14) ከጉባዔው ውስጥ አንድ አራተኛው ብቻ ለመልዕክቱ ትክክለኛ ምላሽ የሚሰጥ ከሆነ፣ ያ መልዕክት ከመመስረቱ (ከመጽናቱ) በፊት በተደጋጋሚ መስበክ አለብህ ማለት ነው።

አንድ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልፎ አልፎ ብቻ ከሆነ፣ ያ አስተምህሮ በጉባዔው ውስጥ ሲመሠረት አይችልም። ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ የተወሰኑ እውነቶችን በጉባዔው ውስጥ መመስረት አለባቸው። መርሆች እና አስተምህሮዎች ካልተመሰረቱ መታነጽ ሊመጣ አይችልም።

> ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ . . .
>
> ዕብራዊያን 6፡1

ጉባዔህ ገና በቤተ ክርስቲያን አመራር ጽንሰ ሀሳብ ላይ እየታገለ ካለ፣ ችግር አለብህ። ጉባዔህ ገና በአስራት ጽንሰ ሀሳብ ላይ እየታገለ ካለ፣ ገቢህ ለስሙ ያህል ይሆናል።

ውድ ወዳጄ፣ መሠረታዊ አስተምህሮዎች ካልተመሠረቱ እንዴት ወደ ታላላቅ ነገሮች መገለል ትችላለህ?

በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ አስተምህሮን እንዲመሠረት የሚያደርጉ ስድስት ደረጃዎችን ላካፍልህ እነኚህ ደረጃዎች ቀላል በሆነ ጥቅስ ላይ የተመሠረቱ ናቸው

. . . በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ **ነገር ሁሉ(አስተምህሮ)** እንዲጸና . . .

ማቴዎስ 18፡16

አንድ ዓይነት ነገር የሚናገሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሰባኪዎች ሲኖሩ አስተምህሮ ይመሠረታል። ማንኛውም ቤተ ክርስቲያን፣ ሁሉም አገልጋዮች አንድ ዓይነት ነገር የሚናገሩ ከሆነ፣ ያ ቤተ ክርስቲያን የተባረከ ነው! የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ደጋግሞ ሲነገር ከኃይል ጋር ወደ ፊት ይገሰግሳል።

በቤተ ክርስቲያንህ አስተምህሮን የሚመሠርቱ ስድስት እርምጃዎች

1. **የተመሰከተውን ትምህርት በተከታታይነት አስተምር**
2. **ሴላ እህት ትምህርት በሴላ ተከታታይ ትምህርት አስተምር ስምሳሴ ያህል፣ ስለ ጸሎት ካስተማርህ ስለ ፃም ልታስተምር ትችላለህ**
3. **ያንኑ ትምህርት ለሁለተኛ ጊዜ አስተምር**
4. **ቆየት ብለህ፣ ረዳትህ ያንኑ ትምህርት እንዲያስተምር አድርግ**
5. **እንደገና፣ የሴል መሪዎች ወይም እረኞች በሴላ ጊዜ እንዲያስተምሩ አድርግ**
6. **ተጋባዥ አገልጋዮች በዚያው ርዕስ ጉባዔህን እንዲያስተምሩ አድርግ**

ዋናው መጋቢ፣ ረዳቱ፣ ሌሎች መሪዎች እና ተጋባዥ አገልጋይ እንኳ አንድ አስተምህሮ ሲያስተምር፣ ያ አስተምህሮ ይመሠረታል። አንዳንድ ጊዜ ስለ ታማኝነት እንዳስተምር እጋብዛለሁ ግን አንድ ስብከት ታማኝ ያለመሆንን ባህል ወደ ታማኝነት እንደማይለወጥ አውቃለሁ። መልእክቱ እስኪ መሠረት ድረስ ደግሞ ደጋግሞ መስበክ ያስፈልጋል። የሁለት ወይም **ከዚያ በላይ ስብከቶች አፍ አስተምህሮን ያጸናል!** አንዳንድ ነገሮች ከመመስረታቸው በፊት ከአመት በላይ የማያቋርጥ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል።

ምዕራፍ 41

መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰብኩ የሚገባበት ሰባት ምክንያቶች

1. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ የቤተ ክርስቲያንህ አባላቶች ለሕይወታቸው ምሪትን ያገኛሉ

የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡

2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16-17

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የተጻፈ ቃል ይሏል፡፡ ለሁላችንም አስተማማኝ የሆነ ምሪት ምንጭ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተሰጠን የሕይወትን ምሪት እንድናገኝ ነው:: የምናደርገው ነገር ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይገባዋል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ፣ የእግዚአብሔር ቃል ለሕይወታችን ፍጹም የሆነ መመሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሊነሳ ለሚችል ማንኛውም ዓይነት ጉዳይ መመሪያ የያዘ ልዩ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ዘመን ተግባራዊ ያልሆነ እና አግባብነት ያሌለው ነው ብለው የሚያስቡ ብዙዎች አሉ፡፡

አንዲት ሴት መጽሐፍ ቅዱስ ፋሽን ያለፈበት ስለሆነ ዝሙት መፈጸም እንደምትችል እንደምታምን ነገረችኝ፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ የብዙ ዓመት

የወንድ ወዳጇ ሲተዋት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜው ያለፈበት እንዳልሆነ ድንገት ተረዳች።

መጽሐፍ ቅዱስ ለዛሬ ክርስቲያን አትራፊ፣ ጠቃሚ፣ አግባብነት ያለው፣ እና ተግባራዊ ነው! ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ እንድትከፍት የማይፈልጉ ግን ትንቢትና መገለጥን ብቻ የሚፈልጉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ።

2. ቃሉን ስትሰብክ፣ ጉባዔው ለጨለማው ብርሃንን ያገኛል

ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን ነው

መዝሙር 119፡105

በዓለም ብዙ ጨለማ አለ። አብዛኛውን ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባን አናውቅም፣ ግን እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች ብርሃን አዘጋጅቷል። ይህ እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች ያዘጋጀው ብርሃን ምንድር ነው?
ቃልህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን ነው። የእግዚአብሔር ቃል መብራትና ብርሃናችን ነው። መብራቱን ስታበራ ብቻ ነው ወዴት መሄድ እንደሚገባህ የምታውቀው መብራት ስታበራ ብቻ ነው ራስህን በዕቃ ከመደናቀፍ ልታድን የምትችለው። ኢየሱስ ራሱን የዚህ ዓለም ብርሃን ብሎ ጠርቷል።

> . . . እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ **የሕይወት ብርሃን** ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም . . .

ዮሐንስ 8፡12

በዚህ ሕይወት ብርሃን ያስፈልግሃል! ኢየሱስ(ቃል) የሕይወትህ ብርሃን ነው። ሕይወታቸውን ያለ ክርስቶስ እና ያለ ቃሉ ለመምራት የሞከሩ ሰዎች በጨለማ ውስጥ መደናቀፍ ስቃይ እንዳለው ተገንዝበዋል።

አንድ ወጣት ቀረበኝና በትዳር ውስጥ ከፍተኛ ችግር እንደገጠመው ነገረኝ። እንድረዳው ፈለገ። ከጋብቻ ችግር ውስጥ መውጫውን ለማወቅ ፈለገ። ሳናግረው የሚያስፈልገው ቃሉ እንደሆነ ተረዳሁ። ግን እንዲህ አለኝ፣ "ነፃ

እንድወጣ ትጸልይኛለህ?" እኔም እንዲህ ስል ጠየቅሁት "ለምንድን ነው ነፃ መውጣት የሚያስፈልግህ?" እርሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ፣ "ኦ፣ ሚስቱ የጥልቁ መንፈስ እንዳለባት ተደርሶባታል።" እኔም፣ "የጥልቁ መንፈስ ምንድር ነው?" ስል ጠየቅሁት። "ኦ! ከዚህ መንፈስ ነፃ ልትወጣ ይገባሃል ብለውኛል። ስለዚህ ነፃ እንድታወጣኝ እፈልጋለሁ" አለኝ። ለራሴ እንዲህ ብዬ አሰብኩ፣ "ይህ ሰው አቋራጭ ይፈልጋል። ቃሉን አይፈልግም እንደ እግዚአብሔር ቃል ምንም ነገር ነፃ ሊያወጣህ እንደማይችል አያውቅም።"

እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም ነጽነት ያወጣችኋል. . .

ዮሐንስ 8፡32

መጠየቄንም ቀጠልሁ "ዳግመኛ የተወለድህ ክርስቲያን ነህ?" "አዎ ነኝ" "ለሚስትህ ታማኝ ነህ" ብዬ ጠየቅሁ ፈገግ አለና "እ . . .በርግጥ አይደለሁም፤" "በርግጥ፣" ብሎ ቀጠለ፣ "በፍፁም ታማኝ ሆኜላት አላውቅም!" ይህን ሰው መጋቢ እንዲኖረው እና የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆን መከርኩት።

እንዲህ አልኩት "የጥልቁ መንፈስህ ከችግሮችህ ሁሉ ትንሹ ችግር ነው። የሚያስፈልግህ በዚህ ሕይወት የእግዚአብሔር ቃል ምሪት ነው። *የሕይወት ብርሃን ያስፈልግሃል፣* አለበለዚያ ግን በጨለማ ውስጥ መደናበርህን ትቀጥላለህ።"

የምሰብካቸውን ነገሮች እንዴት እንደማውቅ የሚገርማቸው ሰዎች አሉ አስታውሳለሁ፣ ለአንድ ኮንፈረንስ ጆሃንስበርግ ስደርስ ከደቡብ ተወካዮች ጋር ተገናኘሁ። ሲያዩኝ አንደኛው እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣ "ቢሾፑ አንተ ነህ?" እኔም "አዎ እኔ ነኝ" ብዬ መለስሁለት። "እውነት! ስንጠባበቅ የነበረው ሽምገል ያለ ሰው ነበር! ካሴቶችህን አድምጠናል መጽሐፎችህንም አንብበናል። እንዲያው፣ ትንሽ ጠና ያልህ ሰው መስለኸን ነበር።" አለኝ። የእግዚአብሔር ቃል ሲኖርህ፣ ጥበብህ ከዕድሜህ በላይ ይሆናል። ከዕድሜ እኩዮችህ ይልቅ በጣም የበሰልህ ትሆናለህ።

3. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ጥበበኞች ይሆናሉ

. . .ትዕዛዝህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ። ምስክርህ ትዝታዬ(የማሰላስለው) ነውና ካስተማሩኝ ሁሉ ይልቅ አስተዋልሁ።

መዝሙር 119፡ 98-99

ውድ መጋቢ፣ ጥበበኛ የቤተ ክርስቲያን አባሎች እንዲኖሩህ ትፈልጋለህ፣ የረጉ እና አስተዋይ ሰዎች በጉባዔህ ውስጥ እንዲኖሩ ትፈልጋለህ? ከሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ። የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ሕይወት ጥበበኛ ያደርግሃል። ለሥራህ ምክርና ምሪት ከእግዚአብሔር ቃል ታገኛለህ። ለአንድ የንግድ ሰው ከንግድ አስተዳደር (ቢዝነስ ማኔጅመንት) ትምህርት ይልቅ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የበለጠ መመሪያ ያገኛል። ስለ ፍልስፍና፣ ስለ ፖለቲካ ሳይንስ፣ ስለ ሥነ ጽሑፍ እና ስለ ታሪክ ከማውቀው የትኛውም መጽሐፍ ይልቅ የበለጠ ትክክለኛ እና ተግባራዊ እውቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ።

4. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ያውቃሉ

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች "እግዚአብሔር ይህን እና ያንን እንዳደርግለት ጠራን፣" ሲሉ ፈገግ እላለሁ። **በቃሉ ውስጥ ያለውን ቀላል ትዕዛዝ ሳትታዘዝ፣ እግዚአብሔር የላቀ ትዕዛዝ የሚሰጥህ ይመስልሃል?** በትንሹ የታመነ በትልቁ ይታመናል። አስራትህን እና መባህን ክፈል የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ካልታዘዝህ፣ እግዚአብሔር ስለ ሌላ ነገር የሚናገርህ ይመስልሃል?

ሰው ሆይ፣ መልካሙን ነግሮሃል፣ እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው?

ሚኪያስ 6፡8

እግዚአብሔር ቃሉን በመጋቢዎች እና በእረኞች አማካኝነት ያገለግላል። ለዚያ ነው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር መልካም ቤተ ክርስቲያን እና መጋቢ ሊኖርህ በጣም የሚገባው።

5. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ ክርስቲያኖች በህይወታቸው ውስጥ ምን እየሆነ እንደሆነ ያውቃሉ፣ ይገነዘባሉ

በመጨረሻው ዘመን፣ እግዚአብሔር በእውቀት እና በመረዳት የሚመግቡን መጋቢዎችን እየሰጠን ነው። እግዚአብሔር በመጋቢዎችህ አማካኝነት የሚሰጥህን እውቀት እና ማስተዋል አሁን ተቀበል!

> እንደ ልቤም በግ ጠባቆችን እሰጣችኋለሁ፣ በእውቀትና በማስተዋልም ይጠብቁአችኋል (ይመግቡአችኋል)።

ኤርሚያስ 3፡15

ከእውቀት እና ማስተዋል ሌላ፣ እግዚአብሔር አንድን የእግዚአብሔር ሰው ለክርስቲያኖች ትዕዛዛትን ለመስጠት ይጠቀምበታል። እነኚህ ትዕዛዛት በሕይወታችን የተሻሉ ሰዎች እንድንሆን ይረዱናል። መጋቢህ ጾምና ጸሎት የሚያዝህ ጊዜ ይኖራል። እንኚህን ትዕዛዞች መከተል በጣም አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእኛ ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች መታዘዝ እንደሚገባ ያስተምረናል።

> የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።

ዕብራዊያን 13፡7

የቤተ ክርስቲያን አባሎች የእረኞቻቸውን ድምፅ መስማት አለባቸው። እግዚአብሔር የበጎችን ዕጣ በእረኞች እጅ አስቀምጧል። እግዚአብሔር በእረኛህ ድምፅ ውስጥ ሕይወትህን ይባርካል፣ ይመራል። መልካሙና የእረኞች ሁሉ እረኛ ኢየሱስ ነው፤ እናም ጴጥሮስን በጐቹን ጠብቅ አለው። ያ ማለት የበጎቹን ጥበቃ ለእረኞች ውክልና ሰጥቷል ማለት ነው። ውድ መጋቢ፣

የሚያስፈራ ኃላፊነት አለብን እናም ይህን ልንፈጽም የምንችለው ከቃሉ ጋር *ስንሆን ብቻ* ነው።።

> . . . በጐቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፣ ከሌላው እንግዳ ከሆነ ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፣ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።።
>
> ዮሐንስ 10፡4

6. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ፣ ኃጢዓት ከጉባዔው ውስጥ ተቃጥሎ ይወጣል

የኃጢአተኞች ጉባኤ እንዲኖርህ ትፈልጋህ? ሞራል የጐደለው ጉባዔ ትፈልጋለህ? የሴትኛ አዳሪዎች የዕፅ አዘዋዋሪዎች፣ የውሸታሞች፣ የሌቦች እና የነፍሰ ገዳዮች ጉባዔ እንዲኖርህ ትፈልጋለህ? እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ!

እንግዳ ይሆንብህ ይሆናል እኔ ግን እንደዚያ ዓይነት ጉባኤ አይቼአለሁ።። የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ፣ ኃጢዓትን የሚያቃጥል እሳት ትለኩሳለህ።።

> . . . **በአፍህ ውስጥ ቃሌን እሳት** ይህንም ሕዝብ እንጨት **አደርጋለሁ፣ ትበላቸውማለች**
>
> ኤርምያስ 5፡14
>
> በውኑ ቃሌ እንደ **እሳት** . . . አይደለችምን?
>
> ኤርምያስ 23፡29

7. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ ግትር በሆኑ ሰዎች ውስጥ ስሜትን ይደቁሳል

> በውኑ ቃሌ . . . ድንጋይንም እንደሚያደቅቅ **መዶሻ** አይደለችምን?
>
> ኤርምያስ 23 : 29

ሁል ጊዜ ጠንካራ ኩርኩም የሚሰጥ ትምህርት ቤት መግባት የሚያስፈልጋቸው ግትር ሰዎች አሉ። ቃሉን መስበክ ግትር በሆኑ ሰዎች ውስጥ ስሜትን ይቀሰቅሳል።

8. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ ሰዎች የእውነት ይድናሉ

> በወንጌል አላፍርምና . . . ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።
>
> ሮሜ 1፡16

የእግዚአብሔር ቃል ካልተሰበክ ሰዎች የእውነት አይድኑም። የቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆኑ ይችላሉ ግን የእውነት አይድኑም። ደህንነት የእግዚአብሔር ቃል መሰበክ ውጤት ነው። ዓለማዊ የስኬት ትምህርቶች የደህንነት ኃይል የላቸውም!

9. የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ እግዚአብሔር የጉባዔውን ጥልቅ ሀሳብ የመረምራል

የውስጥ ሀሳባቸውን የማይገልጡ ብዙ ሰዎች አሉ ምን እንደሚያስቡ በፍጹም አታውቅም። ብዙውን ጊዜ የማይጨበጡ እና ጥያቄዎችን በቀጥታ የማይመልሱ ናቸው። ልባቸው ሊደርስ እና ሊያገለግላቸው የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው!

> የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም፣ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ **የልብንም ስሜትና ሃሳብ ይመረምራል**።
>
> ዕብራዊያን 4፡12

ምዕራፍ 42

መሪዎችህን ማስተማር የሚገባበት ሰባት ምክንያቶች

እያንዳንዱ መጋቢ ከመሪዎቹ ጋር ልዩ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሊኖረው እንደሚገባ አምናለሁ። መሪዎችን ማስተማር አንድ መጋቢ ሊሠራ የሚችለው በጣም ውጤታማ የሆነ እንቅስቃሴ ነው።

መሪዎችን ስታሰተምር፣ በአገልግሎትህ ውስጥ ሴት እና ወንድ ልጆችን ታፈራለህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተፃፉ ደብዳቤዎች ውስጥ ሁለት ጠቃሚ የሆኑ ደብዳቤዎች የተጻፉት ለመሪ እንዲሆነ አስተውለሃል? 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ መጽሐፍት የተጻፉት ለአንድ መጋቢ ነበር። እነኚህ ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያኑን በሙሉ ለመጥቀም ሲባል የተጻፉ አልነበሩም። ለረዳት መጋቢ ጢሞቴዎስ በሐዋርያው ጳውሎስ የተሰጡ ትምህርቶች ነበሩ።

መጋቢዎች እና መሪዎች ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል። ልዩ ትምህርቶችን ለመቀበል ከሌላው ጉባኤ *መለየት* ያስፈልጋቸዋል። እኔ ይህን ሁሌ አደርጋለሁ እናም በመቶዎች የሚቆጠሩ ወንድ እና ሴት ልጆች በአገልግሎት ውስጥ አፍርቼአለሁ። ይህን ማድረጌ በዓለም ላይ መጋቢዎችን እና እረኞችን አስነስቷል።

ከመሪዎችህ ጋር ልዩ እና ቋሚ የሆነ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከሌለህ፣ ቤተ ክርስቲያንህ ትክክለኛ ዓይነት ሠራተኞች አይኖራትም። መሪዎች በልዩ ሁኔታ ካልሠለጠኑ የቤተ ክርስቲያን እድገት ይቀጭጫል። ውድ ወዳጄ ማስተማር የሚገባህን ነገር ፈልግና መሪዎችህን ራስህ ማሠልጠን ጀምር። ምናልባት ለቤተ ክርስቲያንህ የሚያስፈልጋት ቁልፍ ይህ ሊሆን ይችላል።

> እንግዲህ፣ ልጄ ሆይ፣ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።
>
> 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡2

መሪዎችን ማስተማር አስፈላጊ የሆነበት ሰባት ምክንያቶች።

1. ለመሪዎች ስትሰብክ፣ እንደ እውነቱ ለሌሎች ለብዙ ሰዎች እየሰብክህ ነው። የእነኚህን መሪዎች ተከታዮችንም እያስተማርክ ነው።
2. መጋቢዎች የፍንዳታ እድገትን መርህ ማወቅ አለባቸው። ***እድገት ከፈለግህ፣ አባሎችህን አስተምር ግን የእድገትን ፍንዳታ ከፈለግህ፣ መሪዎችህን አስተምር!***
3. *መሪዎችን ማስተማር ከሥርህ በሚሠሩ መሪዎች ላይ ሥልጣን እንዲሰርጽ ያደርጋል።* ይህ የሚሆንበት ምክንያት በመሪዎች ላይ ሥልጣንህ የሚገለጠው ልትመግባቸው ስትችል ነው።
4. ተራ አባላትን ማስተማር በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሀብትን ማፍሰስ (ኢንቨስት ማድረግ) ነው። *መሪዎችን ማስተማር ለወደፊት ኢንቨስት ማድረግ ነው።* ያስተማርካቸው መሪዎች አንተ ስታልፍ ስራውን ይቀጥላሉ። ስኬት ያለ ወራሽ (ተተኪ) ውድቀት ነው!
5. *እያንዳንዱ መጋቢ መሪዎችን ማስተማር አለበት ምክንያቱም ኢየሱስ ሁል ጊዜ መሪዎችን አስተምሯል።* መጋቢዎች ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ከማስተማር ይልቅ ብዙ ጊዜያቸውን መሪዎችን በማስተማር ሊያጠፉ ይገባቸዋል። ይህ በኢየሱስ የተቀመጠ ምሳሌ ነው።

6. *መሪዎችን ማስተማር የእውነተኛ መሰፋፋት ትልቁ ቁልፍ ነው።* መሪዎችን ካላሰለጠንህ አንተን የሚወክል አይኖርህም።

7. *እያንዳንዱ መጋቢ መሪዎቹን ማስተማር አለበት ምክንቱም መሪዎች ካላስተማርካቸው በቀር ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በፍጹም አያውቁም።* ብዙ መጋቢዎች መሪ ሊሆኑ የሚችሉ በዙሪያቸው ያሉት ሰዎች ወሳኝ የሆኑ እውቀቶች በስርገት (Osmosis) የሚያገኙ ይመስላቸዋል። ሰዎች መሪነት ለመሆን ለተፈጠሩ ልዩ ሰዎች የመስላቸዋል። ስርገት የመሪነት ቁልፍ አይደለም ማስተማር እንጂ!

ምዕራፍ 43

ለምን “የውሸት ቃል” እና የሰይጣንን አስተምህሮዎች ልታስወግድ ይገባል

መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትን በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል፤

ነኛ ጢሞቴዎስ 4፡1

የአጋንንት ትምህርቶች

የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰብክ ወደ ሐሰት ትምህርት ወይም “ሲዶ ቃል” ትምህርት ማፈንገጥን ታስወግዳለህ። ግልፅ የሆኑ የሐሰት ትምህርቶችን ለመለየት ቀላል ነው። ከአንድ ማይል ርቀት ላይ ማንነታቸውን መናገር ትችላለህ! እንደ ጆሆቫ ምስክሮች እና ሞርሞን በደንብ የታወቁ የስህተት አስተምህሮዎች ናቸው። ብዙ ክርስቲያኖች እነኚህን ነገሮች መለየት አይቸግራቸውም። ብዙ መጋቢዎች እነኚህን ጉልህ ስህተቶች አይሰብኩም።

“የሐሰት ቃል”

ትክክለኛው አደጋ ያለው “ሲዶ(የሐሰት) ቃል” ትምህርት ብዬ በምጠራው ውስጥ ነው። “የውሸት ቃል” ትምህርት የሚመጣው ከሚያስት መንፈስ ነው።

ይህ የሚያስት መንፈስ አገልጋዮችን ወደ ሚያማልል የአገልግሎት ዓይነት ይስባቸዋል።

መጋቢዎች አብዛኛውን ጊዜ በሚያስደንቁ አከራካሪ ጉዳዮች ይሳባሉ። ብዙ ሻምፒዮን የሚያስፈልጋቸው ማህበራዊ ጉዳዮች አሉ። **ተናጋሪ የሚስፈልጋቸው ብዙ የፖስቲካ እና የሞራል ጉዳዮች አሉ።** እያንዳንዱ መጋቢ ራሱን ሊጠይቅ የሚገባው ጥያቄ፣ "የማኅበራዊ ጉዳይ ሻምፒዮን ለመሆን እግዚአብሔር ጠርቶኛል?" የሚል መሆን አለበት። "መሠረታዊ የሆኑትን የእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮዎች ትቼ ወደ እነኚህ "ግራጫ" አካባቢዎች መሄድ አለብኝ?" "ግራጫ" ብዬ የጠራኋቸው ወይ ዓለማዊ ወይም መንፈሳዊ ርዕስ መሆናቸው ስላለየላቸው ነው። ጥሪህ በ "ግራጫ" አካባቢ እንድትቆይ ከሆነ እግዚአብሔር በዚያ ይባርክሃል። ካልሆነ ጎበዝ የሆነ አጋንንት አባብሎ አስቶሃል። እያንዳንዱ መጋቢ ስለሚያስተምረው አስተምህሮ መጠንቀቅ አለበት።

> ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፣ በእነዚህም ጽና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።

1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡16

'የውሸት ቃል' ትምህርቶች አብዛኛውን ጊዜ ስለ ጥሩ ነገሮች እና ስለ ጥሩ ጉዳዮች ናቸው። **አንድ ነገር ጥሩ ጉዳይ ሲሆን ይችላል ግን ያ የእግዚአብሔር ቃል እንዲሆን አያደርገውም።**

'የሀሰት ቃል' አስተምህሮዎች የተወሰኑ ምሳሌዎችን ላሳይህ። *'የውሸት ቃል' ትምህርቶች እንደ ዓለማዊ የመሪነት ሥልጠና፣ ዓለማዊ ጥበብ ትምህርት፣ ዓለማዊ የስኬት ትምህርት፣ የፖለቲካ ዲስኩር፣ ስለ ማኅበራዊ እና የሞራል ጉዳዮች የሚደረግ ማኅበራዊ ዘመቻ፣ ሰሜትን የሚነኩ እንደ የጾታ ጉዳይ፣ የዘር ጉዳይ እና የቀለም ጉዳይ ወዘተ ብዙ ጉዳዮች አሉ።* እነኚህ ነገሮች በራሳቸው መጥፎ አይደሉም። ያለባቸው ብቸኛ ችግር የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ አስተምህሮ (ዶክትሪን) አለመሆናቸው ነው።

በእነኚህ ጉዳዮች ላይ መስበክ ትክክል አይደለም እያልኩ አይደለም። እግዚአብሔር እነኚህን ጉዳዮች ለማሳወቅ የጠራቸው ሰዎች እንዳሉ እርግጠኛ

ነኝ። ይሁን እንጂ፣ እነኚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ አስተምህሮዎች እንዳልሆኑ ማወቅ አለብህ። የእግዚአብሔር ቃል ዋነኛ ምንጭ አይደሉም። ወንጌል አይደሉም እናም ለደህንነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኃይል የላቸውም! (ሮሜ 1፡16)

የእግዚአብሔርን ቃል ከመስበክ ዋነኛ ምንጭ መንገድ አለመቀየርህን እርግጠኛ ሁን። የማዳን ኃይል ያለው ወንጌል ነው! ዓለማዊ የስኬት ትምህርቶች ነፍሳትን የማዳን ኃይል የላቸውም።

ውድ ወዳጄ፣ እግዚአብሔር እነኚህን ርዕሶች እንድታሳውቅ ካልጠራህና ትኩረትህ ካደረግሃቸው፣ ፍሬ አልባ ወደሆነ አገልግሎት አቅጣጫ ለውጠሃል ስልህ አዝናለሁ።

አንዳንዶች ከእነዚህ ነገሮች ዘወር ብለው ወደ ከንቱ ንግግር ተመልሰዋል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡6

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

መንግሥተ ሰማያትን በተመለከተ፣ ምናልባት ወደ ከንቱ ንግግር (ዋጋ ወደሌለው ጫጫታ) ፈቀቅ ብለሃል።

እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።

2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡4

ክፍለ ፫

ጎብረት ማድረግ

ምዕራፍ 44

ኅብረት ማድረግ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነበት ስምንት ምክንያቶች

ኅብረት ማድረግ መጋቢው ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት የአገልግሎት ዋነኛ ክፍል ሲሆን፣ መጋቢው ከጉባዔው ጋር ጠቃሚ ትስስር የሚመሠረትበት ነው። ከሰዎች ጋር ተራ ውይይት በማድረግ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር የግል ግንኙነት የሚመሠርትበት ነው። ኅብረት ማድረግ 'ከፑልፒት ውጭ' የሚደረግ ቁልፍ የሆነ አገልግሎት እና የቤተ ክርስቲያን እድገትን ለማምጣት ሙሉ በሙሉ መዳበር የሚገባው አገልግሎት ነው።

ሕብረት ማድረግ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነበት ስምንት ምክንያቶች

1. ኅብረት ማድረግ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲቆዩ ያደርጋል

ውድ መጋቢ ይህን አትርሳ! ሰዎች በተለያየ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ ይችሉ። ይሁን እንጂ፣ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የሚቆዩት በሚያውቋቸው እና ጓደኛ በሚያደርጓቸው ሰዎች ምክንያት ነው! ይህን ነው *የቤተ ክርስቲያን ሲሚንቶ* ብዬ የምጠራው። ቤተ ክርስቲያንህ እንድታድግ ከፈለግህ፣ ከአባሎችህ ጋር

ኅብረት አድርግና እነርሱም እርስ በርሳቸው ኅብረት እንዲያደርጉ አበረታታቸው!

2. ኅብረት ማድረግ ሰዎች ተፈላጊነት እንዲሰማቸው ያደርጋል

እያንዳንዷ ነፍስ በጣም አስፈላጊ ነች! በእርግጥ፣ በእያንዷንዷ ነፍስ ራስ ላይ ያለች እያንዳንዷ ጠጉር አስፈላጊ ነች። ጌታ በራሳችን ላይ ያለውን ጠጉር ብዛት እንደሚያውቅ ሲነግረን፣ ለእርሱ በጣም አስፈላጊዎች መሆናችንን እየነገረን ነው። በግል ኅብረት ማድረግ ሰዎች ተፈላጊነት እንዲሰማቸው የሚደርግ ቁልፍ ነው።

> . . . ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቆጠረ ነው. . .
>
> ሉቃስ 12፡7

3. ኅብረት ማድረግ ሰዎች ቁጥር ወይም ስታስቲክስ ብቻ እንዳልሆኑ እንዲሰማቸው ያደርጋል

ኢየሱስ አባቱ ከሰጠው በጎች አንድስ እንኳ እንዳላጠፋ ተናገረ። ለእግዚአብሔር ሁሉም አስፈላጊ ነው! ሁሉም ሰው መጥፋት የለበትም! ማንም ሰው ቁጥር ብቻ አይደለም። ማንም ሰው ከስታትስቲክስ ያላለፈ ነገር ተደርጐ መታየት የለበትም። ሕብረት ማድረግ ይህን ማረጋገጫ ነው።

4. ኅብረት ማድረግ ሰዎች መጋቢውን እውቅ ለማድረግ መጠቀሚያ እቃ እንዳልሆኑ እንዲሰማቸው ያደርጋል

> የንጉሥ ክብር በሕዝብ ብዛት ነው፤ በሰው ጥቂትነት ግን የሹም ጥፋት አለ።
>
> ምሳሌ 14፡28

ሰዎች ብዙ ሕዝብ ካለ፣ መጋቢው (ንጉሡ)፣ እንደሚከበር ያውቃሉ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መጋቢ እንዲታወቅ ለማድረግ መጠቀሚያ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። በግል ኅብረት ማድረግ ሰዎች እንዲህ እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል።

5. ጎብረት ማድረግ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የግል ግንኙነት የተሳሳተ ግምትን ይለውጣል!

የሳባ ንግሥት ስለ ሰለሞን የተሳሳተ ግምት ነበራት፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከእርሱ ጋር በግሏ ጎብረት ካደረገች በኋላ፣ አመለካከቷን ለወጠች በንጉሥ ሰለሞን በጣም ተደነቀች፡፡ እንዲህ አለች፣ "ካሰብኩት የበለጠ የተሻልክ እና ታላቅ ነህ፡፡"

> ንጉሡንም አለችው፡- ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው፡፡ እኔ ግን መጥቼ በዓይኔ እስካየሁ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም እነሆ፣ የጥበብህን ታላቅነት እኩሌታ አልነገሩኝም **ከሰማሁት ዝና ትበልጣለህ**፡፡
>
> 2ኛ ዜና 9፡5,6

እኔን በግላቸው ከማውቃቸው በፊት የተሳሳተ ግምት እንደነበራቸው የነገሩኝ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከሳሉኝ እጅግ የተለየሁ መሆኔን ማመን ያቅታቸዋል፡፡ ሕብረት ማድረግ የተሳሳተ ግምትን ፈጥኖ ፈጽሞ ያጠፋል!

6. ሕብረት ማድረግ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የግል ግንኙነት ሰዎች ይበልጥ የተሰጡ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል፡፡

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያንህ የተሰጡ ሰዎች እንዲሆኑ ከመድረክ ላይ በጣም ለመስበክ ሞክረሃል፡፡ ምናልባት የግል ጎብረት የተሰጡ አባላት ሆነው እንዲለወጡ ቁልፍ ሊሆን ይችላል፡፡

ኢየሱስ ከናትናኤል ጋር በባሕር ዳር ጎብረት ሲያደርግ ውጤቱ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የተሰጠ እንዲሆን አደረገ፡፡ የኢየሱስ ከናትናኤል ጋር ጎብረት ማድረግ እንዴት የተሰጠ ደቀመዝሙር እንዳደረገው ልብ በል፡፡

> ናትናኤል፡- ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው፡፡ ፊሊጶስ፡- መጥተህ እይ አለው፡፡ ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ፡፡ ናትናኤልም ከወዴት ታውቀኛለህ አለው፡፡

ኢየሱስም መልሶ ፊልጶስ ሳይጠራህ፣ ከበለስ በታች ሳለህ፣ አየሁህ አለው፤ ናትናኤልም መልሶ፡ መምህር ሆይ፣ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ አለው።።

ዮሐንስ 1፡47-49

7. ኀብረት ማድረግ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ኢየሱስ ኀብረት አድርጓል

ኢየሱስ ትልቅ ምሳሌአችን ነው።። የእርሱን ምሳሌ በመከተል ስለ አገልግሎት በጣም ልንማር እንችላለን።። ኢየሱስ ያደረገውን ማድረግ እፈልጋለሁ።። ይበልጥ ኢየሱስን መምሰል እፈልጋለሁ።።

በገሊላ ባሕርም አጠገብ ሲያልፍ ስምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፣ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና ኢየሱም፣ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ **አላቸው**።።

ማርቆስ 1፡16፣17

8. ኀብረት ማድረግ ሰዎች ልዩ የመሆን ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል

ሁሉም ሰው ልዩ የመሆን ስሜት እንዲሰማው ከሚያደርግ/ከምታደርግ ሰው ጋር መሆን ይፈልጋል።። ማንም ሰው ቁጥር ወይም ስታትስቲክስ መሆን አይፈልግም።። ሕዝብ ልዩ የመሆን ስሜት እንዲሰማቸው አድርግ እናም እንደ ሱፐር ግሉ (ሙጫ) ይጣበቁብሃል!

ምዕራፍ 45

ከሰዎች ጋር እንዴት ኅብረት ማድረግ እንደሚቻል

1. ከማታውቃቸው ሰዎች ጋር ኅብረት ለማድረግ ሆን ብለህ ወስን

ፍጹም እንግዳ ከሆነ ሰው ጋር መነጋገር ቀላል አይደለም። በሁሉም ሰው ውስጥ ካልታወቀ ሰው ጋር የመገናኘት ፍርሃት አለ። ይህ ደግሞ እንድንቆጠብ እና ከልክ በላይ ጠንቃቆች አንድንሆን ያደርገናል። ሰብረህ በመውጣት የሕይወት ውሃ ወንዝ ከውስጥህ በመውጣት ሰዎችን እንዲባርክ ፍቀድ።

2. ከጥልቅ ባህር ዓሣ ለማጥመድ ወስን

ከጥልቅ ባህር ዓሣ ማጥመድ ብዙ ሕዝብ መሃል በመግባት ፍጹም እንግዳ ከሆኑ ሰዎች ጋር ኅብረት ማድረግን ይጠይቃል። ልታደርገው ትችላለህ! በየእሁዱ አምስት እንግዳ የሆኑ ሰዎችን ለማነጋገር ወስን። ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ ሁሉም መጋቢዎች እና መሪዎች ፍጹም እንግዳ ከሆኑ ሰዎች ጋር መነጋገር አለባቸው። ይህ ስንጸልይበት ወደ ነበረው የቤተ ክርስቲያን እድገት ይመራል።

3. ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመጡ ሰዎች ንጹህ ፍላጐት እንዳለህ አሳይ

ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ያለ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ (ባለሥልጣን) አትምሰል። የውሸት ፈገግታን አስወግደህ ለሰዎች ንጹህ ፍላጐት ያለህ ሰው ለመሆን ወስን።

4. የወዳጅነት ፈገግታ ያለው ፊት ይኑርህ

. . . ነገር ግን ከወንድም አብልጦ የሚጠጋጋ ወዳጅ አለ።

ምሳሌ 18፡24

ፈገግ ማለትን መስታወት ፊት ለፊት በመቆም ተለማመድ አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮ ኮስተር ያለ ፊት አላቸው፤ እነኚህ ፈገግታ በጣም መለማመድ አለባቸው።

5. ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር ጎብረት ለማድረግ የግብዝነትን መንፈስ ግደል

ግብዝነት በሁሉም ሰዎች እንደበት ውስጥ አስቀያሚ ጣዕምን ያስቀምጣል። በምንም ዓይነት አስወግደው! ሀብታም የሚመስሉ ሰዎችን ስም ብቻ አትጠይቅ። ድሃ እና ያልተማሩ ለሚመስሉ ሰዎች ንጹህ ፍላጐት ይኑርህ። ኢየሱስ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር ጎብረት አድርጓል። ከቀራጮች፣ ከፈሪሳዊያን፣ ከመቶ አለቆች (ከመኮንንኖች)፣ ከአሣ አጥማጆች፣ ከእውሮች፣ ከእናቶች፣ ከተከበሩ ሰዎች እና ከሞቱ ሰዎች ጋር እንኳ ተነጋግሯል!

> ወንድሞቼ ሆይ፣ ክቡር በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ እንደመሆናችሁ አድልዎ አታድርጉ። የወርቅ ቀለበት ያደረገና ያማረ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባዔያችሁ ቢመጣ እንዲሁም ያደፈ ልብስ የለበሰ ድኻ ሰው ቢገባ፣ ያማረ ልብስ ለለበሰው

የተለየ አክብሮ በማሳየት፣ “ለአንተ የሚሆን መልካም መቀመጫ ይኸውልህ” ብትሉትና ድኻውን ሰው ግን፣ “አንተ በዚያ ቁም” ወይም “ከእግሬ በታች በወለሉ ላይ ተቀመጥ” ብትሉት፣ በመካከላችሁ አድልዎ ማድረጋችሁ

አይደለምን?

ያዕቆብ 2፡1-4

(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

6. ሰባቱን መሠረታዊ ጎብረት የማድረግ ጥያቄዎችን ጠይቅ

⇒ የሰዎችን ስም ጠይቅ

⇒ የት እንደሚኖሩ ጠይቅ

⇒ የት እንደሚሠሩ ጠይቅ

⇒ የት እንደሚማሩ ጠይቅ

⇒ እንዳገቡ ወይም በቅርቡ ሊያገቡ እንደሆነ ጠይቅ

⇒ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ መሆናቸውን ጠይቅ

⇒ ጓደኞቸው ልትሆን እንደምትችል ጠይቅ

ምዕራፍ 46

ሰዎች ልዩ የመሆን ስሜት እንዲሰማቸው ልታደርግ የምትችልበት ስምንት መንገዶች

1. ሰዎችን በስማቸው በመጥራት ልዩ የመሆን ስሜትን ልትፈጥርባቸው ትችላለህ፡፡

ሰዎችን በስማቸው ስትጠራ ልዩ የመሆን ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ራሳቸው እንዲህ ብለው ያስባሉ፣ “መጋቢው ያውቀኛል፡፡ ከሚያስታውሳቸው ጥቂት ስሞች ውስጥ አንዱ የእኔ ስም ነው፡፡ ልዩ ከሆኑ ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነኝ፡፡”

2. ለሰዎች ፈገግ በማለት እና ዓይናቸውን ውስጥ በማየት ልዩ የመሆን ስሜት ልትፈጥርባቸው ትችላለህ

አንዳንድ ፊቶች “ፈግታ የለሽ” ናቸው፡፡ አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮአቸው ኮስተር ያለ ጠባይ አላቸው፡፡ ይህ ኮስታራነት ወዳጅነትን አለመፈለግ ተደርጐ ሊነበብ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ከሆንክ፣ አሁንም ደግሜ እልሃለሁ መስታወት ፊት ቆመህ ፈገግታን ተለማመድ፡፡ እንዲያ ማድረግ ነበረብኝ! ፈገግ ማለትን እንዲያስታውሱህ ጓደኞችህን ጠይቅ፡፡ ባለቤቴ ሰዎችን ወዳጅ ማድረግን እንዳታስታውሰኝ ጠየቅኋት አደረገችውም!

3. ቅን በመሆን እና ሳታጋንናቸው ሰዎችን ልዩ የመሆን ስሜት ልትፈጥርባቸው ትችላለህ።

ሰዎችን ስትሸነግል፣ ስፍራ ላይሰጡህ ይችላሉ። የሆነ ደረጃ ላይ፣ እያሸሟጠጥካቸው እንደሆነ ያስባሉ። ምናልባትም በአእምሮአቸው ሊረግሙህ ይችላሉ።

ቅንነት የተሞላባቸውን ነገሮች ባትናገር፣ ማንም ሰው ከልቡ አይቀበልህም። ሰዎች አስተያየትህን እንዲቀበሉ ከፈለግህ፣ ማለት የፈለግኽውን ማለት እና የተናገርከው ነገር ለማት የፈለግኽውን መሆኑን ተለማመድ!

> በደለኛውን፣ "አንተ ንጹሕ ነህ" የሚለውን፣ ሕዝቦች ይረግሙታል . . .
>
> ምሳሌ 24፡24
>
> (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

4. የሰዎችን መልካም ነገር በማየት ልዩ የመሆን ስሜትን ልትፈጥርባቸው ትችላለህ

ሁሉም ሰው መልካም እና መጥፎ ነገሮች አላቸው። ከአንድ ሰው ጋር ይህ ነው የሚባል ግንኙነት ለመገንባት ከፈለግህ በዚያ ሰው ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ላይ ልታተኩር ይገባል። እየቆየህ ስትሄድ፣ እውነተኛ ችግሮቹን ልታሳውቀው ትችላለህ። ሁል ጊዜ ይህን አስታውስ፡- እግዚአብሔር መልካም ያልሆኑ ነገሮችህን በየቀኑ ወይም በየሰዓቱ ቢያሳውቅህ፣ ምናልባት ተስፋ ልትቆርጥ ትችላለህ! ለዚያ ነው እግዚአብሔር ወራት እና ዓመታት እየሄዱ ሲሄዱ ቀስ በቀስ የሚለውጠን። እንደ እግዚአብሔር ሁን እና ለሰዎች መልካም ነገር እወቅና ስጥ። ጉድለቶችን ለማሳወቅ ጊዜ ይመጣል።

> የእምነትህም ኅብረት በእኛ ዘንድ ያለውን **በጎ ነገሩ ሁሉ በማወቅ**፣ ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍሬ እንዲያፈራ እለምናለሁ?
>
> ፊልሞና 1፡6

ይህ ጥቅስ እምነታችን ፍሬ የሚያፈራው ኃጢያታችንን ስናውቅ ነው አይልም! ኃጢዓታችን ሁሌም በፊታችን ነው። ብዙ ሰዎች ማንም ሰው ውድቀታችውን ሊያሳውቃቸው አያስፈልጋቸውም። ይህ ጥቅስ እምነታችን ፍሬ የሚያፈራው ለመልካም ነገራችን እንጂ ለመጥፎ ነገራችን እውቅና ስንሰጥ እንዳልሆነ ያስረዳናል።

5. ለሰዎች ጠቅላላ አስተያየት በመስጠት ልዩ የመሆን ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ ትችላለህ ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል

እንዲህ የመሳሳሉ ነገሮችን በል፡-

- *ሁል ጊዜ ሳይህ ደስ ይለኛል።*
- *ስለ ሕይወትህ ሁሌ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።*
- *አንተ እውነተኛ ባርኮት ነህ።*

ጠቅላላ አስተያየት ሰዎችን ደስ ያሰኛል። ሰዎች መልካም አስተያየት ሲሰጣቸው ለምን ደስ እንደሚሰኙ አያውቁትም! ብቻ ደስተኝነት ከውስጣቸው ይፈልቃል። ግን ማንንም ሰው አለማጋነንህን እና አለመሸንገልህን እርግጠኛ ሁን ቅን ሁን እናም ሁል ጊዜ ሰዎች ይቀበሉሃል።

6. ስለ ተወሰኑ ነገሮች አስተያየት መስጠት ሰዎች ልዩ የመሆን ስሜት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል መልካም ተግባራቸውን እንዲደግሙ ያደርጋቸዋል

ለምሳሌ ያህል፣ ለሰዎች ልዩ ነገር እንዲህ አስተያየት ልትሰጥ ትችላለህ፣

- *እንዴት በጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደምትመጣ ማየት ይመስጠኛል*
- *የትጋት ጸሎትህ ደስ ደስ ይለኛል*
- *በጣም ታምራለህ*

ስለ ተወሰኑ ነገሮች ለሰዎች አስተያየት ስትሰጥ፣ *በጣም ደስ ከመሰኘታቸው የተነሳ ሳያውቁት ያንን የተወሰነ ተግባር ይደግሙታል።*

7. ስለ ሰዎች በሌሎች በሰዎች ፊት አስተያየት መስጠት ልዩ የመሆን ስሜት እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል

ስለ አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ፊት መልካም ነገር ስትናገር፣ ለአስተያየተህ ቅመምን ይጨምራል። ማንም ሰው ልዩ አስተያየትን ከገበያ ሊገዛ አይችልም! መጋቢ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ለቤተ ክርስቲያን አባል አስተያየት ሲሰጥ፣ ማንም ሊያደርግ የማይችለውን ነገር እያደረገ ነው።

8. ስለ ሰዎች በስብሰባ ላይ አስተያየት በመስጠት ልዩ የመሆን ስሜት ልትፈጥርባቸው ትችላለህ

ሰዎችን በጓደኞቻቸው ፊት አስተያየት ስትሰጣቸው፣ ለብርቱ ሥራቸው እንደተሸለሙ ይሰማቸዋል። በጣም ልንመስጣቸው የምንፈልገው በደረጃችን ያሉ ጓደኞችንን ነው! ይህ የሕይወት እውነታ ነው። ብሎ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር እያደረጉ ያሉት ጓደኞቻቸው ወይም ባልደረቦቻቸው ስለሚያደርጉት ብቻ ነው። አንድ ሰው በባልደረቦቹ ፊት አስተያት መስጠት፣ የሚሞቅ ካባ መደረብ ነው። በእርግጥ፣ ለምን እንደሆነ እንኳ ሳያውቅ ወደ አንተ ይሳባል።

ምዕራፍ 47

በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል እንዴት ኅብረት ማድረግን ማበረታታት እንደሚቻል

በቤተ ክርስቲያን አባላት መካከል ኅብረት ማድረግ ለቤተ ክርስቲያን እድገት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ቁልፎች መካከል አንዱ ነው። መጋቢው ብቻ አይደለም ከአባላት ጋር ኅብረት ማድረግ ያለበት፣ ግን አባላትም እርስ በርሳቸው ኅብረት ማድረግ አለባቸው።

በቤተ ክርስቲያን አባሎች መካከል ኅብረት ማድረግን የሚያበረታቱ ስድስት ደረጃዎች

1. በአገልግሎት ጊዜ ጉባዔው እርስ በርሱ እንዲነጋገር ማበረታታት!

እርስ በርሳቸው ሰላምታ እንዲለዋወጡ ስታበረታታ ጉባዔውን አትበትን። አብዛኛውን ጊዜ በቀልድ መልክ እርስ በርሳቸው እንዲባባሉ እነግራቸዋለሁ። "ዛሬ ለምሳ ወደ ቤትህ አብሬህ ልመጣ እፈልጋለሁ።" አንዳድ ጊዜ እርስ በርሳቸው እንዲህ እንዲባባሉ እጠይቃለሁ፡ "እግብተሃል/ሻል? አኔን ለማግባት ታስቢያለሽ?" ይህ ሁሉንም ሰው እንዲስቅ እና አየሩን ቀለል በማድረግ ኅብረት እንዲያደርጉ ያበረታታል።

2. የቤተ ክርስቲያን አባላት እርስ በርሳቸው ኅብረት እንዲያደርጉ የቤተ ክርስቲያን ካምፕ ስብሰባዎችን እና ማኅበራዊ ስብሰባዎችን ማዘጋጀት

የካምፕ ስብሰባ ኅብረት ለማድረግ በጣም ምርጥ የሆነ ስብሰባ ነው። ሰዎች በጣም እንዲዝናኑ እና በቀላሉ እርስ በርሳቸው እንዲተዋወቁ ያደርጋል።

> በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሡ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር።
>
> የሐዋርያት ሥራ 2፡46

3. የቤተ ክርስቲያን አባሎች እርስ በርሳቸው እንዲጋቡ አበረታታ።

የቤተ ክርስቲያን አባላት ሊያገቡት የሚፈልጉት ዓይነት ሰው በጉባዔው ውስጥ ሊገኝ እንደሚችል እንዲያወቁ አድርግ። አንዴ የቤተ ክርስቲያን አባላት እርስ በርሳቸው መጋባት ከጀመሩ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የበለጠ መረጋጋት ይኖራል።

4. የቤተ ክርስቲያን አባላት ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባላትን ሥራ እንዲቀጥሩ አበረታታ

> በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ . . .
>
> የሐዋርያት ሥራ 4፡34

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ግንኙነት ኅብረት ማድረግ ሥር እየሰደደ ሲሄድ መተሳሰርም ስር እሰደደ ይሄዳል። ቀጣሪ እና ተቀጣሪ በአንድ መጋቢ ስር በአንድነት ይቀመጣሉ። እያንዳንዱ ትልቅ ቤተክርስቲያን ብዙ እርስ በርሳቸው የተቆራኙ እና ኅብረት የሚያደርጉ አባላት አሉት። ይህ ልክ የማይገኝለት ግንኙነት ነው ጉባዔው እንዲራጋጋ የሚያደርገው!

5. የቤተ ክርስቲያን አባላት በደስታ እና በሀዘን ጊዜ እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ አበረታታ

የቤተ ክርስቲያን አባላቶች በሌሎች ጉዳይ ተካፋይ መሆን ኃላፊነታቸው እንደሆነ እንዲያውቁ አድርግ። ሰዎች እንዲያደርጉ የነገርካቸውን ነገር እንደሚያደርጉ እና የምትለውን እንደሚያምኑ ልትገነዘብ ይገባሃል። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ነው።

> ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፣ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ
>
> ሮሜ 12፡15

6. የቤተ ክርስቲያን አባላቶች ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጓደኛ እንዲያበጁ እና እርስ በርሳቸው ቤታቸው እንዲገባበዙ አበረታታ።

> ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፣ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ።
>
> የሐዋርያት ሥራ 2፡44

ሰዎች አንድ ጊዜ ከጉባኤው መካከል ጓደኞች ካሏቸው፣ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ይጣበቃሉ። ቤተ ክርስቲያንን መተው ትንሽ የተወሳሰበ ይሆንባቸዋል። አሁን ቤተ ክርስቲያንን መተው ማለት ጓደኞቻቸውን ሁሉ መተው ይሆንባቸዋል። በቤተ ክርስቲያን አባላቶች መካከል ጎብረት ማድረግ በእውነት ለቤተ ክርስቲያን መረጋጋት እና የቤተ ክርስቲያን እድገት የሚያበረታታ ቁልፍ ነው።

ምዕራፍ 48

P. V. T. I

ጸ. ጉ. ማ. ጎ

ያካፈልኩህ አራት ዋነኛ የመጋቢ አገልሎቶችን ነው፡፡ ጸሎት፣ ጉብኝት፣ ማስተማር እና ጎብረት ማድረግ (P. V. T . I) እነኚህን ነገሮች እንድታሰላስል እና በአገልግሎትህ ውስጥ እንድትተገብራቸው ጸሎቴ ነው፡፡

ጸሎት፣ ጉብኝት፣ ማስተማር እና ጎብረት ማድረግ P. V. T . I (Prayer, visitation, teaching and interaction) የሚለውን ኮድ አስታውስ እናም በአገልግሎትህ ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚገባህ ሁሌም ታውቃለህ፡፡ በመቅደሱ ውስጥ ያለውን ወርቅ በናስ እንዳትለውጥ ጸሎቴ ነው፡፡

ከእውነተኛ አገልግሎት ጋር ጽና እናም ሽልማትህን በሰማያት ካለው እግዚአብሔር ትቀበላለህ፡፡ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት አትሞክር፡፡ “ሲዶ ሚኒስትሪን (የውሸት አገልግሎትን)” አስወግድ! የጠራህ እግዚአብሔር ነው፣ እናም ደስ ልታሰኘው የሚገባህ እርሱን ነው!

አገልግሎትህን ስትፈጽም እግዚአብሔር የልብህን መሻት ይፈጽምልህ እነኚህን አራት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን እድገት ቁልፎች በተግባር ስታውል በአገልግሎትህ ውስጥ ጥሩ ስኬትን እንደምትለማመድ እምናለሁ፡፡ *ጸሎት፣ ጉብኝት፣ ማስተማር እና ጎብረት ማድረግ!*

ስለ ጸሀፊው

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ በአንዲት ጋና ውስጥ በምትገኝ የገጠር ከተማ የሕክምና ትምህርቱን በመከታተል ላይ ሳለ፣ አንድ ምሽት እግዚአብሔርን በጸሎት ሲጠባበቅ፣ ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ቀባው። ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ "ካሁን ጀምሮ ማስተማር ትችላለህ . . ." የሚል ድምጽ በመስማት ተቀባ። ይህ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ጥሪ ነው ወደ ዓለም አቀፋዊ አገልግሎቱ ያመራው።

ዛሬ፣ "ፈዋሹ ኢየሱስ ክሩሴድ (HEALING JESUS CRUSADE) " የተሰኘው አገልግሎታቸው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን የሚገኙበት እና በብዙ ተዓምራቶች የታጀበ ነው። እነዚህ አስደናቂ ተዓምራቶች በሕክምና ዶክተሮች የተረጋገጡ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ማየት የተሳናቸው ዓይኖች በርተዋል፣ መስማት የተሳናቸው ጆሮዎች ተከፍተዋል፣ ዊልቼሮች ባዶ ሆነዋል እንዲሁም መታን እንኳ ተነስተዋል።

ዳግ ሂዋርድ ሚልስ፣ በርካታ ተፈላጊ መጽሐፍ የጻፉና ዓለምአቀፋዊ ዲኖምኔሽን በመሆን ላይ የምትገኘው "የላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል" ቤተ ክርስቲያን መስራች ናቸው። የሬድዮ፣ ቴሌቪዥን እና የኢንተርኔት መርሃግብራቸው በመላው ዓለም በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን በመድረስ ላይ ይገኛል። ሌሎች የወንጌል ስርጭት አገልግሎታቸው የመጋቢዎች እና የአገልጋዮች ኮንፍረንሶችን ማካሄድ እና አናካዘ የመጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎት እና ስልጠና ማዕከልን ያጠቃልላል።